በእንተ አሕዛብ

በዚኽ «እንተ አሕዛብ» በተሰኘው መጠነኛ ጽሑፍ ውስጥ በዋናነት ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ እነዚኽም፡-

1. ክፍል አንድ ላይ የሰይጣንንና የመሐመድን ጥልቅ ቁርኝት በዝርዝር እናያለን፡፡
2. ክፍል 2 ጂሃድ-የእስልምና እምነት ማስፋፊያ መንገድ! (jihad- the Way of Islam)
3. ክፍል ሦስት ላይ ወሲብ በእስልምና /Sex in Islam/ ማለትም ከሞት በኋላ ባለው ዘላለማዊው ሕይወት በሙስሊሞች ጀነት (ገነት መንግሥተ ሰማያት) ውስጥ ዝሙት ከ72 ደናግላን ጋር እንደሚፈጸም በጣም በጥልቀትና በዝርዝር እናያለን፡፡ ሙሉ ጽሑፉ የቀድሞዋ አሚና መሐመድ የአሁኗ ወለተ ማርያም ካዘጋጀችው መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

የአዘጋጇ አድራሻ፡-
Tel: +447423549663
E-mail: elishaday27@gmail.com

ማሳሰቢያ፡- በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የቁርአንና የሐዲስ አስተምህሮዎችንና ጥቅሶችን በማንኛውም ኢስላማዊ መካነ ድሮች (web sites) ላይ ገብተው ከዚያ ላይ ማረጋገጥ እንደሚቻል ሳልጠቁም አላልፍም፡፡

መግቢያና መግባቢያ

በአጠቃላይ በእስልምና እምነት ታሪክ ውስጥ ሱኒና ሺዓ የተባሉ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ሱኒዎች በዓለም ላይ ካለው የእስልምና እምነት ውስጥ እስከ 90% የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ የተቀሩት ደግሞ ሺዓዎች ናቸው፡፡ በጋራ ሁለቱም ክፍሎች የሚስማሙበትና የሚያምኑበት ነገር አላቸው፡፡ ይህም ሁሉም ሙስሊሞች የሚመሩባቸው የአላህን «ፍጹም መለኮታዊ ቃል» የያዙ ሁለት መጽሐፎች አሏቸው- ቁርአንና ሐዲስ፡፡ ቁርአንና ሐዲስ የእምነቶቹ ምንጮችና ዋነኛ መመሪያዎች ናቸው፡፡ የሸሪዓውም ሕግ ከሁለቱ ተውጣቶ ነው የተዘጋጀው፡፡ ቁርአኑና ሐዲሱ በአተገባበርና በአፈፃፀም ደረጃ አንድ ናቸው፡፡ ልዩነታቸው የአመጣጣቸው ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ እንደ እስልምናው እምነት ቁርአኑ ለሰው ልጆች ሁሉ መመሪያ ይሆን ዘንድ በቀጥታ ከአላህ በመልአኩ በጂብሪል (በገብርኤል) በኩል ለነቢያቸው ለመሐመድ የተሰጠ መገለጥ ሲሆን ሐዲሱ ደግሞ አላህ በሙስሊሞቹ ነቢይ በመሐመድ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ በመገለጥ ለአማኞቹ መልእክቱን ያስተላለፈበት መንገድ ነው፡፡ ቁርአኑ የሙስሊሞቹን ነቢይ የመሐመድን ቀጥተኛ የሆኑ መለኮታዊ መገለጦችን (revelations) የያዘ ሲሆን ሐዲሱ ደግሞ ነቢያቸው መሐመድ የተናገሯቸውን ንግግሮች፣ ያደረጓቸውን ድርጊቶች፣ ያዘዟቸውን ትእዛዞች፣ የመከሯቸውን ምክሮች...በአጠቃላይ ከነቢያቸው ከመሐመድ ሕይወት ጋር የጠቆራኙ ባሕሎችን (traditions) እና አባባሎችን (sayings) ያካትታል፡፡ አላህ ቁርአኑን ለሙስሊሞቹ ነቢይ ለመሐመድ በማውረድ ለአማኞቹ መመሪያ አድርጎ ሲሰጥ ሐዲሱን በተመለከተ ግን መመሪያዎቹን በነቢያቸው በመሐመድ ሕይወት ውስጥ እንዲገለጡ አድርጓል ተብሎ በአማኞቹ ዘንድ በጽኑ ይታመናል፡፡ "I have left you two things and you will not stray as long as you hold them fast. The one is the Book of Allah and the other the Law (Sunnah) of his Prophet." (Mishkat 1:120, Volume 1, page 173).
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያደረጓት ወይም የተናገሯት እያንዳንዷ ነገር አላህ በነቢያቸው በመሐመድ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ለሙስሊሞች ያስተላለፉት መለኮታዊ ሕግ እንደሆነች በጽኑ ይታመናል፡፡ ይህቺ አንዷ ድርጊት ወይም ንግግር ሱና ትባላለች፡፡ የሱናዎቹ

ስብስብ ሐዲሱን ፈጥሯል፡፡ የነቢያቸው የመሐመድ ሕይወቱ በአጠቃላይ አላህ የተናገራቸውን ነገሮች በሙሉ በተግባር ያሳየ ተብሎ ይታመናል፡፡

ሐዲስ ማለት በአጭሩ አላህ ቁርአኑን በተግባር ያሳየበትና ያረጋገጠበት መንገድ ማለት ነው፡፡ ሙስሊም ምሁራኖቻቸውም (Muslim scholars) ይህንን የሚገልጹበት መንገድ ተመሳሳይ ነው፣ (The hadith is the Qur'an in action. Muhammad's life is a visible expression of Allah's utterances in the Qur'an) በማለት ይገልጹታል፡፡ በመሆኑም ቁርአኑም ሆነ ሐዲሱ በመመሪያና በአተገባበር ደረጃ የሚሰጣቸው ቦታ እኩል ነው፡፡ እንዳውም በተሻለ ቋንቋ እንግለጸው ከተባለ ቁርአኑን ያለ ሐዲሱ መረዳት ፈጽሞ አይቻልም፡፡
"Indeed the Quran without the Hadis remains unintelligible in many cases in the work-a-day life of a man. It is the very injunction of the Quran to follow the Prophet in all his deeds and sayings. Therefore if the Quran is believed, there is no other alternative but to believe in the Hadis of the Prophet.
በአማኞቹ ዘንድ ሐዲሱን እንደ ቁርአኑ አድርጎ የማይቀበል ሰው ልክ እንደማያምን ከሐዲ ነው የሚቆጠረው፡፡ በአረብኛው "ካፊር" (kafeer) ይሉታል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሙስሊም በየትኛውም ቦታ ቢሆን ነቢያቸው መሐመድ ያደረጓትንና የተናገሯትን ሁሉ የማድረግና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ መስጊድ ውስጥም ይሁን ሥራ ቦታ፣ ጦር ሜዳም ይሁን ሽንት ቤት...ብቻ የትም ይሁን የት ነቢያቸው መሐመድ ያደረጉትን ነገር የማድረግና ያዘዙትን ትእዛዝ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡
ቁርአኑም ይህንኑ ሲያረጋግጥ"መልእክተኛው የሰጣችሁን ማንኛውንም ነገር ያዙት፡፡ እርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡ አላህንም ፍሩ፤ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና" ነው ያለው፡፡ ሱረቱ አል-ሐሽር 59፡7፡፡ በሌላም ቦታ እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ተገልጧል፡፡ "አላህና መልእክተኛውም ነገርን በፊረዱ ጊዜ ለምእመናንና ለምእመናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም" ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡36፡፡
ነቢያቸው መሐመድም ራሳቸው ሲናገሩ "እኔን የሚታዘዝ ጀነት ይገባል..." ነው ያሉት፡፡ "Whoever obeys me shall enter Paradise and whoever disobeys me, has indeed rejected truth." (Mishkat 1:97, page 159). በእነዚህ ምክንያት ነው አንድ ሙስሊም ነቢያቸው መሐመድ ያደረጉትን ማንኛውንም ነገር የማድረግና ያዘዙውን ትእዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት፡፡ ለዚህ ታማኝ የሆኑ አማኞችን ታዲያ ለየት ያለ ድርጊት ሲያደርጉ አይታችሁ "ምነው?" ብትሏቸው "ሱና" ነው ይሏችኋል፡፡ ሱና ማለት የነቢያቸው አንዲ ድርጊታቸው ወይም ንግግራቸው ናት፡፡ ለምሳሌ፦

ሙስሊም ወንዶች ፂማቸውን ቀለም ይቀባሉ፡፡ ይህ አንድ ሱና ነው፡፡ ፂማቸውንም ቀለም የሚቀቡት ነቢያቸው መሐመድ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ስለማይቀቡ እናንተ በተቃራኒው መቀባት አለባችሁ ብሎ ስላዘዟቸው ነው፡፡ ይህንንም ሐዲሱ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- "The Prophet said, 'Jews and Christians do not dye their hair so you should do the opposite of what they do.'" Sahih Bukhari 7:72:786 (ዝርዝር ሁኔታውን በኋላ በደንብ እናየዋለን) ግን አሁን በአጭሩ መጥቀስ የፈለኩት ነገር በዚህ ዘመን በዓለም ላይ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ እየተደረገ ያለው ማንኛውም ነገር የነቢያቸው የመሐመድ ነፀብራቅ መሆኑን አስምሬበት ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡
ስለ ሐዲሱ ይህችን ታህል ለማንሳት የፈለኩት ከዚህ በኋላ የሚቀርበው ሙሉው ጽሑፍ ከቁርአኑና ከሐዲሱ የተወሰደ ስለሆነ ሐዲስ ሲባል ምን እንደሆነ መነሻ የሚሆን ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡ የሐዲሱ ስብስቦች ምን ምን እንደሆኑ እንይና ወደ ዋናው ነጥብ እገባለሁ፡፡ ስድስት ዋና ዋና የሐዲስ ስብስቦች ናቸው ያሉት፡፡ እነርሱም፡- ሳሂህ ቡኻሪ (Sahih Bukhari)፣ ሳሂህ ሙስሊም (Sahih Muslim)፣ አቡ ዳውድ (Abu Dawud)፣ ማሊክ ሙዋታ (Maliks Muwatta)፣ ሻማ ኢል-ቲርሚድ (Shama-il Tirmidhi) እና ሐዲስ ቁድሲ (Hadith Qudsi) ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስብስቦች ከሁሉም በተሻለ እጅግ ታማኞችና እውነተኛ ተደርገው ነው የሚወሰዱት፡፡ Sahih የሚለውን ቃል "genuine or authentic" ወይም በአማርኛው "እውነተኛ" የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባ ቃል ነው፡፡ በዝርዝር እንያቸው፡-
Sahih Bukhari፡ ከ7000 በላይ ስብስቦች ያሉት ሲሆን በእውነተኛነቱና በታማኝነቱ ከሁሉም የበላይ ተደርጎ ይታያል፡፡ አሰባስቦ ያዘጋጀው ኢማም Bukhari በ256 A.H ነው የሞተው፡፡ M. Muhsin Khan ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡ (A.H after hijra ማለትም ነቢያቸው መሐመድ በ622 ዓ.ም ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱበትን ዘመን ይዘው ሙስሊሞች ዘመናቸውን የሚቆጥሩበት ነው)
Sahih Muslim: በእውነተኛነቱና በታማኝነቱ በ2ኛ ደረጃ ተቀምጧል፡፡ ከ4,000 በላይ ስብስቦችን የያዘውን ይህንን ሐዲስ በ261 A.H. ከመሞቱ በፊት Muslim ibn al-Hajjaj የተባለው ሰው ሰብስቦ ያዘጋጀው ሲሆን Abdul Hamid Siddiqui ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡
Abu Dawud: 4,800 ስብስቦችን የያዘው ይህ ሐዲስ ከ6ቱ ዋና ዋና የሐዲስ ስብስቦች ውስጥ በ3ኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው፡፡ ሐዲሶቹን ያሰባሰባቸው Abu Dawud ሲሆን prof.Ahmad Hasan ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡
Maliks Muwatta፡ ይኸኛው ሐዲስ በቀደምትነቱ ከሁሉም ይበልጣል፡፡ ያሰባሰበውና ያዘጋጀው ኢማም Malik ibn Anas ሲሆን A'isha `Abdarahman ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡
የተቀሩት ሁለቱ (Shama-il Tirmidhi እና Hadith Qudsi) እንደ ሌሎቹ ሐዲሶች ብዙም ተዘውትረው አይጠቀሱም፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ግን ከቁርአኑ እኩል እጅግ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ እኔም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማጣቀሻነት የተጠቀምኩት በዋናነት እነዚህን የሐዲስ ስብስቦች በተለይም የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ነው፡፡ ቁርአኑ በዋናነት እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ስድስት ዋና ዋና የሐዲስ ስብስቦች በተጨማሪ ከሁሉም እውነተኛና ታማኝ ሐዲሶች ውስጥ የተውጣጡ በርካታ የነቢያቸውን የመሐመድን ንግግሮችና ድርጶች የያዘ al-Baghawi በተባለ ሰው የተዘጋጀ "Mishkat-al-Masabih" የተባለ ጥንታዊ መጽሐፍ አለ፡፡ James Robson ወደ እንግሊዝኛ የተረጎመውን ይህን መጽሐፍም ለማጣቀሻነት ተጠቅሜበታለሁ፡፡
ሌላው በማጣቀሻነት የተጠቀምኩበት መጽሐፍ ከሁሉም ኢስላማዊ ጽሑፎች ውስጥ እጅግ ጥንታዊ የሆነውና በ750 ዓ.ም የተጻፈው የኢብን ኢሻቅ "Sirat Rasul Allah" መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በጥንታዊነቱ የመጀመሪያ ነው፡፡ ቁርአኑንንም ሆነ ሁሉንም ሐዲሶች

ይቀድማል:: ቁርአኑ በሙስሊሞቹ ነቢይ በመሐመድ ተከታይ ከሊፋዎች አማካኝነት ተሰብስቦ በአንድ ጥራዝ መልክ የተዘጋጀው ነቢያቸው መሐመድ በ632 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ቢያንስ 200 ዓመትና ከዚያ በላይ ቆይቶ ነው:: ይህን እጅግ ጥንታዊ የሆነና የነቢያቸውን የመሐመድን የሕይወት ታሪክ (biography) የያዘ መጽሐፍ ግን የተጻፈው በ750 ዓ.ም ነው:: በዚህ ዘመን መጽሐፉን በጣም ጥልቀትና ስፋት ባለው መልኩ የጻፈው ኢብን ኢሻቅ (Ibn Ishaq) ሲሆን እርሱ "Sirat Rasul Allah" በሚል ርዕስ የጻፈውን Alfred Guillaume የተባለው ጸሐፊ "The Life of Muhammad" ማለትም «የመሐመድ ሕይወት» በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1955 ዓ.ም ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል:: ይህንን መጽሐፍ እኔም ባዘጋጀሁት ጽሑፍ ላይ በምንጭነት ተጠቅሜበታለሁ:: ሌሎችም እንዲሁ በቀደምትነት የተጻፉ ኢስላማዊ መጽሐፎችን ለማየት በጣም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል:: ስለዚህ ይህ መጽሐፍ ቁርአኑን፣ ሐዲሱንና ጥንታዊ የሆኑ ኢስላማዊ መጽሐፎችን ብቻ መሠረት ተደርጎ የተጻፈ ስለሆነ መጽሐፉ "based upon the earliest & original source of Islamic manuscripts" "የመጀመሪያና ጥንታዊና የሆኑ ኢስላማዊ ጽሑፎችን መሠረት ተደርጎ የተዘጋጀ" ነው መባሉ ትክክልና አሳማኝ ነው፤ ተገቢም ነው::

መልካም ንባብ! ጽሑፉን አንብባችሁ የአሕዛብን እርኩሰት በማየት ለሚፈጠርባችሁ መጥፎ ስሜት አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ::

የሰይጣንና የመሐመድ ቁርኝት

እስቲ እኔ ምንም ነገር ከመናገሬ በፊት እነዚህን የቁርአንና የሐዲስ ጥቅሶችን በደንብ ተመልከቷቸው:-

1. በሐዲሱ በሳሂህ ቡኻሪ 9:87:111 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻለው:- «ከጥቂት ቀናት በኋላ ዋራቃ ስለሞተ መለኮታዊው መገለጥም ለትንሽ ጊዜ መውረዱን አቁሞ ነበር:: እናም ነቢዩ በጣም አዝኖ እንደነበርና ብዙ ጊዜ ራሱንም ከተራራው ጫፍ ላይ ሊወረውር አቅዶ እንደነበር ሰማን:: ራሱን ቁልቁል ለመወርወር ብሎ በየጊዜው ወደ ተራራው ጫፍ ይወጣ ነበር:: ጂብሪልም ከፊቱ እየታየው 'አ መሐመድ ሆይ! አንተኮ በእውነት የአላህ ሐዋርያ ነህ' ይለው ነበር:: መሐመድም ልቡ ፀጥ ሲልና ሲረጋጋ ወደቤቱ ይመለሳል:: የመለኮታዊው መገለጥ ለረጅም ጊዜ ሳይመጣ ሲቆይ እንደበፊቱ ያደርጋል:: ነገር ግን የተራራው ጫፍ ላይ በደረሰ ሰዓት ጂብሪል ከፊቱ ይሆንና ከአሁን በፊት የተናገረውን ደግሞ ይነግረዋል::" Bukhari Volume 9, Book 87, Number 111: «after a few days Waraqa died and the Divine Inspiration was also paused for a while and the Prophet became so sad as we have heard that he intended several times to throw himself from the tops of high mountains and every time he went up the top of a mountain in order to throw himself down, Gabriel would appear before him and say, "O Muhammad! You are indeed Allah's Apostle in truth" whereupon his heart would become quiet and he would calm down and would return home. And whenever the period of the coming of the inspiration used to become long, he would do as before, but when he used to reach the top of a mountain, Gabriel would appear before him and say to him what he had said before.»
2. ቁርአኑ ሱረቱ አል-ሐጅ 22:52 ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል:- «ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም፣ ባነበበና ዝም ባለ ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ ማጥመሚያን ቃል የሚጥል ቢሆን እንጂ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፤ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል::» በዚህ የቁርአን ጥቅስ መሠረት ሰይጣናዊ ጥቅሶች ለመሐመድ ተሰጥተውታል:: መሐመድ የቁርአን ክፍሎች እንዲሆኑ አንዳንድ ጥቅሶችን ተናግረዋል ነገር ግን በእርግጥ ጥቅሶቹ የመጡት ከሰይጣን ነበር፣ ነገር ግን የሰይጣን ጥቅሶች ተደምስሰው በተሻሉ ጥቅሶች ወይንም በተመሳሳይ ጥቅሶች ተተክተዋል:: ይህም በቁርአኑ 2:106 እና 22:52-53 ላይ ተጠቅሷል::
3. ከላይ በቁ.2 እንዳየነው ሰይጣን በመሐመድ ልብ ውስጥ ማጥመሚያ ቃልን በመጣል ብቻ አላበቃም ይልቁንም ሰይጣንና መሐመድ አብረው ተዘርረው ይሰግዱ ነበር:: መሐመድ የአል-ነጂምን ሱራ በቃላቸው ከተረኩ በኋላ ከመስሊሞች፣ ከፓጋን አረቦችና ከጂኒዎች ማለትም ከሰይጣኖች ጋር ሆነው በከፍተኛ ድካም መሬት ላይ ተዘርረው እንደነበር በሐዲሱ ላይ ተዘግቧል:: "The Prophet performed a prostration when he finished reciting Surat-an-Najm, and all the Muslims and pagans and Jinns and human beings prostrated along with him." Sahih Bukhari 6:60:385

4. በሐዲሱ ላይ የተመዘገ አንድ አስገራሚ ታሪክ አለ፡፡ አንድ ሰው የኡምራ ጉዞ ሊያደርግ አስቦ ከዚያ በፊት ምን ማድረግ እንዳለበት ለመጠየቅ ወደ መሐመድ በመጣ ሰዓት ድንገት መገለጡ በመሐመድ ላይ ይመጣል፡፡ ይህን ጊዜ አብሮ የነበረው ኡማር መሐመድን በጨርቅ ይሸፍናቸዋል፡፡ ኡመርም ለእንግዳው ሰው መገለጡቹ ለመሐመድ እየመጡላቸው መሆኑን ይነግረዋል፡፡ መሐመድም በጨርቅ ተጠቅልለው እንደተኙ እያዓሩና እያሸካኩ ሲጮሁ እንግዳውም ሰው አይቷቸዋል፣ ሰምቷቸዋል፡፡ እያዓሩ ሳለ ድምጻቸውን መጀመሪያ ሲሰማው የግመል ድምጽ ነው ብሎ ገምቶ ነበር፡፡ ይህንን የመሐመድ ድርጊት አላህ ከእሳቸው ጋር የተገናኘበት መንገድ እንደሆነ ነው እንግዳው ሰው የተረዳው፡፡ ኡመርም የነገረው ይህንኑ ነው፡፡ መሐመድም መንፈሱ ለቋቸው ወደ ማንነታቸው ከተመለሱና ተሸፍነውበት የነበረውን ጨርቅ ከገለፁት በኋላ «ስለ ኡምራ የጠየቀኝ ሰው የታለ?» በማለት ጥያቄውን መልሰውለታል፡፡ (Sahih Muslim Book 007, Number 2654) ይህ ዓይነቱ የመሐመድን ክስተት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት አንዳንድ ባዕድ አምልኮ ከሚፈጽሙ ጠንቋዮች ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በጨርቅ ተጠቅልሎና ተሸፋፍኖ ማዓራት የጠንቋዮች አሠራር ነው፡፡ እርግጥ ነው ይህ ዓይነቱ አሠራር በነ አዳል ሞቴና በነ ጠቋር ዘንድ ብቻ ያለ አሠራር ነው፡፡
5. የመሐመድ በሰይጣን የመያዛቸው ጉዳይ በወቅቱ አጠገባቸው ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ለሚስቶቻቸውም ጭምር ግራ ያጋባ ስለነበር ሚስቶቻቸው “ምናልባት መተት ተደርጎበት ይሆን እንዴ?” ብለዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ አይሻ እንዲህ ነው ያለቸው፡- “አንድ ጊዜ ነቢዩ መተት ተደርጎበት ነበር፤ ስለዚህም በእውነት ያላደረገውን ነገር እንዳደረገው አድርጎ መገመትንና ማሰብን ጀምሮ ነበር” Aisha narrated: "Once the Prophet was bewitched so that he began to imagine that he had done a thing which in fact, he had not done." (Sahih Al-Bukhari, Number 3175.) የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በአንድ አይሁዳዊ ሰው መተት ተደርጎባቸው እንደነበር በሐዲሱ ላይ ሌላም የተዘገበ ታሪክ አለ፡፡ “ነቢዩ በአይሁዳዊ ሰው መተት ተደርጎበታል፣ ለብዙ ጊዜ የሚያደርገውንም ነገር አያውቅም ነበር” ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ The Prophet had been bewitched by a Jew, and for several days he did not know what he was doing. (Bukhari, 59/11; 76/47; Hanbal 6/57; 4/367) “በአላህ መልእክተኛ ላይ አስማት ተሰርቶ ነበር፣ ስለዚህም እርሱ ግብረ ስጋ ግንኙነትን ከሚስቶቹ ጋር ሳያደርግ እንዳደረገ አድርጎ ያስብ ነበር፡፡” “Aisha narrated: Magic was worked on Allah’s Apostle so that he used to think that he had had sexual relations with his wives while he actually had not. (Ibid, Number 5765.)
6. የቀርአኑ 72ኛው ሱራ(ምዕራፍ) በራሱ በሰይጣን ስም የተሰየመ ነው፡፡ «ሱረቱ አል-ጂን(የጋኔን ምዕራፍ)» ይላል ሙሉ ርዕሱ፡፡ ገና ሲጀምርም 72፡1 ላይ የሰይጣን ጭፍሮች ቁርዓንን እንደሚያዳምጡ ይናገራል፡፡

አሁን ወደ እኔ ሀሳብ ልምጣና ቀጣዩን ርዕስ በጥሞና እንመለከተው፡-

ሰይጣናዊ መገለጦች (Satanic Verses)፡- ከሁሉም በፊት እስቲ እንድ ነገር እናስብ! ያልሆነና ፍጹምም ሊሆን የማይችል ቢሆንም ግን ግዴለም ለጊዜው እኛ እናስበው እስቲ! ምን እናስብ አትሉኝም? ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ከጥምቀቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወዲያው ነው በፈቃዱ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ በሰይጣን የተፈተነው፡፡ *“ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው”* እንዲል መጽሐፍ፡፡ ማቴ 4፡1-3፡፡
ምንም እንኳን ለባሕርይው ፍጹም የማይስማማው ቢሆንም እኛ ግን እንዲህ ብናስብስ! ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈተናውን ማለፍ ባይችል ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር? ብለን እናስብ፡፡ ለምን ይህን እንዳልኩኝ በኋላ ላይ በደንብ ትረዱታላችሁና አሁን ግር አይበላችሁ፡፡ ይልቁንም አሁን አብረን እናስበው! መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሰይጣን ካቀረበለት ከ3ቱ ፈተናዎች በአንዱ እንኳ ተሸንፎለት ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር? በክርስቶስ ያገኘናቸውን ጸጋዎች ከዚያ በኋላ ማግኘት ይቻለን ነበር? ሰይጣን ለክርስቶስ ባቀረበው ፈተና ድል አግኝቶ ቢሆን ኖሮ አሁን በዓለም ላይ ያለው የክርስትናው ገፅታ ምን ሊመስል እንደሚችል አስባችሁታል? አዳም ለሰይጣን ፈተና ተሸንፎ ዕፀ በለስን ስለበላ አይደል 5500 ዘመን ሙሉ በኢጋንንት ሲቀጠቀጥ የኖረው? ይህም ሕገ እግዚአብሔርን የመጣሱና በሰይጣን ፈተና የመሸነፉ ውጤት ነው እንጂ የአንዲት ዕፀ በለስ መበላት ለእግዚአብሔር ጉዳዩ ሆኖ አይደለም፡፡ በአጭሩ ለማለት የፈለኩት በሰይጣን ፈተና መሸነፍ ውጤቱ እጅግ የከፋ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሰይጣን ለጌታችን ባቀረባቸው ፈተናዎች ድል አድርጎ ቢሆን ኖሮ ብለን እንድናስብ የፈለኩት፣ ምንም እንኳ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል ቢሆንም ማለት ነው፡፡

ጌታችን የሰይጣንን ሦስት የተለያዩ ፈተናዎች በአሸናፊነት ተወጥቷቸዋል፡፡ ለእኛም የምናሸንፍበትን ኃይልና ጥበብ ሰጥቶናል፡፡

ለክርስቶስ የቀረቡለት ሦስት ፈተናዎች ስስት፣ ትዕቢትና ፍቅረ ንዋይ (የገንዘብ ፍቅር) ነበሩ። ጌታችን 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ መራቡንና መጠማቱን ያየ ሰይጣን እነዚህን ድንጋዮች ዳቦ አድርግ በማለት በስስት ቢፈትነው "ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" በማለት በትዕግስት አሸነፈው። ማቴ 4፡4። በሁለተኛው ፈተና ወደ ቤተመቅደስ ጫፍ አውጥቶ መላእክት ስለሚጠብቁህ እስቲ ራህን ከዚህ ወርውር ብሎ በትዕቢት ቢፈትነው "አምላክህን አትፈታተነው ተብሏል" በማለት በትሕትናና በጥበብ አሸነፈው። በ3ኛው ፈተና ደግሞ የዓለምን ግዛት ከነክብሩ አሳይቶት ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ ብሎ በገንዘብ ፍቅር ቢፈትነው "ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፣ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሏል" በማለት ገንዘብን በመጥላት አሸንፎታል። ሰይጣንም ከዚህ በኋላ መሸነፉን ሲያውቅ እንደ ጢስ ተኖ እንደ አቧራ በኖ ጠፍቷል።

አሁን የሙስሊሞቹን ነቢይ የመሐመድን ጉዳይ ማየት እንችላለን። ሰይጣን ልክ ጌታችንን እንደፈተነው ሁሉ ሌሎች ሰዎችንስ መፈተኑ ይቀራልን? እነዚያስ ሰዎች ፈተናውን በምን መልኩ ተወጡት? አንድ ቀላል ምሳሌ እንውሰድ፡- መሐመድ ኃጢአተኛ መሆናቸውን ቁርአኑ ራሱ በግልጽ እንደመሰከረባቸው አይተናለል። በአንጻሩ ደግሞ ቁርአኑ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት ያልተገኘበት ንጹሕ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ እንዲያው ነገሩን እንደ ቁርአኑ አስተሳሰብ እንኳ እንየውና ፍጹም ከኃጢአት ንጹሕ የሆነው ክርስቶስ በሰይጣን ከተፈተነ ኃጢአተኛው መሐመድ የማይፈተኑበት ምንም ምክንያት የለም። በዚህ ምንም ጥርጥር የለንም፣ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ነን። ታዲያ ዋናው ነጥብ አሁን ነው መነሳት ያለበት። ነቢያቸው መሐመድ በሰይጣን የቀረበላቸውን ፈተናዎች በምን መልኩ ተወጡት? እንዴትስ ነው የተፈተኑት? የመሐመድ የፈተና ውጤት በወቅቱ ለነበረውም ሆነ አሁን ላለው ዓለም ያስገኘው ውጤት ምንድነው? ቀጥሎ በሐዲሱ ላይ ተጽፎ የተቀመጠውን ነገር ስናነብ የእነዚህንና የሌሎችንም ጥያቄዎች ሁሉ ግልጽ የሆነ መልስ እናገኛለን።

በሳሂህ ቡኻሪ ሐዲስ ላይ በግልጽ ተጽፎ የተቀመጠ አንድ ታሪክ ነገር አለ። ማለትም የጂብሪልና የመሐመድ የመጀመሪያ ግንኙነታቸውን ምን ይመስል እንደነበር፣ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተገናኙ የሚናገር አንድ አስገራሚ ታሪክ አለ። በቅድሚያ እርሱን ማየቱ የተሻለ ነው። በሳሂህ ቡኻሪ 9:87:111 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻለው፡- "ለአላህ ሐዋርያ እርሱ ተኛቶ ሳለ በህልሙ መለኮታዊው መገለጥ በእውነተኛ መልክ መታየት ጀመረ። ህልም አልነበረም ያየው ነገር ግን እንደ ብሩህ ቀን ብርሃን እውነት ሆነ እንጂ። ነቢዩ ለተከታታይ ብዙ ቀናቶችና ሌሊቶች አላህን ብቻ ወደሚያመልክበት ወደ ሂራ ዋሻ ይሄድ ነበር። የሚያቆየውን ያህል ምግቡንም አብሮ ከእርሱ ጋር ይወስድ ነበር። በሌላም ጊዜ ለመቆየት የሚያስችለውን ምግብ ደግሞ ለመውሰድ ወደ ሚስቱ ከድጃ ተመልሶ ይመጣ ነበር። ይህም የሆነው በሂራ ዋሻ ውስጥ ድንገት እውነቱ በእርሱ ላይ እስኪወርድለት ድረስ ነበር። በዚያም ሳለ መልአኩ መጣለት እንዲያነብ ጠየቀው። ነቢዩም 'እንዴት እንደሚነበብ አላውቅም' ብሎ መለሰለት። ነቢዩም ይህን ተናገረ፡- መልአኩ ከአቅሜ በላይ በሆነ መልኩ በኃይል ተጭኖ ያዘኝ። ከዚያም ለቀቀኝና እንደገና መልሶ እንዳነብ ጠየቀኝ። እኔም 'እንዴት እንደሚነበብ አላውቅም' ብዬ መለስኩለት። አሁንም እንደገና ከአቅሜ በላይ በሆነ መልኩ ለሁለተኛ ጊዜ በኃይል ተጭኖ ያዘኝ። ከዚያም ለቀቀኝና እንዳነብ በድጋሚ ጠየቀኝ። ነገር ግን እኔም በድጋሚ 'እንዴት እንደሚነበብ አላውቅም' ብዬ መለስኩለት። ለሦስተኛ ጊዜ በኃይል ተጭኖ ያዘኝ። ከዚያም ለቀቀኝና ፍጥረቱን ሁሉ ባስገኘው፣ ሰውንም ከረጋ ደም በፈጠረው በጌታህ ስም አንብብ አለኝ። አንብብ ጌታህ ቸር ነው አለኝ.....ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ ዋራቃ ስለሞተ መለኮታዊው መገለጥም ለትንሽ ጊዜ መውረዱን አቁሞ ነበር። እናም ነቢዩ በጣም አዝኖ እንደነበርና ብዙ ጊዜ ራሱንም ከተራራው ጫፍ ላይ ሊወረውር አቅዶ እንደነበር ሰማን። ራሱን ቁልቁል ለመወርወር ብሎ በየጊዜው ወደ ተራራው ጫፍ ይወጣ ነበር። ጂብሪልም ከፊቱ እየታየው 'አ መሐመድ ሆይ! አንተኮ በእውነት የአላህ ሐዋርያ ነህ' ይለው ነበር። መሐመድም ልቡ ፀጥ ሲልና ሲረጋጋ ወደቤቱ ይመለሳል። የመለኮታዊው መገለጥ ለረጅም ጊዜ ሳይመጣ ሲቆይ እንደበፊቱ ያደርጋል። ነገር ግን የተራራው ጫፍ ላይ በደረሰ ሰዓት ጂብሪል ከፊቱ ይሆንና ከአሁን በፊት የተናገረውን ደግሞ ይነግረዋል።"

Bukhari Volume 9, Book 87, Number 111: Narrated 'Aisha: "The commencement of the Divine Inspiration to Allah's Apostle was in the form of good righteous (true) dreams in his sleep. He never had a dream but that it came true like bright day light. He used to go in seclusion (the cave of) Hira where he used to worship (Allah Alone) continuously for many (days) nights. He used to take with him the journey food for that (stay) and then come back to (his wife) Khadija to take his food like-wise again for another period to stay, till suddenly the Truth descended upon him while he was in the cave of Hira. The angel came to him in it and asked him to read. The Prophet replied, "I do not know how to read." (The Prophet added), "The angel caught me (forcefully) and pressed me so hard that I could not bear it anymore. He then released me and again asked me to read, and I replied, "I do not know how to read," whereupon he caught me again and pressed me a second time till I could

not bear it anymore. He then released me and asked me again to read, but again I replied, "I do not know how to read (or, what shall I read?)." Thereupon he caught me for the third time and pressed me and then released me and said, "Read: In the Name of your Lord, Who has created (all that exists). Has created man from a clot. Read and Your Lord is Most Generous...that which he knew not." (96.15)

.....(Parts before omitted because it was too long)....

But after a few days Waraqa died and the Divine Inspiration was also paused for a while and the Prophet became so sad as we have heard that he intended several times to throw himself from the tops of high mountains and every time he went up the top of a mountain in order to throw himself down, Gabriel would appear before him and say, "O Muhammad! You are indeed Allah's Apostle in truth" whereupon his heart would become quiet and he would calm down and would return home. And whenever the period of the coming of the inspiration used to become long, he would do as before, but when he used to reach the top of a mountain, Gabriel would appear before him and say to him what he had said before. (Ibn 'Abbas said regarding the meaning of: 'He it is that Cleaves the daybreak (from the darkness)' (Quran 6:96) that Al-Asbah. means the light of the sun during the day and the light of the moon at night).

እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህን የመሐመድን ጂብሪል እውነተኛ ማንነት ለማወቅ በጣም ቀላል ነው፡፡ አሁን ወደ ቁርአኑ እንሂድና የዚህ የመሐመድን ጂብሪል እውነተኛ ማንነት የበለጠ ግልጽ እናድርገው፡፡ ከሙስሊሞቹ ነቢይ ከመሐመድ መነሳት በፊት በመካ ይመለኩ ከነበሩና በኋላም እሳቸው ካጠፏቸው በርካታ ጣዖታት ውስጥ በዋናነት ሦስቱ የአላህ ልጆች ተደርገው ይመለኩ የነበሩት ጣዖታት ይገኙበታል፡፡ ስማቸውም በቁርአኑ ሱረቱ አል-ነጅም 53፡19 ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ አል-ላትን፣ አል-ዑዛንና መናት ስለተባሉት ስለእነዚህ የአላህ ልጆች መሐመድ ሲያስተምሩ እንዲህ ነው ያሉት፡- “አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን አያችሁን? የምትገዟቸው ኃይል አላቸውን?...” እያሉ ሲያስተምሯቸው እነርሱም የጣዖቶቻቸውን ስም ስለጠሩላቸው በደስታ ይሰሟቸው ነበር፡፡ ስለ ጣዖቶቻቸውም ጥሩና መልካም ነገሮችን መናገር ቢጀምሩም አንዳንድ የሚቃወሟቸው ሰዎችም አልጠፉም፡፡ ለምሳሌ አል-ዋሊድ ቢ. አል-ሙግሂራ የተባለው ሽማግሌ ሰው ቆሻሻ በእጆቹ ሙሉ ዘግኖ አምጥቶ በመሐመድ ፊት ላይ ደፍቶባቸዋል፡፡ ያን ጊዜ ሁሉም ሰዎች ተበታተኑ፡፡ ቁራይሾቹም ወጥተው ሄዱ፡፡ ከዚያም ጂብሪል ወደ ነቢዩ መጣና “ምንድነው ያደረከው መሐመድ? አላህ ያላዘዘህንና እኔም ከአላህ ዘንድ ላንተ ያላመጣሁልህን ነገር ለሰዎቹ ተናግረሀል” አላቸው፡፡ ነቢያቸውም በዚህ በጣም ጥልቅ ሀዘን ተሰማቸው፡፡ የአላህንም ቁጣና ቅጣት በእጅጉ ፈሩ፡፡ ስለዚህም አላህ ለእሳቸው መሐሪ ስለሆነ መገለጦችን እንደገና አወረደላቸውና ከሀዘናቸው አፅናናቸው፡፡ ሰይጣን በሀሳባቸው መሀል ጣልቃ ገብቶ በአንደበታቸው አናግሮ እንዳሳሳታቸውና ይህም በአላህ መሀሪነት እንደሚሻር ከእሳቸው በፊት መልእክተኛና ነቢያት እንዳልተላኩ ነገራቸው፡፡ ስለዚህ ሰይጣን እንዲሳሳቱ አድርጎ ያቀረበላቸውን ሀሳብና ያናገራቸውን ነገር የሚሽር ጥቅስ አወረደላቸው፡፡ (Ibn Ishaq:166) እንዲሁም ይህ ታሪክ በተመሳሳይ ሁኔታና አገላለጽ በአል-ታባሪ መጽሐፍ ላይም ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ Al-Tabari, Vol. 6, pp. 107-112

ኢብን ኢሻቅና አል-ታባሪ የመሐመድን የግል የሕይወት ታሪክ በስፋትና በጥልቀት ከጻፉት ውስጥ እኔ ለማሳያ ያህል ብቻ ቀንጭቤ ነው ያቀረብኩት፡፡ ይህ ከላይ ያየነውን ነገር ማለትም በመሐመድ ሀሳቦችና ትምህርቶች ውስጥ የሰይጣን ጣልቃ ገብነት እንደነበር እነርሱ (ኢሻቅና ታባሪ) የጻፉትን ቁርአኑ ሲያረጋግጠው እናያለን፡፡ ቀጥሎ ቁርአኑን የሚነናገረውን ላስቀምጠውና ሱረቱ አል-ሐጅ 22፡52 ምን እንደሚል እንመልከት፡- *“ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም፣ ባነበበና ዝም ባለ ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ ማጥመሚያን ቃል የሚጥል ቢሆን እንጂ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፤ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል፤ አላህም አዋቂና ጥበበኛ ነው፡፡”* ይላል ቁርአኑ፡፡ ሰይጣን በመሐመድ ልብ ውስጥ ማጥመሚያ ቃልን በመጣል ብቻ አላበቃም ይልቁንም አብረውት እንዲሰግዱም አድርጓቸዋል፡፡ መሐመድ የአል-ነጂምን ሱራ በቃላቸው ከተረኩ በኋላ ከመስሊሞች፣ ከፓጋን አረቦችና ከጂኒዎች ማለትም ከሰይጣኖች ጋር ሆነው በከፍተኛ ድካም መሬት ላይ ተዘርረው እንደነበር በሐዲሱ ላይ ተዘግቧል፡፡ "The Prophet performed a prostration when he finished reciting Surat-an-Najm, and all the Muslims and pagans and Jinns and human beings prostrated along with him." Sahih Bukhari 6:60:385

ከሰይጣን ጋር አብሮ መስገድ! ለመሆኑ ይህ ምን ማለት ነው? ለመሐመድ የመጡላቸው መገለጦች ከሰይጣን ተፅዕኖ የተላቀቁ ነበሩ ብሎ ማሰብ ፈጽሞ አይቻልም፡፡ ይህም የሚረጋገጠው ራሳቸው መሐመድም ሆኑ ቁርአኑ ስለ ሰይጣናዊ መገለጦች የሰጡት ማረጋገጫ ነው፡፡ በመሰረቱ የመሐመድ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው በራሱ ከሰይጣን ጋር የተቆራኘ ለመሆኑ ብዙ ምስክሮች አሉ፡፡ ሌላው ቢቀር አብሯቸው እንኳ ይሰግድ ነበር፡፡ ስለዚህ ማጠቃለያችን ሊሆን የሚችለው መሐመድ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በጂብሪል እየተመሰለ ብዙጊዜ ይገለጥላቸው የነበረው ራሱ ሰይጣን ነበር፡፡ በተለይም በሂራ ተራራ ዋሻ ውስጥ ለብቻቸው ወስዶ ልባቸውን ቀዶ ውስጣቸውን

በዘምዘም ውኃ እንዳጠበላቸውና ጥበብን እንደሰጣቸው ራሳቸው መሐመድ ናቸው በአንደበታቸው የተናገሩት፡፡ የእስልምናውንና የመሐመድን የግል ሕይወት ታሪካቸውን የጻፉት ቀደምት ጸሐፊያንም ይህንን ያረጋግጣሉ፡፡ መልአክ በእንደዛ ዓይነት ሁኔታ ሊገለጽ ፈጽሞ አይችልም፡፡ ለዚያውም ለድንግል ማርያም ከሦስቱ ቅዱስ አንዱን ቅዱስ ተወልጃለሽ ብሎ ካበሰረ ከ600 ዓመት በኋላ ገብርኤል የነበረውን ስሙን ቀይሮ ጂብሪል ሆኖ ውሸተኛም ሆኖና ቃሉን ቀይሮ ‹አላህ አይወልድም አይወለድም› ብሎ ሊያስተምር አይችልም፡፡ የመሐመድ ጂብሪል ማለት ዓለሙን ሁሉ ያሳተው እርሱ ዲያብሎስ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎ ሲነግረን «ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና» (2ኛ ቆሮ 2፡14) እንዳለ ብርሃናዊውን መልአክ ቅዱስ ገብርኤልን ተመስሎ ለመሐመድ የተገለጠላቸው እርሱ ነፍሰ ገዳዩ ሰይጣን ነው፡፡ ጌታችንም አስቀድሞ «ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና» (ዮሐ 8፡44) ብሎ እንደነገረን ሐሰትን ለመሐመድ አስተምሮ ዓለሙን ያሳተው ሰይጣን ነው፡፡ የራሳቸው ቁርአን «ስለ ኃጢአትህ ምሕረትን ለምን» (47፡19፣ 40፡55፣48፡2) በማለት የመሰከረባቸውን መሐመድን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ «ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና» (1ኛ ዮሐ 3፡8) በማለት ደምድሞታል፡፡ በውጤቱም እሳቸውም ሆኑ ተከታዮቻቸው ፍጻሜያአቸው ምን እንደሆነ ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ ያየውን እንዲህ ብሎ ነግሮናል፡- «ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሠቃያሉ።» ራእ 20፡10፡፡

ከመጀመሪያዎቹ የእስልምናን ታሪክ ጸሐፊዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት በርካቶች ናቸው፡፡ ‹ሲራት ራሱል-አላህ፣ አል-ዋቂዲ፣ ኢብን ሳድ፣ አል-ታባሪና፣ ሚሽካት አል-ማሳቢህና› ሌሎችም ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ መሐመድ በሰይጣን ተይዘው እንደነበር ጽፈዋል፡፡ በእነዚህ ጥንታዊ መጽሐፎች ውስጥ የተጻፉትንም ነገሮች ራሳቸው ቁርአኑና ሐዲሱ ሲያረጋግጡት ይገኛሉ፡፡ በወቅቱ ከሂራ ተራራ አስጨናቂ መገለጥ በኋላ መሐመድ ወደቤታቸው ሲመለሱ ያያቸው ሰው ግማሹ «አብዷል» ሲላቸው ግማሹ ደግሞ «በሰይጣን ተይዟል» እያሉ ይጠቋቆሙባቸው ነበር፡፡ ከታሪክ ጸሐፊያኑም በላይ ቁርአኑና ሐዲሱ የሚመሰክሩት መሐመድ በሰይጣን ተፅዕኖ ስር የነበሩ መሆኑን ነው፡፡ እንደሐዲሱ ዘገባ «መገለጦች» ለመሐመድ ድንገት ይከሰቱበት የነበረበት ሁኔታም ነበር፡፡ ሰዎች መሐመድን ለማየትና ለመጠየቅ ወደ እሳቸው በመጡ ሰዓት ምን እንደተፈጠረ ሐዲሱ አንድ የዘገበው አስገራሚ ታሪክ አለ፡፡ ታሪኩ በራሱ ብዙ የሚያነጋግር ነው፡፡ አንድ ሰው የኡምራ ጉዞ ሊያደርግ አስቦ ከዚያ በፊት ምን ማድረግ እንዳለበት ለመጠየቅ ወደ መሐመድ በመጣ ሰዓት ድንገት መገለጡ በመሐመድ ላይ ይመጣል፡፡ ይህን ጊዜ አብሮ የነበረው ኡማር መሐመድን በጨርቅ ይሸፍናቸዋል፡፡ ኡመርም ለእንግዳው ሰው መገለጦቹ ለመሐመድ እየመጡላቸው መሆኑን ይነግረዋል፡፡ መሐመድም በጨርቅ ተጠቅልለው እንደተኙ እያጓሩና እያሸካኩ ሲጮሁ እንግዳውም ሰው አይቷቸዋል፣ ሰምቷቸዋል፡፡ እያጓሩ ሳለ ድምጻቸውን መጀመሪያ ሲሰማው የግመል ድምጽ ነው ብሎ ገምቶ ነበር፡፡ ይህንን የመሐመድ ድርጊት አላህ ከአሳቸው ጋር የተገናኘበት መንገድ እንደሆነ ነው እንግዳው ሰው የተረዳው፡፡ ኡመርም የነገረው ይህንኑ ነው፡፡ መሐመድም መንፈሱ ለቋቸው ወደ ማንነታቸው ከተመለሱና ተሸፍነውበት የነበረውን ጨርቅ ከገለፀት በኋላ «ስለ ኡምራ የጠየቀኝ ሰው የታለ?» በማለት ጥያቄውን መልሰውለታል፡፡

“A person came to the Apostle of Allah as he was at Ji'rana and he (the person) had been putting on a cloak which was perfumed, he (the narrator) said: There was a trace of yellowness on it. He said (to the Holy Prophet): What do you command me to do during my Umra? (It was at this juncture) that the revelation came to the Apostle of Allah and he was covered with a cloth, and Ya'la said: Would that I see revelation coming to the Apostle of Allah. He (Hadrat 'Umar) said: Would it please you to see the Apostle of Allah receiving the revelations 'Umar lifted a corner of the cloth and I looked at him and he was emitting a sound of snorting. He (the narrator) said: I thought it was the sound of a camel. When he was relieved of this he said: Where is he who asked about Umra? When the person came, the Holy Prophet said: Wash out the trace of yellowness, he said: the trace of perfume and put off the cloak and do in your 'Umra what you do in your Hajj.” (Sahih Muslim Book 007, Number 2654)

That was how Allah talked to Muhammad--through the ‘bleating’ of a camel!

ይህ ከላይ ያየነውን የመሐመድን ክስተት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት አንዳንድ ባዕድ አምልኮ ከሚፈጽሙ ጠንቋዮች ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በጨርቅ ተጠቅልሎና ተሸፋፍኖ ማጓራት ወይም ማሸካካት የጠንቋዮች አሠራር ነው፡፡ እርግጥ ነው ይህ ዓይነቱ አሠራር በነ አዳል ሞቴና በነ ጠቋር ዘንድ ብቻ ያለ አሠራር ነው፡፡ ከኢጋንንት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ጠንቋዮች በዚህ ዓይነት መንገድ ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ተነጋግረው ሲጨርሱ ነው ወደ ባለጉዳዩ ተመልሰው «ጉዳይህ የሚፈታልህ በዚህ መንገድ ነው...» እያሉ ነው የሚናገሩት፡፡ ይህም መሐመድ ማጓራታቸውንና ማሸካካታቸውን ከጨረሱ በኋላ ወደ ማንነታቸው ከተመለሱና ተሸፍነውበት የነበረውን ጨርቅ ከገለፀ በኋላ «ስለ ኡምራ የጠየቀኝ ሰው የታለ?» ብለው ጥያቄውን ከመለሰላት ጋር በጣም ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይህ የመሐመድ በሰይጣን ተፅዕኖ ስር መውደቅ ከሌሎች በእሳቸው ሕይወት ዙሪያ ካሉ እውነታዎች ጋር ተደምሮ ማለትም ያደረጓቸው ድርጊቶች፣ የተናገሯቸው ነገሮች፣ ያስተማሯቸው ትምህርቶች እነዚህ ሁሉ በሰይጣን ተፅዕኖ ስር ከመውደቃቸው ጋር ሲደመሩ በትክክል አንድ ነገር አጠቃለን እንድንናገር ያስገድዱናል። መሐመድን ሰይጣን ተዋሕዶአቸዋል። ይህንንም ራሳቸው መሐመድ አረጋግጠውልናል።

«ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን ይዋሐደዋል» አሉ ነቢያቸው ሲያስትምሩ። እንደ መሐመድ አስተምህሮት ከሆነ ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን በሁለት ጣቶቹ ሁለቱንም ጎኖቹን ይዳስሳቸዋል። በዚህም ከሕጻኑ ጋር ውሕደትና ቁርኝት ይፈጥራል። ሲወለድ ሰይጣን የማይነካውና የማይቆራኘው የአዳም ዘር ስለሌለ ማንኛውም ሕጻን ሲወለድ የዚህ ችግር ተጠቂ ነው። ሕጻናትም ልክ ከእናታቸው ማኅፀን ሲወጡ የሚያለቅሱት ሰይጣኑ በሁለት ጣቶቹ ጎኖቻቸውን ስለዳሰሳቸው ነው። “Allah’s Apostle said, ‘There is none born among the off-spring of Adam, but Satan touches it. A child therefore, cries loudly at the time of birth because of the touch of Satan.” Sahih Bukhari Book 55 No. 641

በሌላ ቦታ እንተጻፈው መሐመድ ሲያስተምሩ ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እያደረጉ እያለ “በአላህ ስም! አ አላህ ሆይ! ከሰይጣን ጠብቀን፣ የምትሰጠንንም ልጅ ሰይጣን እንዳይደርስበት አንተ ጠብቅልን” በማለት ጸሎት ካደረጉ ሰይጣን በልጃቸው ላይ እንደማይደርስባቸው ለአማኞቻቸው አስተምረዋል። ባልና ሚስት በግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው ወቅት ይህቺን ጸሎት ካልጸለዩ ግን በዚያች ቅፅበት የሚፀነሰውን ልጃቸውን ሰይጣን ይቆራኘውና አብሮት ያድጋል። እንዲሁም ባልና ሚስት በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ወደ ሀፍረተ ሥጋቸው የሚያዩ ከሆነ በዚያው ቅፅበት የሚፀነሰው ልጅ ዐይነ ስውር ይሆናል። The Prophet said, "If anyone of you, when having sexual relation with his wife, say: 'In the name of Allah. O Allah! Protect us from Satan and prevent Satan from approaching our offspring you are going to give us,' and if he begets a child (as a result of that relation) Satan will not harm it." Sahih Bukhari 4:54:493. መሐመድ ስለ ሰይጣን ያላቸው አመለካከትና ይህ ትምህርታቸው ከምን የመጣ እንደሆነ ግልጽ ነው። በራሳቸው ላይ ሰይጣን ካሳደረባቸው ተፅዕኖና ካለባቸው መንፈስ ተነስተው ነው ይህንን ሊያስተምሩ የቻሉት። ራሳቸውን ሰይጣን እንደተዋሐዳቸው እርግጠኛ ባይሆኑ ኖሮ ሁሉም ሰው ገና ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ሰይጣን ይዋሐደዋል ብለው ለማስተማር ባልደፈሩ ነበር። ባደረባቸው መንፈስ በእጅጉ ስለተጨነቁና በሰይጣን እንደተያዙ ስላወቁ ራሳቸውን ለመግደል ወደ ተራራ ጫፍ ወጥተው ሳለ ጂብሪል ነው የአላህ ነቢይ እንደሚሆኑ ነግሯቸው ራሳቸውን ከማጥፋት የተረፉት። Narrated 'Aisha: “The Prophet became so sad as we have heard that he intended several times to throw himself from the tops of high mountains and every time he went up the top of a mountain in order to throw himself down, Gabriel would appear before him and say, ‘O Muhammad! You are indeed Allah's Apostle in truth.’” Bukhari Volume 9, Book 87, Number 111:

“አሁን ከአላህ ፍጥረታት ሁሉ በሰይጣን እንደተለከፈ ገጣሚ ወይንም ራሱን የሚስት ሰው ዓይነት ለእኔ የሚያስጠላኝ ምንም ነገር የለም፤ እኔ ወደ እነርሱ እንኳን ለመመልከት አልችልም። ያሰብኩትም እኔ ገጣሚው ወይንም የተለከፍኩት ወዮልኝ ብዬ ነው፤ ኩራይሽ የሆነ ይህን ስለ እኔ በፍጹም አይናገርም። ስለዚህም እኔ ወደ ተራራ ጫፍ ላይ እወጣለሁ ራሴንም ወደ ታች ወርውሬ እገድልና አርፋለሁ።” “Now none of Allah’s creatures was more hateful to me than an (ecstatic) poet or a man possessed: I could not even look at them. I thought, Woe is me poet or possessedNever shall Quraysh say this of me! I will go to the top of the mountain and throw myself down that I may kill myself and gain rest.” (Ibid, p.106)

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሐዲሱ ላይ አንድ የተጠቀሰ ነገር አለ። “መገለጥ ወደ አላህ መልእክተኛ ላይ በሚመጣበት ጊዜ ምንም እንኳን ቀኑ ቀዝቃዛ ቢሆንም ግንባሩ ያልበዋል” በማለት አይሻ እንደዘገበችው መሐመድ ብቻቸውን ሆነው ወደ ሂራ ተራራ በመሄድ መገለጦቹ መጡልኝ በሚሉበት ሰዓት ምንም እንኳን የአየር ሁኔታው በጣም ቀዝቃዛ ቢሆንም ወደቤታቸው በሚመለሱ ጊዜ በላብ ተዘፍቀው ነበር። በላብ መዘፈቅ ብቻ አይደለም የፊታቸው ከለርም ይለወጥ ነበር።

“Allah’s Apostle sweated in cold weather when revelation descended upon him. Aisha reported: When revelation descended upon Allah’s Messenger even during the cold days, his forehead perspired. Ubada bin Samit reported that when wahi (inspiration) descended upon Allah’s Messenger, he felt a burden on that account and the colour of his face underwent a change.” (Sahih Muslim, Abdul Hamid Siddiqi, tr., Number 5763. & Ibid, Number 5764.)

መሐመድ በእንደዚህ ዓይነት በጣም በአስጨናቂ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ሳለ በከፍተኛ ጭንቀትና ውጥረት ይሰቃዩ ስለነበር ሰውነታቸውንም ብርድ ብርድ ይላቸው ነበር። እናም ወደቤት ሲመለሱ ሕጻኗ ሚስታቸው አይሻን በብርድልብስ እንድትሸፍናቸው ይነግሯት ነበር። «መሐመድ አለ፡- ‹የመለኮት መገለጡ ለጥቂት ጊዜያት ዘግይቶ ነበር ነገር ግን በድንገት እኔ እየተራመድሁ እያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁኝ እኔም ወደ ሰማይ ስመለከት ያስደንቃል በሂራ ዋሻ ውስጥ እያለሁ ወደ እኔ የመጣውን መልአክ አየሁት እሱም በሰማይና በምድር መካከል በወንበር ላይ ተቀምጦ ነበር። እኔም በእሱ በጣም ፈርቼ ነበር ስለዚህም በምድር ላይ ወደቅሁና ወደ

ቤተሰቤ ተመልሼ እንዲህ አልኳቸው ሸፍኑኝ፤ ሸፍኑኝ (በብርድ ልብስ)፤ ሸፍኑኝ› አልኳቸው::» Muhammad said: "The Divine Inspiration was delayed for a short period but suddenly, as I was walking, I heard a voice in the sky, and when I looked up towards the sky, to my surprise, I saw the angel who had come to me in the Hirra Cave, and he was sitting on a chair in between the sky and the earth. I was so frightened by him that I fell on the ground and came to my family and said (to them), Cover me! (with a blanket), cover me!" (Sahih Al-Bukhari, Number 3238.)

ሌላው ማየት ያብን ነገር መሐመድ የደወል ድምፅ ማለት የሰይጣን ድምጽ እንደሆነ ለተከታዮቻቸው ማስተማራቸውን ይህም በሐዲሱ ላይ በስፋት የተጠቀሰ መሆኑን ነው:: መሐመድ የደወልን ድምፅ ጥላቻው ከምን የመጣ እንሆነ ራሱ ሐዲሱ መልስ ይሰጠናል:: መሐመድ በዚያ በሂራ ተራራ ዋሻ ውስጥ በከፍተኛ ጭንቀትና ውጥረት ውስጥ ሆነው ሳለ ይሰሙት የነበረው ድምፅ የደወል ድምፅ ነበር:: ያንን ድምጽ ነው መሐመድ የሰይጣን ድምጽ ነው ያሉው:: በጣም ይረብሻው እንደነበር በዚህም እንደጠሉት ሲናገሩ እንዲህ ነው ያሉት:- "አይሻ እንደዘገበችው ሃሪዝ ቢን ሂሻም የአላህን ሐዋርያ እንዴት ነው መገለጥ (ዋሂ) ወደ አንተ የሚመጣው? በማለት ጠየቀው:: እርሱም አንዳንድ ጊዜ ወደ እኔ የሚመጣው እንደሚያቃጭል ቃጭል ደወል ነው፤ ያ ለእኔ በጣም መጥፎው ነገር ነው:: በሚያቆምበትም ጊዜ በመገለጥ ወይም በዋሂ መልክ የተቀበልኩትን ነገር አስታውሰዋለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መልአክ ወደ እኔ በሰው መልክ ይመጣልና ይናገራል፤ በዚያን ጊዜም የተናገረውን ሁሉ አስታውሰዋለሁ::" A'isha reported that Harith bin Hisham asked Allah's Apostle: How does the wahi (inspiration) come to you? He said: At times it comes to me like the ringing of a bell and that is most severe for me and when it is over I retain that (what I had received in the form of wahi), and at times an Angel in the form of a human being comes to me (and speaks) and I retain whatever he speaks. (Sahih Muslim, Abdul Hamid Siddiqi, tr., Number 5765. & Ibid, Number 5765.)

<u>የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ መተት ተደረጎባቸው እንደነበር ለምን ሊታሰብ ቻለ???</u>:- የመሐመድ በሰይጣን የመያዛቸው ጉዳይ በወቅቱ አጠገባቸው ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ለሚስቶቻቸውም ጭምር ግራ ያጋባ ነገር ነበር:: ሚስቶቻቸው "ምናልባት መተት ተደርጎበት ይሆን እንዴ?" ብለው እስከሚያስቡ ድረስ ተጨንቀው ነበር:: ይህንን በተመለከተ አይሻ እንዲህ ነው ያለቸው:- "አንድ ጊዜ ነቢዩ መተት ተደርጎበት ነበር፤ ስለዚህም በእውነት ያላደረገውን ነገር እንዳደረገው አድርጎ መገመትንና ማሰብን ጀምሮ ነበር" Aisha narrated: "Once the Prophet was bewitched so that he began to imagine that he had done a thing which in fact, he had not done." (Sahih Al-Bukhari, Number 3175.)

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በአንድ አይሁዳዊ ሰው መተት ተደርጎባቸው እንደነበር በሐዲሱ ላይ ሌላም የተዘገበ ታሪክ አለ:: "ነቢዩ በአይሁዳዊ ሰው መተት ተደርጎበታል፤ ለብዙ ጊዜ የሚያደርገውንም ነገር አያውቅም ነበር" ተብሎ ነው የተጻፈው:: The Prophet had been bewitched by a Jew, and for several days he did not know what he was doing. (Bukhari, 59/11; 76/47; Hanbal 6/57; 4/367)

"በአላህ መልእክተኛ ላይ አስማት ተሰርቶ ነበር፤ ስለዚህም እርሱ ግብረ ስጋ ግንኙነትን ከሚስቶቹ ጋር ሳያደርግ እንዳደረገ አድርጎ ያስብ ነበር:: ከዚያም አንድ ቀን እርሱ እንዲህ አለ:- 'አ አይሻ አላህ ስለጠየቅሁት ነገር ምን እንዳዘዘኝ ታውቂያለሽን? ሁለት ሰዎች ወደ እኔ መጡ አንደኛው በራሴ አጠገብ ሌላው ደግሞ በእግሬ አጠገብ ተቀመጡ:: በእራሴ አጠገብ የተቀመጠው በእግሬ ስር ለተቀመጠው 'ይህንን ሰው ምን ነካው?' በማለት ጠየቀው:: ሁለተኛውም 'እርሱኮ በመተት ቁጥጥር ውስጥ ነው ያለው' አለው:: የመጀመሪያውም ሰው 'በእሱ ላይ መተትን የሰራው ማን ነው?' አለ:: ሁለተኛውም መልሶ 'ከባኒ ዙራይቅ ወገን የሆነው ሰው ላቢድ ቢን አል-አሳም ነው፤ እርሱም የአይሁዶች አጋዥና ተመፃዳቂ የሆነ ግብዝ ሰው ነው' በማለት መለሰ:: የመጀመሪያውም ሰው 'እርሱ ይህን ለማድረግ የተጠቀመው ምንድን ነው?' ብሎ ጠየቀ:: ሁለተኛውም 'ማበጠሪያና በውስጡ ፀጉር የተጣበቀበት ነው' በማለት መለሰ'" (Ibid, Number 5765.) "Aisha narrated: Magic was worked on Allah's Apostle so that he used to think that he had had sexual relations with his wives while he actually had not. Then one day he said, "O Aisha, do you know that Allah has instructed me concerning the matter I asked Him about? Two men came to me and one of them sat near my head and the other sat near my feet. The one near my head asked the other: 'What is wrong with this man?' The latter replied, 'He is under the effect of magic.' The first one asked, 'Who has worked magic on him?' The other replied, 'Labid bin Al-Asam, a man from Bani Zuraiq who was an ally of the Jews and was a hypocrite.' The first one asked, 'What material did he use?' The other replied, 'A comb and the hair stuck to it.'" (Ibid, Number 5765.)

ኢብን ኢሻቅም ይህንኑ ሁኔታ በገጽ 240 ላይ አስፍሮታል:: ይህም ላቢድ ቢን አሳም በአላህ ሐዋርያ ላይ አስማት (መተት) እንዳደረገባቸውና በዚህም ምክንያት መሐመድ ከአይሻ በቀር ወደ ሌሎች ሚስቶቻቸው መሄድ እንዳልቻሉ ነው ኢብን ኢሻቅ

የዘገበው፡፡ (Ibn Ishaq sirat rasul Allah, p. 240)

ስለዚህ እስካሁን በዝረዝር እንዳየነው መሐመድን ሰይጣን ከተዋሐዳቸው በቁርአኑም ላይ ማጥመሚያ ቃልን አሳርፎ ከነበረ ነገር ግን አላህ ማጥመሚያውን ቃል ካስወገደላቸው /ሱረቱ አል-ሐጅ 22፡52/ እንዲሁም መሐመድ የአል-ነጂምን ሱራ በቃላቸው ከተረኩ በኋላ ከተከታዮቻቸው ሙስሊም አረቦችና ከጂኒዎች ማለትም ከሰይጣኖች ጋር ሆኖ በከፍተኛ ድካም መሬት ላይ ተዘርረው ከሰይጣን ጋር አብረው ከሰገዱ /ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡385/ ከዚህ በኋላ ከመሐመድ ምንድነው የምንጠብቀው? ስለዚህ እርግጠኞች ሆነን መናገር የምንችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ያም ለመሐመድ ሃይማኖቱን የሰጣቸው ሰይጣን ነው፡፡ በመሠረቱ መሐመድ እምነታቸውን ምክንያት አድርገው ያደረጓቸው ነገሮች ሁሉ ሃይማኖታቸውን ከሰይጣን ለመሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ መሐመድ ካሉበት ጊዜ ጀምሮ በእርሳቸው ጅሃዳዊ ትእዛዞች ምክንያት እስከዛሬ ድረስ በዓለም ላይ ከ270 ሚሊዮን በላይ ንጹሓን ዜጎች ለሞት ተዳርገዋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታዎችንና በቁርአን ውስጥ ስላሉት የግድያ አንቀፆቻቸው የራሱ የሆነ ሰፊ ርዕስ ስላለው ያን ጊዜ በደንብ እናየዋለን፡፡

የመሐመድ በሰይጣን መያዝ ከሕፃንናተቸው ጀምሮ የመጣ ነገር ነው፡፡ መሐመደ ወላጅ እናታቸው ከመሞቷ በፊት የምትንከባከባቸው ሞግዚት ነበረች፡፡ ይህችም ሞግዚት በመሐመድ የልጅነት ጊዜ ስለተከሰቱት እንግዳና ያልተለመዱ ነገሮች የሚከተሉትን ትናገራለች፡- “መሐመድና ወንድሙ (አብረው ጡት እየጠቡ ስላደጉ ነው ወንድም የተባለው) ከድንኳኑ ጀርባ ከበግ ግልገሎቻችን ጋር ነበሩ፤ ወንድሙ ሮጦ ወደእኛ መጣና እንዲህ አለ፡- ‘ሁለት ሰዎች ነጭ ልብስን ለብሰው ኩራይሺውን ወንድሜን ያዙትና ጣሉት፡፡ ከዚያም ሆዱን ከፈቱና አማሰሉት’ እኛም ወደእርሱ ሮጠን ሄድን፤ መሐመድንም ቆሞ ፊቱም ተለዋውጦ ከሰል መስሎ አገኘነው፡፡ ይዘነውም ‘ምንድነው ነገሩ?’ ብለን ጠየቅነው፡፡ እርሱም ‘ሁለት ነጭ ልብስን የለበሱ ሰዎች መጥተው ጣሉኝና ሆዴን ከፍተው ውስጤን በረበሩት፣ ምን እንደሆነ አላውቅም’ አለን፡፡ ወደ ድንኳናችን መልሰን ወሰድነው፡፡ አሳዳጊ አባቱ ‘እኔ የምፈራው ይህ ልጅ የልብ ድካም አለበት ብዬ ነው፤ ስለዚህም ውጤቱ ከመታየቱ በፊት ወደ ቤተሰቡ ውሰጅው’ አለኝ፡፡ ስለዚህም አንስተን ወደ እናቱ ወሰድነው፤ እሷም እኔ እንደዚያ የእሱን ደኅንነት እየጓጓሁኝና ከእኔ ጋርም ልጠብቀው እየፈለግሁ እያለሁ ለምን እንደመለስነው ጠየቀችን፡፡ እኔም ‘አላህ እስካሁን ልጄን በጤንነት ጠብቆታል እኔም የሚገባኝን ተግባሬን እስካሁን ተወጥቻለሁ፡፡ ያመው እንደሆን ብዬ ስለፈራሁ እንደምትፈልጊው ወደ አንቺ እንደገና አምጥቼዋለሁ’ አልኳት፡፡ እርሷም ምን እንደሆነ እስከነግራት ድረስ እረፍት አላጥታ ጠየቀችኝ፡፡ እናቱም ሰይጣን ይዞታል ብዬ እፈራ እንደሆነ በጠየቀችኝ ጊዜ ‘አዎን ሰይጣን ይዞታል’ ብዬ መለስኩላት፡፡” Muhammad and his brother were with our lambs behind the tents when his brother came running and said to us, "Two men clothed in white have seized that Qurayshi brother of mine and thrown him down and opened up his belly, and are stirring it up." We ran towards him and found him standing up with a livid face. We took hold of him and asked him what was the matter. He said, "Two men in white raiment came and threw me down and opened up my belly and searched therein for I know not what." So we took him back to our tent. His father said to me, "I am afraid that this child has had a stroke, so take him back to his family before the result appears." So we picked him up and took him to his mother who asked why we had brought him when I had been anxious for his welfare and desirous of keeping him with me. I said to her, "Allah has let my son live so far and I have done my duty. I am afraid that ill will befall him, so I have brought him back to you as you wished." She asked me what happened and gave me no peace until I told her. When she asked if I feared a demon possessed him, I replied that I did." Ibn Ishaq, *Sirat Rasul Allah* (*The Life of Muhammad*), A. Guillaume, tr. (New York: Oxford University Press, 1955), p. 71-72. መሐመድ በሰይጣን መያዛቸው ያስፈራት የነበረችው ሞግዚታቸው ብቻ አልነበረችም፡፡ ራሳቸው መሐመድም ጂብሪል ተገለጠልኝ ያሉት ነገር በሲራት ራሱል አላህ ላይ እንዲህ ተጽፎ ይገኛል፡- “አላህ በራሱ ተልእኮ ባከበረውና ለባርያው ምህረትን ባሳየበት ምሽት በሆነ ጊዜ ጂብሪል ወደ እርሱ የአላህን ትዕዛዝ አመጣለት፡ ‘ወደ እኔ መጣ’ አለ የአላህ ሐዋርያ፡፡ ‘እኔ አንድ ጽሑፍ ያለበት የአልጋ ልብስ የመሰለ ጨርቅ ለብሼ ተኝቼ በነበረበት ጊዜ ‘አንብብ!’ አለኝ፡፡ እኔም ‘ምን ላንብብ?’ አልኩት፡፡ እርሱ በዚያው ነገር በጣም አጥብቆ ስለተጫነኝ እኔ ሞት ነው ብዬ አሰቤ ነበር፡፡ ከዚያም ለቀቀኝና ‘አንብብ!’ አለኝ፤ እኔም ‘ምን ላንብብ?’ አልኩት፡፡ እንደገና በዚያው ነገር በጣም አጥብቆ ሲጫነኝ እኔ ሞት ነው ብዬ አሰቤ ነበር፡፡ እንደገና ለቀቀኝና ‘አንብብ’ አለኝ፤ እኔም ‘ምን ላንብብ?’ አልኩት፡፡ እርሱም በዚያው ነገር ለሦስተኛ ጊዜ ተጫነኝ፤ እኔም ሞት ነው ብዬ አሰቤ ነበር፡፡ እርሱም ‘አንብብ’ አለኝ፤ እኔም ‘ታዲያ ምንድነው የማነበው?’ አልኩት፡፡ ይህንንም የተናገርኩት ራሴን ከእጁ ለማስመለጥና ይህንንም እንደገና እንዳያደርግብኝ ብዬ ነበር፡፡ እርሱም ‘በፈጠረህ በጌታህ ስም አንብብ፤ ከረጋ ደም ሰውን በፈጠረው አንብብ! ጌታህ በጣም ቸርና ርኅሩኅ ነው፤ በብዕር ባስተማረው፣ ለሰዎች ያልታወቀውን ያስተማረው’ አለኝ፡፡ ስለዚህም አነበብኩት፣ እርሱም ከእኔ ተለየኝ፡፡ ከእንቅልፌም ነቃሁ፣ እነዚያም ቃላቶች ልክ በልቤ ላይ እንደተጻፉ ሆነው ነበር፡፡”

When it was the night on which Allah honored him with his mission and showed mercy on His servants thereby, Gabriel brought him the command of Allah. "He came to me," said the apostle of Allah, "while I was asleep, with a

coverlet of brocade whereon was some writing, and said, 'Read!' I said, 'What shall I read?' He pressed me with it so tightly that I thought it was death; then he let me go and said, 'Read!' I said, 'What shall I read?' He pressed me with it again so that I thought it was death; then he let me go and said 'Read!' I said, 'What shall I read?' He pressed me with it the third time so that I thought it was death and said 'Read!' I said, 'What then shall I read?'and this I said only to deliver myself from him, lest he should do the same to me again. He said: 'Read in the name of thy Lord who created, Who created man of blood coagulated. Read! Thy Lord is the most beneficent, Who taught by the pen,Taught that which they knew not unto men.' So I read it, and he departed from me. And I awoke from my sleep, and it was as though these words were written on my heart." (Ibn Ishaq, Sirat Rasul Allah (The Life of Muhammad), A. Guillaume, tr. (New York: Oxford University Press, 1955), p.106.) (በነገራችን ላይ የኢብን ኢሻቅ "Sirat Rasul Allah" መጽሐፍ ከሁሉም ኢስላማዊ ጽሑፎች ውስጥ እጅግ ጥንታዊው ሲሆን የተጻፈውም በ750 ዓ.ም ነው። ይህ መጽሐፍ በጥንታዊነቱ የመጀመሪያ ስለሆነ ቁርአኑንም ሆነ ሁሉንም ሐዲሶች ይቀድማል። የመሐመድ ተከታይ በሆኑት ከሊፋዎች አማካኝነት ቁርአኑ ከየቦታው ተሰብስቦ በአንድ ጥራዝ መልክ የተዘጋጀው መሐመድ በ632 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ቢያንስ 200 ዓመትና ከዚያ በላይ ቆይቶ ነው።)

ከዚህ በኋላም ስለነበረው ሁኔታ በዚሁ የኢብን ኢሻቅ "Sirat Rasul Allah" መጽሐፍ ላይ የተጻፈውን ቀጥሎ እንመለከት፡- "አሁን ሐዋርያው ስለሕዝቦቹ ደኅንነት ይጨነቅ ነበር። እነርሱንም ለመሳብ እስከሚችለው ድረስ እየተመኘ ነው... የራሱ ሕዝቦች ጀርባቸውን እንዳዞሩበት ባየ ጊዜ እንዲሁም እርሱ አመጣሁ ከሚለው መልእክት መለያየት በገጠመው ጊዜ ነገሩ ህመም ሆነበት። ሕዝቦቹንም ከአላህ ጋር የሚያስታርቅለት መልእክት መጥቶለት ከሕዝቡ ጋር መስማማትን ተመኘ። ለሕዝቦቹ ካለው ፍቅር የተነሳ ለዚህ ሥራው እንቅፋት የሆነበት ነገር ቢወገድለት በእጅጉ ይደሰት ነበር። ከዚያም አላህ "በኮከብ በሚጠልቅበት ጊዜ ያንተ ጓድ ሳይተላለፍና ሳይታለልና ከእራሱ ምኞት ሳይናገር" የሚልን መልእክት ላከ። እናም መሐመድ በሚያስታርቅበት ጊዜና ወደ ሕዝቡም ለመምጣት በሚመኝበት ጊዜ 'ስለ አል-አላት እና አል-ኡዛ እና ስለ ሦስተኛዋ ማናትና ስለሌሎች አሰባችሁን' የሚለው ቃል ላይ ሲደርስ ሰይጣን በምላሱ ላይ 'እነዚህ የተከበሩ ናቸው ጋራኒቅ (ኑሚድያን ክሬንስ) ምልጃቸው ተቀባይነት ያገኙ ናቸው' የሚልን ቃል አስቀመጠ። ቁራይሾች ይህንን በሰሙ ጊዜ እጅግ በጣም ደስ አላቸው፤ ስለ አማልክቶቻቸውም የተናገረበት መንገድ አስደሰታቸውና ይሰሙት ጀመር። አማኞቹ ይዘውት የነበረው የእነርሱ ነቢይ ከጌታ ዘንድ ያመጣው እውነት ነው በማለት አምነው ነበር ምንም ስህተት እንዳለበትም አልጠረጠሩም፣ ከንቱ የሆነ መሳት እንዳለበት ምንም አልጠረጠሩም ነበር። እርሱም ለመስገድ በደረሰ ጊዜ ወይንም በሱራው መጨረሻ ላይ በደረሰ ጊዜ እርሱ በሚሰግድበት ጊዜ ሙስሊሞችም እራሳቸው ሰገዱ፤ ነቢያቸው ሲሰግድና ያመጣውን ሲያረጋግጥና ለትዕዛዙ ሲታዘዝ ብዙ ጣዖታት አምላኪዎች ከኩራይሽ የሆኑት እና ሌሎችም በመስጊድ ውስጥ የነበሩት የአማልክቶቻቸውን ስም መጠራት ሲሰሙ ሰገዱ። ስለዚህም በመስጊድ ውስጥ የነበረው እያንዳንዱ አማኙም የማያምነውም ሁሉም ሰገደ...ከዚያም ሕዝቡ ተበተነ፤ ቁራይሾችም ስለ አማልክቶቻቸው በተነገረው ነገር እየተደሰቱ ሄዱ፤ 'መሐመድ ስለ አማልክቶቻችን ድንቅ በሆነ መንገድ ተናገረ እያሉ ነበር የሄዱት።

ዜናው የነቢዩ ጓደኞች እስካሉበት እስከ አቢሲኒያ ድረስ ደረሰ፤ የተነገረውም ኮራይሾች እስልምናን ተቀበሉ የሚል ዜና ነበር። ከዚህም ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ከስደት መመለስ ሲጀምሩ ሌሎች ግን ወደ ኋላ ቀሩ። ከዚያም ጂብሪል ወደ ሐዋርያው መጥቶ 'ምንድነው ያደረግኸው መሐመድ? ለእነዚህ ሰዎች እኔ ከአላህ ዘንድ ወደ አንተ ያላመጣሁትን ነገር ነው ያነበብክላቸው፤ እርሱም ያላለህን ነገር ነው የተናገርከው' አለው። ሐዋርያውም መሪር የሆነ ሀዘን አዝኖ አላህን በጣም ፈርቶ ነበር። ስለዚህም አላህ መገለጥን ላከ፤ እርሱ ለመሐመድ መሐሪ ነውና ከሀዘኑ አፅናናው፤ ለእርሱ ምቾት ሲባል ነገሩንም አቀለለውና ከእርሱ በፊት የነበረ ሐዋርያና ነቢይም ሁሉ የሚፈልገውን እንደፈለገ የሚመኘውንም እንደተመኘ ነገረው እናም ሰይጣን እርሱ በተመኘው ነገር ላይ ገና በምላሱ ላይ እንዳለ አቋርጦት አንድን ነገር እንደጨመረበት ነው። ስለዚህም አላህ ሰይጣን ያቀረበለትን ሐሳብ ሰርዞ የራሱን ጥቅስ መስርቷል ማለትም አንተ ልክ እንደ ሐዋርያትና ነቢያት ነህ ብሎ በመናገር ነው። ከዚያም አላህ እንዲህ የሚል ጥቅስ አወረደለት፡- 'ከአንተ በፊት ሐዋርያትንም ነቢያትንም አልላክንም ነገር ግን አንድን ነገር ሲመኝ ሰይጣን በተመኘው ነገር ውስጥ የራሱን ሐሳብ ይሰጣል። ነገር ግን ሰይጣን የሰጠውን ሐሳብ አላህ ይሽረዋል። ከዚያም አላህ የራሱን ጥቅስ ያፀናል፣ አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው'" (Ibn Ishaq sirat rasul allah, 165-166.) እዚሁ ላይ እንዳለን ሰይጣን ለመሐመድ የሰጣቸውን ሀሳብና አላህም ያንን የሻረላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተከታዩን የቁርአን ጥቅስ ማስታወሱ በቂ ነው፡- "ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም፣ ባነበበና ዝም ባለ ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ ማጥመሚያን ቃል የሚጥል ቢሆን እንጂ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፤ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል፤ አላህም አዋቂና ጥበበኛ ነው።" ሱረቱ አል-ሐጅ 22፡52

"Now the apostle was anxious for the welfare of his people, wishing to attract them as far as he could. ...When the apostle saw that his people turned their backs on him and he was pained by their estrangement from what he brought them from Allah he longed that there should come to him from Allah a message that would reconcile his

people to him. Because of his love for his people and his anxiety over them it would delight him if the obstacle that made his task so difficult could be removed. Then Allah sent down "By the star when it sets your comrade errs not and is not deceived, he speaks not from his own desire," and when he reached His words "Have you thought of al-Lat and al-Uzza and Manat the third, the other", Satan, when he was meditating upon it, and desiring to bring it to his people, put upon his tongue "these are the exalted Gharaniq [Numidian cranes] whose intercession is approved." When the Quraysh heard that, they were delighted and greatly pleased at the way in which he spoke of their gods and they listened to him; while the believers were holding that what their prophet brought them from their Lord was true, not suspecting a mistake or a vain desire or a slip, and when he reached the prostration and the end of the Sura in which he prostrated himself the Muslims prostrated themselves when their prophet prostrated confirming what he brought and obeying his command, and the polytheists of Quraysh and others who were in the mosque prostrated when they heard the mention of their gods, so that everyone in the mosque believer and unbeliever prostrated . . . Then the people dispersed and the Quraysh went out, delighted at what had been said about their gods, saying, "Muhammad has spoken of our gods in splendid fashion."

The news reached the prophet's companions who were in Abyssinia, it being reported that Quraysh had accepted Islam, so some men started to return while others remained behind. Then Gabriel came to the apostle and said, "What have you done, Muhammad? You have read to these people something I did not bring you from Allah and you have said what He did not say to you." The apostle was bitterly grieved and was greatly in fear of Allah. So Allah sent down (a revelation), for He was merciful to him, comforting him and making light of the affair and telling him that every prophet and apostle before him desired as he desired and wanted what he wanted and Satan interjected something into his desires as he had on his tongue. So Allah annulled what Satan had suggested and Allah established His verses, i.e. you are just like the prophets and apostles. Then Allah sent down: "We have not sent a prophet or apostle before you but when he longed Satan cast suggestions in his longing. But Allah will annul what Satan has suggested. Then Allah will establish his verses, Allah being knowing and wise." (Ibn Ishaq sirat rasul allah, 165-166.)

በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ ከላይ ባየነው የኢብን ኢሻቅ ሲራት ራሱል-አላህ ቀደምት ጽሑፍ ላይም ይሁን በቁርአኑና በሐዲሱ ላይ ካየነው ነጥብ በመነሳት እንደማጠቃለያ ሊሆኑ የሚችሉ የተወሰኑ አንኳር ነጥቦችን ማንሳት እንችላለን፡፡ ይህም፡-

1ኛ. ነቢያቸው መሐመድ መገለጦችን ተቀበልኩ ያሉት ነገር የራሳቸውን የግል ምኞትና ፍላጎታቸውን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

2ኛ. መሐመድ በእርግጥም መገለጥን ከሰይጣን ተቀብለዋል፡፡

3ኛ. ከሰይጣን የተቀበሉትን መገለጥ ከአላህ የመጣ ነው በማለት አስተምረዋል፡፡

4ኛ.እርሳቸውና ተከታዮቻቸው ከሰይጣን ለተቀበሉት ሀሳብ ወይም ለመገለጡ መምጣት ክብር ሲሉ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሰግደዋል፤ በዚህም መሐመድ ስሕተት እንደሠሩ ቁርአኑ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ለዚህም እንደመፍትሄ የተወሰደው ለስሕተታቸው የተሰጠው የአላህ የማስተካከያ ምላሽ ነው፡፡ ይህም አላህም በመሐመድ ልብ ውስጥ የሰረፀውን የሰይጣንን ማጥመሚያ ቃል አስወግዷል ቢባልም ምንም ዓይነት መረጃና ፍንጭ የሚሰጠን ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን በመሐመድ ልብ ውስጥ ያሰረፃቸው ማጥመሚያ ቃላት ምን ነበሩ? አላህስ ያስወገዳቸው የትኞቹን ነው? የሚሉት ጥያቄዎች መላሽ አልባ ናቸው፡፡

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ለዓለም ያበረከቷቸው አስተዋፅአዎች፡- **ሰዎች መሐመድ ከሰይጣን ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንደነበራቸው ብሎም እንደተዋሐዳቸው እስካሁን አይተናል፡፡ እስቲ አሁን ደግሞ የመሐመድን ፍሬዎች እንይ፡፡ መሐመድ ለዓለም ያበረከቱት ነገር ምንድነው? ምንስ ዓይነት ሰው ነበሩ? ቀጣዮቹ ርዕሶች ለእነዚህና ተያያዥ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡**

መሐመድ «ነቢይ ነኝ» ብለው እስከተነሡበት ጊዜ ድረስ ለ40 ዓመታት ጣዖት አምላኪ ነበሩ፡- “Some people believe that in the beginning he (the Prophet) was a Kaffir. Then Allah (swt) guided him and made him a Prophet. Qalbee says: This verse “And He found thee wandering” means that that he was kafir among

misguided people. Then Allah (swt) guided him to the path of Tauheed. Al-Sudi states that he (the Prophet) followed the faith of his Kaffir people for forty years". *(Tafsir al Kabir by Fakhruddin al Razi, Volume 8 page 424)* "For forty years, He was on the faith of his people". (Sahih al-Sirah al-Nabawyiah by Dr.Muhammad Rezq al-Tarhuni, volume 2 page 41)

መሐመድ የሰዎችን አካል በመቆራረጥ ያሰቃይ ነበር /Torturer/:- ይህንን ለማረጋገጥ ቀጥሎ ያለውን የቁርአን ጥቅስ ማስታወሱ ብቻ በቂ ነው። "እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚዋጉ፣ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከሀገር መባረር ነው" ይላል ቁርአኑ። ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡33። "The punishment of those who wage war against Allah and His messenger and strive to make mischief in the land is only this, that they should be murdered or crucified or their hands and their feet should be cut off on opposite sides or they should be imprisoned; this shall be as a disgrace for them in this world, and in the hereafter they shall have a grievous chastisement" Qur'an 5:33

ወደ ሐዲሱም ስንመጣ መሐመድ የፈጸሙትን አንድ አስገራሚ ታሪክ እናገኛለን። በታሪኩ ላይ አካልን በመቆራረጥ አሰቃይቶ ስለመግደል የሚናገረውን የቁርአን ጥቅስ መሐመድ እንዴት በተግባር እንዳዋሉት እናያለን። ሙሉ ታሪኩ በሦስቱም ዋና ዋና ሐዲሶች (ቡኻሪ፣ አቡ ዳውድና ሳሂህ ሙስሊም) እንዲሁም በመሐመድ የግል የሕይወት ታሪካቸው /biography/ ላይም በዝርዝር ተቀምጧል። ዑራይና ከሚባል ጎሳ የመጡ 8 ሰዎች የመሐመድን እምነት ይቀበሉና አብረዋቸው መጓዝ ይጀምራሉ። ከዚያ በኋላ ግን ደስተኞች አልነበሩም፤ አጠቃላይ ሁኔታውም ሆነ የአካባቢው አየር ስላልተስማማቸው ታመሙና መድኃኒት ወይም ወተት እንዲሰጧቸው ነቢያቸውን ይጠይቃሉ። ነቢያቸው መሐመድም ወደ በረሃው ወርደው የግመልን ወተትና ሽንት ለመድኃኒትነት እንዲጠቀሙበት ነው የነገሯቸው። እነርሱም ግመሎቹን ይዘው በዛው ይጠፋሉ። ጠፍተው አልቀሩም ተይዘው መሐመድ ፊት ቀረቡ። መሐመድም ዐይናቸውን ቢጋለ ብረት አውጥተው፣ እጅና እግራቸውን ቆራርጠው ነው የገደሏቸው። "The Prophet sent some men in their pursuit, and before the sun rose high, they were brought, and he had their hands and feet cut off. Then he ordered for nails which were heated and passed over their eyes, and whey were left in the Harra (i.e. rocky land in Medina). They asked for water, and nobody provided them with water till they died" (Sahih Bukhari 4:52:261), "The Prophet then ordered to cut their hands and feet (and it was done), and their eyes were branded with heated pieces of iron, They were put in 'Al-Harra' and when they asked for water, no water was given to them." (Sahih Bukhari 1:4:234), "The Prophet ordered for some iron pieces to be made red hot and their eyes were branded with them and their hands and feet were cut off and were not cauterized. Then they were put at a place called Al-Harra, and when they asked for water to drink they were not given till they died." (Sahih Bukhari 8:82:796)

ነቢያቸው መሐመድ "አሰቃዩትና እውነቱን ይናገር" የሚል ትእዛዝ ኪናናህ በተባለው ሰው ላይ አስተላልፈውበት ሰውየውን ደረቱን በእሳት አቃጥለው ካሰቃዩት በኋላ መሐመድ ለሌላኛው ተከታያቸው «አንገቱን ሰይፈው» ብለው አሰይፈውታል። "The Prophet gave orders concerning Kinanah to Zubayr, saying, 'Torture him until you root out and extract what he has.' So Zubayr kindled a fire on Kinanah's chest, twirling it with his firestick until Kinanah was near death. Then the Messenger gave him to Maslamah, who beheaded him." Al-Tabari, Vol. 8, p. 122, See Also Ishaq:515. እንዲሁም ሌሎች በርካታ ተመሳሳይ ታሪኮችን ተጽፈው እናገኛለን። "Following Badr, Muhammad sent a number of raiders with orders to capture some of the Meccans and burn them alive."(Ishaq:316), "The Apostle said, 'Get him away from me and cut off his tongue.'" (Ishaq:595) የአንዷን ሴት ታሪክ ግን ከሁሉም በተለየ ሁኔታ ሰፋ ባለ መልኩ ማየቱ ግድ ነው። ዑም ቂርፋህ ትባላለች። ፋዛራ ከተባሉ የፓጋን ዐረብ ጎሳዎች ወገን የሆነች በዕድሜ የገፋች ትልቅ ሴት ናት። የጎሳዋን መሪ እነ መሐመድ ቀደም ብለው ወረራ ባደረጉ ጊዜ ገድለውታል። ዛይድ በጦርነቱ ቆስሎ ስለነበር በንዴት ብዙ ሴቶችና ሕጻናትን ጭምር ገድሎ የተቀሩትን በምርኮ ሲወስድ ይህቺን ትልቅ አሮጊት ሴት ቃይስ አል-ሙሳህር ለተባለው ሰው ግደላት ብሎ ይሰጠዋል። እርሱም ሴት ልጇን ለዝሙት ባርነት በምርኮ ከወሰደ በኋላ ዑም ቂርፋህ እጅግ አሰቀቂ በሆነ ሁኔታ ገደላት። Ibn Ishaq: 980። በገመድ ሁለት እግሮቿን ሁለት የተለያዩ ግመሎች ላይ አስሮ ግመሎቹን ሰዎች ጋልበዋቸው በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ እንዲሄዱ በማድረግ ሰውነቷ ተበጣጥሶ

እንድትሞት ነው ያደረጓት:: Sahih Muslim 19:4345

“A raiding party led by Zayd set out against Umm in Ramadan. During it, Umm suffered a cruel death. Zyad tied her legs with rope and then tied her between two camels until they split her in two. She was a very old woman. Then they brought Umm’s daughter and Abdallah to the Messenger. Umm’s daughter belonged to Salamah who had captured her. Muhammad asked Salamah for her, and Salamah gave her to him.” Al-Tabari, Vol. 8, p. 96. “Then they brought Umm Qirfa’s daughter and Mas’ada’s son to the apostle. The daughter of Umm Qirfah belonged to Salama b. Amr who had taken her.” Ibn Ishaq 980. “An expedition led Zaid bin Haritha was despatched to Wadi Al-Qura in Ramadan 6 Hijri after Fazara had made an attempt at the Prophet’s life. Following the Morning Prayer, the detachment was given orders to raid the enemy. Some of them were killed and others captured. Amongst the captives, were Umm Qirfah and her beautiful daughter” (Saifur Rahman al-Mubarakpuri- the Sealed Nectar: Page 152)

ነቢያቸው መሐመድ በማሰቃየት የመቅጣትንና የመግደልን አዋጅ ያስተላለፉት በእስልምና በማያምኑት ወይም በክርስቲያኖች ላይ ብቻ አልነበረም:: ሶላት ለመስገድ ከቤት ወጥተው ወደ መስጊድ የማይሄዱም ሙስሊሞች እዛው እቤታቸው ውስጥ እንዳሉ እሳት እንዲለኮስባቸው አዘው ነበር:: “The Prophet said, ‘No prayer is harder for the hypocrites than the Fajr and the 'Isha' prayers and if they knew the reward for these prayers at their respective times, they would certainly present themselves (in the mosques) even if they had to crawl." The Prophet added, "Certainly I decided to order the Mu'adh-dhin (call-maker) to pronounce Iqama and order a man to lead the prayer and then take a fire flame to burn all those who had not left their houses so far for the prayer along with their houses.’” Sahih Bukhari 1:11:626

መሐመድ ጅምላ ጭፍጨፋ ያካሄዱ ነበር /Mass Murderer/:- በመጀመሪያ ካሁን በፊት በጥቂቱ የጠቀስነውን አንድ ታሪክ አንስተን ማየት እንችላለን:: ቁጥራቸው ከ800-900 የሚሆኑ በመዲና ከተማ ይኖሩ የነበሩ የባኑ ቁራይዛ ጎሳዎች በ627 ዓ.ም በመሐመድ ትእዛዝ በአንድ ቀን በሰይፍ ተሰይፈዋል:: ቁርአኑ በሱረቱ አል-አሕዛብ 33:26 ላይ «እነዚያንም ከመጽሐፉ ባለቤቶች የረዱዋቸውን ቁረይዛን ከምሽጎቻቸው አወረዳቸው፤ በልቦቻቸውም ውስጥ መባባትን ጣለባቸው፤ ከፊሉን ትገድላላችሁ፤ ከፊሉንም ትማርካላችሁ» በማለት ይጠቅሳቸዋል:: በሐዲሱ ላይ በግልጽ እንደተመዘገበው መሐመድ መጀመሪያ ላይ በጣም ትልቅና ረጅም የምሽግ ጉድጓድ እንዲቆፈር አደረጉ:: ከዚህ በኋላ ከታሰሩበት በግሩፕ በግሩፕ እየተከፈሉ ተወስደው በየተራ አንገታቸው እየተሰየፈ ወደተቆፈረው ጉድጓድ እንዲጣሉ ሲደረግ መሐመድ ይህን ክስተት ቁጭ ብሎ ሲከታተሉት ነው የዋሉት:: በመጨረሻም ሚስቶቻቸውንና ሕጻናቱን ለራሳቸውና ለተከታዮቻቸው ለዝሙትና ለባርነት ተግባር አከፋፍሏቸዋል:: “The Prophet offered the Fajr Prayer [Prayer of Fear] near Khaybar when it was still dark. He said, ‘Allahu-Akbar!’ [Allah is Greatest] Khaybar is destroyed, for whenever we approach a hostile nation to fight, then evil will be the morning for those who have been warned.’ Then the inhabitants came out running on their roads. The Prophet had their men killed; their children and woman were taken as captives.” Sahih Bukhari: 5:59:512. “Then the Messenger of Allah sent Sa’d bin Zayd with some of the Qurayza captives to Najd, and in exchange for them he purchased horses and arms.” “The Messenger of God commanded that furrows should be dug in the ground for the Qurayza. Then he sat down. Ali and Zubayr began cutting off their heads in his presence.” Al-Tabari, Vol. 8, pp. 39-40

ነቢያቸው መሐመድ ሰዎች ለጠየቋቸው ጥያቄ መልሱን ከሰማይ አወርድላችኋለሁ ብለው ከነገሯቸው በኋላ የተናገሩትን ነገር በሰዎቹ ፊት በተግባር ማሳየት ባለመቻላቸው በዚህም ብዙዎች እንደካዱ በቁርአኑ 5፡102 ላይ ተጠቅሷል፡፡ በተመሳሳይ አገላለጽ ኢብን ኢሻቅም ይህንን በሰፊው ዘግቦታል፡፡ Ibn Ishaq:248፡፡ በቁርአኑ 8፡18 ላይም እንዲሁ ተአምር አደርጋለሁ ካሉ በኋላ ባለማድረጋቸው የተጠራጠሩትን ሰዎች መሐመድ ተንኮለኞችና ከሀዲዎች ናቸው ብለዋቸዋል፡፡ 8፡71 ላይ ደግሞ “ሊከዱህ ቢፈልጉ ከዚህ በፊት አላህን በእርግጥ ከድተዋል” በማለት ለወደፊቱ ተከታዮቻቸው ቢከዷቸው እንኳ መካዳቸው አዲስ እንዳልሆነ በመንገር ራሳቸውን አፅናንተውታል፡፡ በሐዲሱም ውስጥ ብዙ ቦታዎች ላይ “The Prophet said, ‘War is deceit.’” ማለትም “ጦርነት ማታለል ነው” ብሎ እንደተናገረ ተጠቅሷል፡፡ Sahih Bukhari 4:52:267 , Sahih Bukhari 4:52:268 , Al-Tabari, Vol. 8, p. 23 & Sahih Bukhari 4:52:269. አፈ ጮሌነት ልክ እንደ ማጂክ ዓይነት ሥራ እንደሆነ ነው በሐዲሱ ላይ የተነገረው፡፡ Sahih Bukhari 7:71:662. ማታለል ለመሐመድ ብቻ እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ነቢይ እንዳልተፈቀደ መናገራቸውን ኢብን ኢሻቅ ጽፎታል፡፡ “Then Allah said, ‘It is not for any prophet to deceive.’” Ishaq: 397

27.መሐመድ ራሳቸውን ያስመልኩ ነበር /Megalomaniac/፡- መሐመድ ሲያስተምሩ «ከእናንተ ውስጥ እኔን ከአባቱ፣ ከልጅቹና ከሁሉም የሰው ዘር ሁሉ አብልጦ ያልወደደኝ ቢኖር እርሱ እምነት አይኖረውም» በማለት እርሳቸውን ከማንም በላይ ካልወደዱ እምነት እንደማይኖራቸው ማለትም እንደማይድኑ ነው የተናገሩት፡፡ Narrated Anas: The Prophet said ‘None of you will have faith till he loves me more than his father, his children and all mankind." Sahih Bukhari 1:2:14

መሐመድ ጽዳት የሌላቸው ሰው ነበሩ /unclean/፡- ከዚህ ጋር የተያያዙ ተሰምተው የማይታወቁ አንዳንድ ነገሮችን ቀጥሎ በዝርዝር እናያለን፡፡ ቀጥዬ የምጠቅሳቸውም ነገሮች በሐዲሱ ላይ ተጽፈው የሚገኙ ናቸው እንጂ ከራሴ ፈጥሬ አንዳች ነገር አልጻፍኩም፡፡
መሐመድ በራስ ፀጉራቸው ውስጥ ያለውን ቅማል ሚስታቸው ትቀምልላቸው ነበር /Lice on Mohammed’s head/፡- በጣም በሚያሳዝን መልኩ ዘይነብ የተባለችው ሚስታቸው ከመሐመድ ራስ ላይ ቅማሎችን ትቀምል እንደነበር በአቡ ዳውድ ሐዲስ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ “Narrated Zaynab: She was picking lice from the head of the Apostle of Allah while the wife of

Uthman ibn Affan and the immigrant women were with him. They complained about their houses that they had been narrowed down to them and they were evicted from them." Abu Dawud 19:3074

መሐመድም ሆኑ ተከታዮቻቸው መጥፎ የሰውነት ጠረን ነበራቸው /Bad bodily odor/፡- መሐመድና ተከታዮቻቸው መጥፎ የሰውነት ጠረን ነበራቸው፡፡ አንዱ የመሐመድ ተከታይ ልጁን ሲመክረው እንዲህ ነው ያለው፡- «ልጄ ከአላህ ሐዋርያ ጋር ሆነን በእኛም ላይ ዝናብ ዘንቦ ስታየን ጠረናችን የበግ ጠረን እንደሆነ ማሰብ አለብህ» ብሎታል፡፡ "Abu Burdah said: My father said to me: 'My son, if you had seen us while we were with the Apostle of Allah and the rain had fallen on us, you would have thought that our smell was the smell of the sheep.'" Abu Dawud 32:4022. ይህ አባት ለምን ልጁን እንዲህ ሊለው እንደቻለ ለመገመት ያን ያህል አስቸጋሪ አይመስለኝም፡፡ እኔ ሳስበው አባትየው ከመሐመድ ጋር ለውጊያ ወጥቶ ሲመለስ የሰውነቱን ጠረን በተመለከተ ልጁ ለአባቱ ሲናገር የተሰጠው መልስ ይመስለኛል፡፡ ለማንኛውም አባትየው በምንም ምክንያት ይናገረው በዋናነት ማንሳት የፈለኩት ጉዳይ አባትየው «ከመሐመድ ጋር ሆነን ዝናብ ሲዘንብብን በግ በግ እንሸታለን» እያለ የተናገረውን ነገር ነው፡፡ ካሁን በፊት አታስታውሱም መሐመድና ተከታዮቻቸው እንዲሁም እረዳቱ ነው ያሉት መልአኩ ጂብሪልም ጭምር በጂሃድ ሲሳተፉ ሰውነታችን በአቧራ ተሸፍኖ ነበር እያሉ መሐመድ መናገራቸውን? መሐመድ ከጂሃድ ጦርነት ሲመለሱ የጦር መሳሪያቸውን አስቀምጠው ሰውነታቸውን ሊታጠቡ ሲሉ «አብሮኝ የተዋጋው ጂብሪል ሰውነቱ በአቧራ ተሸፍኖ ወደ ቤት ገባና ጦርነቱኮ ገና አላለቀም ለምን መሳሪያህን አስቀመጥክ? ብሎኝ ተመልሼ ለጦርነት ወጣሁ...» እያሉ መሐመድ መናገራቸውን አስታወሳችሁ? መሐመድ ሲያስተምሩም ቢሆን «በአላህ መንገድ ሲዋጋ እግሮቹ በአቧራ እስኪሸፈኑ ድረስ የተጋደለ ጂሃዲስት ነው ጀነት የሚገባው» ብለው ማስተማራቸውንስ «ጂሃድ» በሚለው ርዕስ ላይ የተነጋገርነውን አስታወሳችሁ? ስለዚህ አሁን እዚህ ጋር ይህ አባት ለልጁ ሲናገር «ከመሐመድ ጋር ሆነን ዝናብ ሲዘንብብን በግ በግ እንሸታለን» ማለቱ ከእነዚህ የመሐመድ ድርጊቶችና ትምህርቶች ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ በዚያ ላይ የመሐመድ ሚስታቸው ዘይነብ ቅማላቸውን ከራስ ፀጉራቸው ላይ ስትቀምል ነበር መባሉን ከዚሁ ጋር አያይዙት፡፡ ጤና አጠባበቅና መሐመድ እንዴት ናቸው አያስብልም? እኔ ግን ከዚህም በላይ ሊነገር የሚችል በጣም ብዙ ነገር አለ እላለሁ፡፡ ቀጥሎ ያሉትን አስገራሚ ነገሮችንም እንያቸው፡-

መሐመድ እጅግ አስገራሚ የምግብ ጤና አጠባበቅ አስተምህሮ ነበራቸው፡- ብዙዎቹ የመሐመድ አስተምህሮዎች በተለይ ከጤና ጋር በተያያዘ ያስተማሯቸው ትምህርቶች በአግራሞት እጅን በአፍ የሚያስጭኑ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሙስሊሞች ምግብ ከበሉ በኋላ በውሃ ከመታጠባቸው በፊት ጣታቸውን መላስ ወይም ለሌላ ሰው ማስላስ እንዳለባቸው ትእዛዝ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ይህም በሦስቱም ዋና ዋና ትላልቅ ሐዲሶች ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ "The Prophet said, 'when you eat, do not wipe your hands till you have licked it, or had it licked by somebody else.'" Sahih Bukhari 7:65:366, Sahih Muslim 3:21:5042, Abu Dawud 3:20:3838.
አይጥ በምግብ ቅቤ ውስጥ ብትገባ ምን መደረግ እንዳለበት መሐመድ ተጠይቀው ነበር፡፡ እርሳቸውም ለዚህ የሰጡት መልስ አይጧን ከቅቤው ውስጥ አውጥተው እንዲወረውሯት ነገር ግን የቀረውን ቅቤ ለምግብነት እንዲጠቀሙበት ነው ያስተማሩት፡፡ "Allah's Apostle was asked regarding ghee (cooking butter) in which a mouse had fallen. He said, 'Take out the mouse and throw away the ghee around it and use the rest.'" Sahih Bukhari 1:4:236. መሐመድ በወቅቱ የነበሩት ተከታዮቻቸው አሮጌ ቴምር አመጡላቸውና ውስጡን ሲመረምሩት ትል አገኙበት፡፡ ትል ቢያገኝበትም ትሉን ከውስጡ አውጥተው በመጣል ቴምሩን ለምግብነት መጠቀምን መርጧል፡፡ "Narrated Anas ibn Malik: When the Prophet was brought some old dates, he began to examine them and remove the worms from them." Abu Dawud 27:3823
ነቢያቸው መሐመድ እንደራባቸው ያየ አንድ ተከታያቸው ወደቤቱ ሄዶ ያርድላቸውና ይጋብዛቸዋል፡፡ መሐመድም የተጋበዙበት ቤት ሄደው ምግቡ ሲቀርብላቸው ሥጋው የተቀቀለበት ሸክላ ማሰሮ ውስጥ ምራቃቸውን ይተፉበታል፡፡ ምራቃቸውን ምግቡ ውስጥ ከተፉበት በኋላ ነው አላህ ምግቡን እንዲባርከው የለመኑት፡፡ Narrated Jabir bin 'Abdullah: When the Trench was dug, I saw the Prophet in the state of severe hunger. So I returned to my wife and said, "Have you got anything to eat, for I have seen Allah's Apostle in a state of severe hunger." So I went to him and said to him secretly, "O Allah's Apostle! I have slaughtered a she-animal (i.e. kid) of ours. ....I to my wife, "I have told the Prophet of what you said." *Then she brought out to him. Then he proceeded towards our earthenware meat-pot and spat in it and invoked for Allah's Blessings in it.* Then he said (to my wife). Call a lady-baker to bake along with you and keep on taking out scoops from your earthenware meat-pot, and do not put it down from its fireplace." They were one-thousand (who took their meals), and by Allah they all ate, and when they left the food and went away, our earthenware pot was still bubbling (full of meat) as if it had not decreased, and our dough was still being baked

as if nothing had been taken from it. Sahih Bukhari 5:59:428

መሐመድ ደርቆ የተጣበቀ የዘር ፈሳሽ በልብሳቸው ላይ ይታይ ነበር/Semen on Mohammed's closes/፡- በዘር ፈሳሻቸው ምክንያት የተበላሹ የመሐመድን ልብሶች ታጥብ እንደነበር ሚስታቸው አይሻ ተናግራለች፡፡ እንዲያውም የዘር ፈሳሻቸው ሲደርቅ ከልብቻቸው ላይ በጥፍሯ እየፋቀች ታስለቅቃቸው እንደነበር ነው የተናገረችው፡፡ ልክ እንደ ደህና ነገር ይህን ታሪክ ሐዲሱ በጣም ብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ Narrated 'Aisha: "I used to wash the semen off the clothes of the Prophet and even then I used to notice one or more spots on them." Sahih Bukhari 1:4:233. Narrated Abdullah b. Shihab al-Khaulani: "I stayed in the house of 'A'isha and had a wet dream (and perceived its effect on my garment), so (in the morning) I dipped both (the clothes) in water. This (act of mine) was watched by a maid-servant of A'isha and she informed her. She (Hadrat A'isha) sent me a message: What prompted you to act like this with your clothes? He (the narrator) said: I told that I saw in a dream what a sleeper sees. She said: Did you find (any mark of the fluid) on your clothes? I said: No. She said: Had you found anything you should have washed it. *In case I found that (semen) on the garment of the Messenger of Allah dried up, I scraped it off with my nails."* Sahih Muslim 2:572, See Also Sahih Muslim 2:566 Sahih Muslim 2:567-2:571

መሐመድ የሞቱት በመርዝ ነው፡- ስለ መሐመድ አሟሟት በቁርአኑ ላይ ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በሐዲሱ ላይ በሰፊው ስለተጠቀሰ እርሱን ማየት እንችላለን፡፡ መሐመድ ከሁሉም ሚስቶቻቸው ውስጥ በበለጠና በተለየ ሁኔታ ይወዷት የነበረችው ሚስታቸው አይሻ እንደተናገረችው መሐመድ በጠና በታመሙ ሰዓት ሌሎቹን ሚስቶቻቸውን ትተው በአይሻ ቤት እረፍት ማድረግን ነበር የመረጡትው፡፡ በሁለት ሰዎችም ድጋፍ ነው ወደ አይሻ ቤት የተወሰዱት፡፡ Narrated 'Aisha: "When the Prophet became seriously ill and his disease became aggravated he asked for permission from his wives to be nursed in my house and he was allowed. He came out with the help of two men and his legs were dragging on the ground.'" Sahih Bukhari 1:11:634

ስለ አሟሟታቸው ሁኔታ ሐዲሱ እንደሚናገረው መሐመድ የሞቱት አስገድደው ያገቧት አንዲት አይሁዳዊ ሚስታቸው በመርዝ በከላ በሰጠቻቸው ምግብ ነው፡፡ ይህችን አይሁዳዊ ሴት በምን ዓይነት ሁኔታ እንደገቧት ማስታሱ ተገቢ ነው፡፡ ስሟ ሳፊያ ቢንት ሁያይ ይባላል፡፡ ከአይሁድ ወገን ስትሆን በካይባር ጦርነት ወቅት መሐመድ ባሏንና አባቷን ከገደሉባት በኋላ በጦር ማርከው ያገቧት ሚስታቸው ናት፡፡ በሐዲሱ ላይ እንደተዘገበው ነቢያቸው ኪናን የተባለውን ወጣት ባሏን አሰቃይተው እንዲሞት ካደረጉት በኋላ ነው እርሷን ወዲያው ወደ መኝታቸው ድንኳን ይዘዋት የሄዱት፡፡ ከዚያ ቀደም ብሎ ደግሞ አባቷን ሁያይንና ወንድሟን ከሌሎች አይሁዶች ጋር በሰይፍ እንዲሰየፉ አድርገዋቸዋል፡፡ (*Bukhari* vol.2 book 14 ch.5 no.68 p.35; vol.4 book 52 ch.74 no.143 p.92; vol.4 book 52 ch.168 no.280 p.175 and *al-Tabari* vol.39 p.185.) ስለዚህ ይህቺ ሴት ናት መጨረሻ ላይ ምግባቸውን በመርዝ በከላ የገደለቻቸው፡፡ ተከታዮቻቸውም ይህን እንዳወቁ እርሷን መሐመድ ፊት አቅርበው እንዲገድሏት ቢጠይቁትም ፍቃደኛ አልሆኑላቸውም፡፡ Narrated Anas bin Malik: A Jewess brought a poisoned (cooked) sheep for the Prophet who ate from it. She was brought to the Prophet and he was asked, "Shall we kill her?" He said, "No." I continued to see the effect of the poison on the palate of the mouth of Allah's Apostle. Sahih Bukhari 3:47:786.

በቡኻሪ ሐዲስ ላይ እርሷን እንዳላስገደሏት የተጠቀሰ ቢሆንም በአቡ ዳውድ ሐዲስ ላይና በሌሎቹም መጻሕፍት የተመዘገበው ግን እንዳስገደሏት ነው፡፡ «...*A Jewess presented him at Khaybar with a roasted sheep which she had poisoned. The Apostle of Allah ate of it.* The Prophet sent for the Jewess (and said to her): What motivated you to do the work you have done? She said: *If you were a prophet, it would not harm you; but if you were a king, I should rid the people of you. The Apostle of Allah then ordered regarding her and she was killed.*» Abu Dawud 39:4498 , see also Ibn Sa'd, Vol. 2, p. 249, Ibn Ishaq, p. 516 & Al-Tabari, Vol. 8, pp. 124-125

መሐመድ ኃጢአተኛ እንደነበሩ ቁርአኑ ይናገራል፡- በሚገርም ሁኔታ ነቢያቸው መሐመድ ኃጢአተኛ እንደነበሩ ቁርአኑ ብዙ ቦታ ላይ አውጆባቸዋል፡፡ ተከታዮቹን የቁርአን ጥቅሶች በደንብ ተመልከቷቸው፡- "መሐመድ ሆይ! ታገስም፤ የአላህ ተስፋ እውነት ነውና ለስሕተትህም ምሕረትን ለምን፤ ከቀትር በኋላም በማለዳም ጌታህን በማመስገን አጥራው" (ሱረቱ አል-ሙእሚን 40:55)፣ "ስለ ስሕተትህም፣ ለምእመናንም ምሕረትን ለምን" (ሱረቱ መሐመድ 47:19)፣ "አላህ ከኃጢአትህ

ያለፈውንና የሚመጣውን ላንተ ሊምር፣ ጸጋውንም ባንተ ላይ ሊሞላ፣ ቀጥተኛውንም መንገድ ሊመራህ ከፈተልህ" ሱረቱ አል- ፈትሕ 48፡2።

በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጥቅሶች ላይ በአማርኛው ቁርአን ላይ "... ስለ ስሕተትህም ምሕረትን ለምን" ተብሎ ቢጻፍም የእንግሊዝኛው ቁርአን ግን "ask forgiveness for your sin" በማለት ነው የሚገልጸው። ሦስተኛው ጥቅስ ላይ ግን የአማርኛውም ቁርአን በግልጽ "አላህ ከኃጢአትህ ያለፈውንና የሚመጣውን ላንተ ሊምር..." በማለት አስቀምጦታል። ስሕተት መስራት ማለት ኃጢአት ማለት ነው። ስለዚህ "ስሕተትም" ተባለ "ኃጢአት" በየትኛውም መንገድ ቢገለጽ የአገላለጹ ጉዳይ ችግር የለውም። ከዚህ ይልቅ በአገላለጹ ላይ ችግር ያለበት "ያለፈውንና የሚመጣውን" በምትለዋ አገላለጽ ላይ ነቢያቸው መሐመድ ገና ወደፊት ለሚሠሩት ኃጢአት ሁሉ ሳይቀር ዋስትና ያገኙ መሆኑ ላይ ነው። መሐመድ በእስልምናው እምነት እንደሚሰጣቸው እጅግ ትልቅ ቦታ ኃጢአት ወይም ስሕተት መሥራታቸው በራሱ እጅግ አሳፋሪ ቢሆንም ያለፈውን ኃጢአታቸውን ይቅር መባላቸው አግባብ ነው። ግን ገና ለገና ወደፊት ለሚሠሩት ኃጢአት እንዴት የይቅርታ ዋስትና ሊሰጣቸው ቻለ? ለመሆኑ በሕይወት ዘመናቸው የሠሯቸውና ይቅር የተባሉበት ኃጢአቶታቻቸው ምን ምን ናቸው? ቀድሞ ይቅርታ ያገኙባቸውና የወደፊት ኃጢአቶቻቸውስ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ለሚለው እስካሁን ያየነው በቂ መልስ ነው።

ቁርአኑ ስለ መሐመድ የሚናገረው ስለ ኃጢአተኛነቱ ብቻ አይለም። እስቲ ቀጥሎ ያሉትን ርዕሶች ተመልከቷቸው፡-

በወቅቱ የነበሩ ሰዎች መሐመድን አጭበርባሪ ነው ይሏቸው ነበር፡- የቁርአን ክፍል እንዲሆን መሐመድ ከሰጣቸው ጥቅሶች መካከል አንዱ በሌላ ጥቅስ በተተካበት ጊዜ በወቅቱ የነበሩ ሰዎች የተናገሩት መሐመድ አጭበርባሪ እንደሆኑና ነቢይ ነኝ ብሎ በማጭበርበር የሚጠይቅ እንደነበረ ነው። ቀርአኑን 16፡101 ተመልከት።

በወቅቱ የነበሩ ሰዎች የመሐመድን ትምህርቶች «ጥንት የነበሩና የተለመዱ ተረቶች ናቸው» ይሉት ነበር፡- በወቅቱ የነበሩ ሰዎች መሐመድን ትምህርታቸውን «የጥንት የተመዱ ተረቶች ናቸው» ይሏቸው ነበር። በቁርአን ውስጥም ያሉትን ተረቶች አንድ የሆነ ሰው ጊዜውን ሰጥቶ እነዚህን ነገሮች ለመሐመድን አስተምሮት ነው ብለው ያመናሉ። ቁርአን 16፡24፣ 25፡5፣ 68፡15፣ 83፡13 ተመልከት።

መሐመድ ምንም ተዓምር እንዳላደረገ ቁርአኑ ይናገራል፡- ሙስሊሞች ያልሆኑት ያስተዋሉት ነገር ሙሴ ተዓምራትን ሲያደርግ መሐመድ ግን ምንም ተዓምራትን አላደረጉም። መሐመድም ራሳቸው ምንም ተዓምራቶች እንዳላደረጉ አምነዋል። ቁርአን 28፡48፣ 10፡20፣ 13፡7 እና 6፡37 ተመልከት።

መሐመድ በሰይጣን የተያዙ ስለመሆኑ ቁርአኑም ይናገራል፡- በወቅቱ የነበሩ ሰዎች መሐመድን ትኩር ብለው ሲለከቷቸው እርሱ (መሐመድ) በሰይጣን የተያዘ መሆኑን ይናገሩ ነበር። ቁርአን 68፡51 እና 25፡8 ተመልከት።

መሐመድ ሐሰተኛ ነቢይ መሆናቸውን ፓጋን አረቦቹ ያውቁ ነበር፡- አሁንም በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ስለ መሐመድ ሲናገሩ የቁርአን ጥቅሶችን ራሱ መሐመድ ነው የፈጠራቸው ናቸው ይሉት ነበር። ቁርአን 46፡8፣ 52፡33 እና 25፡4 ይመለከቱ።

በወቅቱ የነበሩት ሰዎች መሐመድ ዕብድ ናቸው ይሏቸው ነበር፡- በወቅቱ የነበሩ ሰዎች መሐመድን እብድ ነው ይሏቸው እንደነበር ቁርአኑ ይናገራል። ቁርአን 68፡2 ላይ ይመልከቱ። እንዲሁም መሐመድ ምንም ተዓምራቶችን ስላላደረጉ ፓጋኖቹ የእነርሱ አማልክቶቻቸው መሐመድን ዕብድ ይሁን ብለው እንደረገሙት ቁርአኑ ይናገራል። ፲፡53-54።

መሐመድ የግል አስተማሪ ነበረው፡- በወቅቱ የነበሩ ሰዎች መሐመድን የሚከሱት አንድ አረብ ያልሆነ ሰው ቁርአንን እንዲቀዱ መሐመድን እንደረዳው (እንዳስተማረው) ነው። ይህ የመሐመድ አስተማሪ ደግሞ ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ተወግዞ የተለየ ቡኻሪያ የተባለ መነኮሴ ነው። ቁርአን 16፡103 ላይ ተመልከት።

መሐመድን ሰዎች "ስብከቶችህ ቀድሞ የምናውቃቸው የዱሮ ተረቶች ናቸው" ይሏቸው ነበር፡- መሐመድ ገና ከመነሻው እስልምናን መስበክ ሲጀምሩ የመካ ሰዎች ትምህርታቸውን "የቀደሙት አባቶቻችን የሚያወሯቸው ተረቶች ብቻ እንጂ ሌላ አይደሉም" በማለት ያፌዙባቸው ነበር። ይህንንም ራሳቸው መሐመድ በቁርአኑ አል-ሙእሚኑን 23፡83 ላይ ጠቅሰውታል። "On the contrary they say things similar to what the ancients said. "Such things have been promised to us and to our fathers before! They are nothing but tales of the ancients!'" Qur'an 23:83። ለዚህም ነው መሐመድ በቁርአን 9፡61 ላይ

“ነቢዩን ጆሮ ሰሚ ነው ይላሉ” ካለ በኋላ ወደ ማስፈራሪያው የሚገባው፡፡ ከቁ.63 ጀምሮ እንዲህ ይላል፡- «አላህንና መልእክተኛውን የሚከራከር ሰው ለእርሱ የገሀነም እሳት በውስጧ ዘውታሪ ሲሆን የተባቺው መሆኑን አያውቁምን? ይህ ታላቅ ውርደት ነው፡፡ መናፍቃን በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ነገር የምትነግራቸው ሱራ በእነርሱ ላይ መወረዷን ይፈራሉ፤ አላገጡ» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ቁርአኑ በ23 ዓመት ውስጥ ለመሐመድ ወረደላቸው በተባለው ጊዜ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ቢታዩ ማለትም መጀመሪያ ወርዷል ከተባለው ከሱራ 96 ጀምረን ብናየው የመጀመሪያዎቹ የግጥም መልክ ሲኖራቸው ቀስ በቀስ ነው ይዘታቸው እየተቀየረ የመጣውና ወደ ጎይልና ግድያ እያመዘኑ የመጡት፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ከመነሻው ሲያስተምራቸው ትምህርቱ ሰዎቹ ከሚያውቋቸው የቀደሙ ተረቶች ያልተለዩ ስለሆኑ አልቀበል ስላሏቸው ነው በቀጥታ ጂሃድን የእምነታቸው ማስፋፊያ ዋነኛ መንገድ ያደረጉት፡፡

መሐመድ በሴት ቀሚስ ውስጥም እያሉ መገለጦቹ ይመጡላቸው ነበር፡- ለመሐመድ አንዳንድ ጊዜ መገለጦቹ ይመጡላቸው የነበረው የአይሻን ቀሚስ በሚለብሱበት ጊዜ ነበር፡፡ ማለትም ከሁሉም ሚስቶቻቸው በበለጠ ሁኔታ አይሻን በጣም ይወዷት ነበር (እርሳቸው በ53 ዓመታቸው አይሻ ደግሞ የ9 ዓመት ሕጻን ልጅ እያለች እንዳገቧትና ወሲብ እንፈጸሙባት ያስታውሱ) የመሐመድ ሁሉም ሚስቶች እርሳቸውን የሚያስተናግዱት በተራ ነበር፡፡ ነገር ግን ለአይሻ ካላቸው የተለየ ፍቅር የተነሳ መሐመድ ከተከታዮቻቸው ስጦታ ሲበረከትላቸው እንኳ ስጦታውን በአይሻ ቤት ብቻ እያሉ እንዲያመጡቸው ያደርጉ ነበር፡፡ የሚመጣላቸውን ስጦታ በሌሎቹ ሚስቶቻቸው ቤት እያሉ አይቀበሉም ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በሚስቶቻቸው መካከል መከፋፈል መጣና አንደኛዋ ዑም ሰላማህ የተባለችው ሚስታቸው የዚህን ምክንያት ስትጠይቃቸው መሐመድ የሰጧት ምላሽ “መገለጦቹ የሚመጡልኝ የአይሻን ቀሚስ ስለብስ ነው” የሚል ነው፡፡ ይህ ታሪክ በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ “narrated by Aisha who related that the wives of the prophet were divided into two groups. One group consisted of Aisha, Hafsa, Safiya and Sawdah while the other group consisted of Um Salamah and the rest of the women that belonged to the prophet. The Muslims had learned of the great love that the prophet had for Aisha so that if one of them had a gift he desired to give to the prophet, he would delay giving it until the prophet came to Aisha's house. Then the group who sided with Um Salamah came to Um Salamah and asked her to tell the prophet that he should command the people that if any of them had a gift to give to the prophet, they should give it him in whatever house of his wives the prophet was in at the time. So Um Salamah went and talked with the prophet but he did not respond to her. When the group asked her what the prophet said she told them that he did not respond. So they asked her to go talk to him again until he responds... then the prophet said to her, “Do not hurt me with Aisha, for the inspiration did not come upon me when I was in a women's garment [fee thawb imra'ah] except that of Aisha.” Sahih Bukhari 2393 , “Muhammad went around to her and she spoke to him. He said to her, “Do not injure me regarding 'A'isha. The revelation does not come to me when I am in the garment of any woman except 'A'isha.” She said, "I repent to Allah from injuring you, Messenger of Allah.” Sahih Bukhari 2442 , Sahih Bukhari 3941, Sahih Muslim 31:5984 , Sahih Muslim 4472 , Mishkat Al Masabih, Volume II Book XXVI

መሐመድ ስለ ሰይጣን ያላቸው አመለካከት፡- መሐመድ ስለ ሰይጣን ያላቸው አስተምህሮት እጅግ አስቂኝና አሳዛኝ ነው፡፡ እስቲ ቀጣዮቹን ንዑስ ርዕሶች ይመልከቷቸው፡፡

መልአኩ ጂብሪል ለመሐመድ “ሚስትህን ሰላም በልልኝ” አላቸው፡- መሐመድ በ9 ዓመቷ ላገቧትና ከሁሉም ሚስቶቻቸው አስበልጠው በጣም ለሚወዷት ሕፃኗ ሚስታቸው ለአይሻ መልአኩ ጂብሪል “ሚስትህን ሃይ! በልልኝ” ብሎ ነግሯቸው መሐመድም እቤት እንደገቡ “ጂብሪል ሰላም ብሎሻል!” ይሏታል፡፡ አይሻም “የአላህ ምሕረትና ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን” በማለት አፀፌታውን መልሳለች፡፡ Narrated 'Aisha: that the Prophet said to her, "Gabriel sends Salam (greetings) to you." She replied, "Wa 'alaihi-s-Salam Wa Rahmatu-l-lah." (Peace and Allah's Mercy be on him). Sahih Bukhari 8:74:270

በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ባልና ሚስት የሚጸልዩት ጸሎት፡- እንደ መሐመድ አስተምህሮ ከሆነ ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እያደረጉ እያለ *“በአላህ ስም! ኦ አላህ ሆይ! ከሰይጣን ጠብቀን፣ የምትሰጠንንም ልጅ ሰይጣን እንዳይደርስበት አንተ ጠብቅልን”* በማለት ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ በግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው ወቅት ይህቺን ጸሎት ካልጸለዩ በዚያች ቅፅበት የሚፀነሰውን ልጃቸውን ሰይጣን ይቆራኘውና አብሮት ያድጋል፡፡ ልጃቸውን ከዚህ ዓይነቱ መቅሰፍት ለመታደግ ብቸኛው አማራጭ እንደዚያ ብሎ መጸለይ ነው፡፡ ይህንንም መሐመድ ለተከታዮቻቸው ሁሉ በትእዛዝ መልክ ነው ያስተላለፉው፡፡ “ማንኛችሁም ብትሆኑ ከሚስቶቻቸሁ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ስታደርጉ ይህቺን ጸሎት ጸልዩ፡- ‘በአላህ ስም! ኦ አላህ ሆይ! ከሰይጣን ጠብቀን፣ የምትሰጠንንም ልጅ ሰይጣን እንዳይደርስበት አንተ ጠብቅልን’ ይህን ካደረጋችሁ ልጃችሁን ሰይጣን አይጎዳውም” The Prophet said, "If anyone of you, when having sexual

relation with his wife, say:'In the name of Allah. O Allah! Protect us from Satan and prevent Satan from approaching our offspring you are going to give us,' and if he begets a child (as a result of that relation) Satan will not harm it." Sahih Bukhari 4:54:493. እንዲሁም ባልና ሚስት በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ወደ ዕቃቸው የሚያዩ ከሆነ በዚያ ባዩበት ቅፅበት የሚፀነሰው ልጅ ዐይነ ስውር ይሆናል። በግንኙነት ወቅትም ብዙ የሚያወሩም ከሆነ ልጁ መናገር የማይችል ይሆናል። the prophet said: If one of you got engaged in intercourse, they shouldn't look at the genital for that inherits blindness, and not talk too much for that inherits aphonia (lack of the ability to talk). Hadith translated by FFI forum member.

ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን ይዋሐደዋል፦ እንደ መሐመድ አስተሳሰብ ከሆነ ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን በሁለት ጣቶቹ ሁለቱንም ጎኖቹን ይዳስሳቸዋል። በዚህም ከሕጻኑ ጋር ውሕደትና ቁርኝት ይፈጥራል። ይህ ነገር ያልተፈጸመው በመሪየምና በልጇ በዒሳ ላይ ብቻ ነው። ሰይጣን ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ዒሳንም ሲወለድ ሊዳስሰው ቢሞክርም ሳይችል ቀርቷል። በእርሱም ምትክ የእንግዴ ልጁን ነው የነካው። The Prophet said, "When any human being is born, Satan touches him at both sides of the body with his two fingers, except Jesus, the son of Mary, whom Satan tried to touch but failed, for he touched the placenta-cover instead." Sahih Bukhari 4:54:506. ይህ የመሐመድ አስተሳሰብ ሁለት ነገሮችን በጣም ግልጽ ያደርግልናል። የመጀመሪያው ከላይ እንዳየነው ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን ጎኖቹን በመዳሰስ የሚቆራኘው መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን በጣም የሚገርመውና ሁለተኛው ነገር መሐመድ ራሳቸውን ከእንደዚህ ዓይነቱ የሰይጣን ቁርኝትና ፈተና ነፃ ለማድረግ አለመፈለጋቸው ነው። እርሳቸውም የችግሩ ገፈት ቀማሽ ነበሩ ማለት ነው። ለነገሩኮ በሌላ ቦታ መሐመድ ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እያደረጉ እያለ *"በአላህ ስም! ኦ አላህ ሆይ! ከሰይጣን ጠብቀን፣ የምትሰጠንንም ልጅ ሰይጣን እንዳይደርስበት አንተ ጠብቅልን"* በማለት ጸሎት ካደረጉ ሰይጣን በልጃቸው ላይ እንደማይደርስባቸው ለአማኞቻቸው ማረጋገጫ የምትሆነውን ጸሎት አስተምረው ነበር። በግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው ወቅት ይህቺን ጸሎት ካልጸለዩ ግን በዚያች ቅፅበት የሚፀነሰውን ልጃቸውን ሰይጣን ይቆራኘውና አብሮት ያድጋል። Sahih Bukhari 4:54:493. የመሐመድ አስተምህሮ ይህ ብቻ አይደለም። ሲወለድ ሰይጣን የማይነካውና የማይቆራኘው የአዳም ዘር ስለሌለ ማንኛውም ሕጻን ሲወለድ የዚህ ችግር ተጠቂ ነው። ሕጻናትም ልክ ከእናታቸው ማኅፀን ሲወጡ የሚያለቅሱት ሰይጣኑ በሁለት ጣቶቹ ጎኖቻቸውን ስለዳሰሳቸው ነው። Abu Huraira said, "I heard Allah's Apostle saying, 'There is none born among the off-spring of Adam, but Satan touches it. A child therefore, cries loudly at the time of birth because of the touch of Satan, except Mary and her child." Then Abu Huraira recited: "And I seek refuge with You for her and for her offspring from the outcast Satan." (3.36) Sahih Bukhari Book 55 No. 641 አሁንም ቢሆን ከዚህ ችግር ፍጹም ነፃ ሆነው የተወለዱት እመቤታችንና ልጇ ብቻ ናቸው። እመቤታችን ስትወለድና እርሷም ልጇን ስትወልድ ከዚህ ችግር የተጠበቁ ለመሆኑ ቁርአኑም በግልጽ ምስክርነቱን አስቀምጧል።

የሰይጣን መኝታ ቤት፦ የሰይጣን መኝታ ቤት የት ይመስላችኋል? ጨለማ ውስጥ?ሲኦል? አመድ ምናምን ወይ የሆነ ቆሻሻ ነገር የተደፋበት ወንዝ ውስጥ? ወይስ የት የሚተኛ ይመስላችኋል? እስቲ ገምቱ! ገምቱና በኋላ እኔ የመሐመድን መልስና አስተምህሮ እነግራችኋለሁ። እንደ መሐመድ ትምህርት ከሆነ የእኛ የአፍንጫችን ቀዳዳ የሰይጣን መኝታ ቤት ነው። ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ አሉ መሐመድ «ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ ውዱ አድርጉ (በሃይማኖታዊ ስርዓት ታጠቡ) የአፍንጫችሁን ቀዳዳዎች በውኃ እጠቡና 3 ጊዜ በውኃው ተናፈጡ ምክንያቱም በላይኛው የአፍንጫችሁ ውስጣዊ ክፍል ውስጥ ሰይጣን ሌሊቱን ሙሉ ተኝቶበት አድሯልና» ቡኻሪ 4:54:516፤ ሳሂህ ሙስሊም 2:462. "Narrated Abu Huraira: The Prophet said, 'If anyone of you rouses from sleep and performs the ablution [ritual washing], he should wash his nose by putting water in it and then blowing it out thrice, because Satan has stayed in the upper part of his nose all night." Sahih Muslim 2:462

ሰይጣን በሚያፋሽጉ ሰዎች ላይ ይስቅባቸዋል፦ እንደ መሐመደ ትምህርት ከሆነ ማፋሸግ ከሰይጣን፣ ማስነጠስ ደግሞ ከአላህ ነው። ስለዚህ አላህ ማፋሸግን ሲጠላ ማስነጠስን ግን ይወዳል። እናም የሚያፋሽጉ ከሆነ ሰይጣን ስለሚስቅብዎ ማፋሸግዎን ለማቆም የተቻለዎትም ሁሉ ማድረግ አለብዎ። ሲያስነጥሱ ግን አላህ ስለሚደሰትብዎ በሚያስነጥሱ ሰዓት አላህን ማመስገን ይጠበቅብዎታል። The Prophet said, "Allah likes sneezing and dislikes yawning, so if someone sneezes and then praises Allah, But as regards yawning, it is from satan, so one must try one's best to stop it, if one says 'Ha' when yawning, satan will laugh at him." Sahih Bukhari 8:73:242. Narrated Abu Huraira: The Prophet said, "Yawning is from Satan and if anyone of you yawns, he should check his yawning as much as possible, for if anyone of you (during the act of yawning) should say: 'Ha', Satan will laugh at him." Sahih Bukhari 4:54:509

ሰይጣን በሰው ጆሮ ውስጥ ሽንቱን ሸንቶ አደረ፦ መሐመድ ሌሊቱን ሙሉ ተኝቶ ስላደረ አንድ ሰው ይሰማሉ። ሰውየው ሌሊት

ለሶላትና ለጸሎት እንዳልተነሳ ይልቁንም እስከ ጠዋት ድረስ ተኝቶ እንዳደረ ለመሐመድ ይነገራቸዋል። ያን ጊዜ መሐመድ የሰጡት አስተያየት *"ሰይጣን በጆሮው ውስጥ ሸንቶበት ነው"* የሚል ነው። "A person was mentioned before the Prophet and he was told that he had kept on sleeping till morning and had not got up for the prayer. The Prophet said, "Satan urinated in his ears." Sahih Bukhari 2:21:245

ሰይጣን የሙስሊሞችን ጸሎት ለማስታጎል ሲል ፈሱን ይፈሳባቸዋል፦ ሙስሊሞች ለመስገድና ጸሎት ለማድረግ ጥሪ ሲደረግላቸው ጥሪውን እንዳይሰሙና ተረጋግተውም በሰከነ አእምሮ ሆነው ዱአ እንዳያደርጉ ሰይጣን ፈሱን ይፈሳባቸዋል። የእርሱን የፈስ ሽታ ተቋቁመው ተረጋግተው ጸሎታቸውን ቢያደርጉም እንኳን የጸለዩትን ነገር እንዳያስታውሱ ይልቁንም እንዲረሱት ያደርጋቸዋል። Allah's Apostle said, "When the Adhan is pronounced Satan takes to his heels and passes wind with noise during his flight in order not to hear the Adhan. When the Adhan is completed he comes back and again takes to his heels when the Iqama is pronounced and after its completion he returns again till he whispers into the heart of the person (to divert his attention from his prayer) and makes him remember things which he does not recall to his mind before the prayer and that causes him to forget how much he has prayed." Sahih Bukhari 1:11:582

ሰይጣን የሚመገባቸው ምግቦች፦ መሐመድ ዐይነ ምድር እየተፀዳዱ እያለ አንድ ሰው በአጠገባቸው ሲያልፍ ስላያቸው ነቢያቸው «መጥረጊያ የሚሆን ድንጋይ አምጣልኝ» ይሉታል። መሐመድ በዚህ ብቻ አላቆሙም። ሰውየውን ድንጋይ ብቻ ነው የምታመጣልኝ አጥንት ወይም ከእንስሳት የሚወጡትን (በጠጥ፣ እበት ወይም ፋንድያ) እንዳታመጣ ይሉታል። ምክንያቱም እንደ መሐመድ አስተሰሳሰብ እነዚህ ነገሮች የሰይጣን ምግቦች ናቸው። እንዲያውም ሰይጣኖች መሐመድን የሚበሉትን ፍርፋሪ ምግብ እንዲሰጧቸው ጠይቀዋቸው ነበር። መሐመድም በዚህ አዝነው አላህን ንጹሕ ምግብ እንዲሰጣቸው ለምነውላቸዋል። That once he was in the, company of the Prophet carrying a water pot for his ablution and for cleaning his private parts. While he was following him carrying it(i.e. the pot), the Prophet said, "Who is this?" He said, "I am Abu Huraira." The Prophet said, "Bring me stones in order to clean my private parts, and do not bring any bones or animal dung." Abu Huraira went on narrating: So I brought some stones, carrying them in the corner of my robe till I put them by his side and went away. When he finished, I walked with him and asked, "What about the bone and the animal dung?" He said, "They are of the food of Jinns. The delegate of Jinns of (the city of) Nasibin came to me--and how nice those Jinns were--and asked me for the remains of the human food. I invoked Allah for them that they would never pass by a bone or animal dung but find food on them." Sahih Bukhari 5:58:200

ሰይጣን በሦስት የተለያዩ ምሽቶች በሰው አምሳል እየተገለጠ የሰዎችን ምግብ ሰርቋል፦ Allah's Apostle said, "Verily, he told you a lie and he will return." I waited for him attentively for the third time, and when he (came and) started stealing handfuls of the foodstuff, I caught hold of him and said, "I will surely take you to Allah's Apostle as it is the third time you promise not to return, yet you break your promise and come." He said, "Forgive me"... The Prophet said, "He really spoke the truth, although he is an absolute liar. Do you know whom you were talking to, these three nights, O Abu Huraira?" Abu Huraira said, "No." He said, "It was Satan." Sahih Bukhari 3:38:505

ሰይጣን መሐመድን ከጸሎት ሊያቋርጣቸው መከረ፦ መሐመድ ዱዓ አድርገው ሲጨርሱ ስለራሳቸው ሲናገሩ "ሰይጣን በፊት ለፊቴ መጥቶ ትኩረቴን ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊቀይርብኝ በፅኑ ሞከረ ነገር ግን አላህ እንዳሸንፈው ጥንካውን ሰጠኝ" በማለት ተናግረዋል። The Prophet offered a prayer, and (after finishing) he said, "Satan came in front of me trying persistently to divert my attention from the prayer, but Allah gave me the strength to over-power him." Sahih Bukhari 4:54:504

ሰይጣን ማታ ማታ በእያንዳንዱ ሰው ጀርባ ላይ ሦስት የድግምት ቋጠሮዎችን አስሮ ያድራል፦ በእያንዳንዱ ሰው ጀርባ ላይ ማታ በተኛበት ሰይጣን ሦስት ቋጠሮዎችን ከጀርባው ይቋጥርበታል። በሁሉም ቋጠሮዎች ላይ "ሌሊቱ ረጅም ነው ስለዚህ በደንብ ተኛ" የሚል ቃልን ይተነፍስባቸዋል። ሰውየው ልክ እንደነቃ አላህን የሚያመሰግን እንደሆነ አንደኛው ቋጠሮ ይጠፋለታል። ውዱ ሲያድርግ ሁለኛው። ጸሎት ሲያደርግ ደግሞ የመጨረሻው ቋጠሮ ይጠፋለታል። ይህን ካደረገ ጠዋት ሲነቃ ደስተኛ ይሆናል አለበለዚያ ግን ቀኑ አሰልቺና ድብርታም ይሆንበታል። Allah's Apostle said, "During your sleep, Satan knots three knots at the back of the head of each of you, and he breathes the following words at each knot, 'The night is, long, so keep on sleeping,' If that person wakes up and celebrates the praises of Allah, then one knot is undone, and when he performs ablution the second knot is undone, and when he prays, all the knots are undone, and he gets up in the morning lively and gay, otherwise he gets up dull and gloomy. "Sahih Bukhari 4:54:491

መሐመድ እንዴት ነቢይ ብሎ ሊነሣ ቻለ? ይህንን ጥያቄ በደንብ ለመመለስ ያስችለን ዘንድ ቀጣዩን ርዕስ በጥሞና መመልከቱ ተገቢ ይሆና፡፡

የዐረቢያ ምድር- ከመሐመድ መወለድ በፊት፡- የዐረቢያ ምድር ከጥንት ጀምሮ የሁሉም የቤዱይን ፓጋን ዐረቦች መሰባሰቢያ ነበረች፡፡ በተለይም ዋናዋ መካ ከተማ የብዙ ቤተ-ጣኦታት (House of god) መናኸሪያ ነበረች፡፡ በውስጧም ከ360 በላይ ጣኦታትን በጋራ የያዘ ካዕባ (ka'aba) እየተባለ የሚጠራ የማምለኪያ ቦታ ነበር፡፡ መካ ከተማ ለንግድ ወደ ብዙ ሀገራት ለሚመላለሱ የሲራራ ነጋዴዎች ማረፊያ ስትሆን ዋነኛ የንግድ ማዕከልም ነበረች፡፡ መካ ሲደርሱም በጣኦቶቻቸው ፊት አምልኮታቸውን ይፈጽማሉ፡፡ መካ የቀድሞ ስሟም «በካህ» ይባል ነበር፡፡ ቁርአኑ 3:96 ላይ «ለሰዎች መጸለያ መጀመሪያ የተኖረው ቤት ቡሩክና ለዓለማት ሁሉ መምሪያ ሲሆን ያ በበካህ (በመካ) ያለው ነው» በማለት በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

በዘላንነት ከሚኖሩት ከተለያዩ ፓጋን ዐረብ ጎሳዎች በተለየ ሁኔታ ቁራይሽ የሚባሉት ጎሳዎች ዋነኛ የንግድ መናኸሪያ በሆነችው በመካ ሰፍረው ይኖሩ ነበር፡፡ ቁራይሾቹ ነጋዴዎች ከሩቅ ሲመጡ በካዕባ አጠገብ ካለው ውሃ ጥማቸውን የሚቆርጡበት ዘምዘም የሚባል ውሃ ከመሸጥ ጀምሮ ከነጋዴዎች በተለያየ መንገድ ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ መካን በዋናነት ሰፍረውባት የሚኖሩት ቁራይሾች ሦስት የተለያዩ ቡድኖች ወይም ግሩፖች ነበሩባት፡፡ የመጀመሪያዎቹ የ360 ጣኦታት መከማቻ የሆነውን የካዕባን ቤተ-ጣኦት ያስተዳድሩ የነበሩ የቀሳውስት አባላት ናቸው፡፡ ሁለተኞዎቹ በንግዱ የሚሳተፉ ትንሽ አባላት ያሉበት ሲሆን ሦስተኛዎቹ በኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ነገር ግን በርካታ አባላት ያሉበት ሲሆን ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው በየዓመቱ ለአምልኮ ወደ መካ ለሚመጡ ለሌሎች ፓጋን ዐረቦች ውሃ በማቅረብ ይተዳደራሉ፡፡ ለአምልኮ የሚመጡት ሰዎች ወቅት ጠብቀው ስለሆነ እነዚህ ሦስተኛዎቹ ወገኖች ታዲያ በቂ ገቢ ስለማያገኙ በኑሮ የተጎዱ ነበሩ፡፡ አብደላህ (Abdullah) የተባለ የእነዚህ የሦስተኛዎቹ ወገን አባላት የሆነ የቁራይሽ ሰው ነበር፡፡ ሚስቱ አሚና ትባላለች፡፡ አብደላህ ቋሚና በቂ ገቢ ስላልነበረው ኑሮው አስቸጋሪ ስለነበር እራት ሳይበሉ የሚተኙበት ጊዜም ነበር፡፡ አሚና ይህ ሕይወታቸው በእጅጉ ያሳስባት ስለነበር ልጅ እንዳይወልዱ ለማድረግ የተለየ ዘዴን እንዲጠቀም ባሏን ታስገድደው ነበር፡፡ ይጠቀሙበት የነበረው ዘዴም የወንዱን የዘር ፈሳሽ ወደ ውጭ እንዲፈስ (ejaculate) በማድረግ ነው፡፡ አብደላህና አሚና ይህንን ዘዴ ለረጅም ጊዜ ተጠቅመውበታል፡፡ {በነገራችን ላይ ይህን ዘዴ እነ መሐመድ የጂሃድ ጦርነት አድርገው ሴቶችንና ሕጻናትን በምርኮ (War captives) ከወሰዱ በኋላ ለባርነት ንግድ እንዲያመቻቸው በማለት ሴቶቹ እንዳያረግዙ ይህንን ዘዴ ይጠቀሙ እንደነበር በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጠቅሷል፡፡ ቡኻሪ 3:34:436፡፡ እንዲያውም መሐመድ ተከታዮቻቸው ይህንን ዘዴ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡ "ወደ አላህ መልእክተኛ አንድ ሰው መጣና እንዲህ አለ፡- 'የምታገለግለን ባሪያ ሴት ልጃገረድ አለችን፡፡ ከእርሷ ጋር ዝሙት ፈጽሜያለሁ ነገር ግን እንድታረግዝ አልፈልግም' ነቢዩም እንዲህ ሲል መለሰለት፡- 'ከፈለግህ የዘር ፈሳሽህን ወደ ውጭ በማፍሰስ (coitus interruptus or ejaculate) በማድረግ እንዳታረግዝ ማድረግ ትችላለህ'" (Sahih Muslim 8:3383)"ከነቢዩ መሐመድ ጋር ሆነን የባኑ አልሙስጣሊቅ ጎሳዎችን በጦርነት ለመማረክ ሄድን፡፡ የጦር ምርኮዎቻችን የሆኑ ሴቶችንም ወሰድን፡፡ ለወሲብ ስለተመኘናቸውም የዘር ፈሳሻቸንን ወደ ውጭ በማፍሰስ (coitus interruptus or ejaculate) በማድረግ እንዳያረግዙ አድርገን ከእነርሱ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀምን ፈለግን" (Sahih Bukhari 5:59:459)}

ወደ አብደላህና አሚና እንመለስና ሁለቱ በቂ ገቢ ስላልነበራቸው ኑሮውም በጣም አስቸጋሪ ስለሆነባቸው አሚና ልጅ እንዳይወልዱ ለማድረግ ይህንን የወንዱን የዘር ፈሳሽ ወደ ውጭ እንዲፈስ (ejaculate) የማድረግ ዘዴን ለረጅም ጊዜ እንዲጠቀም ባሏን ስታስገድደው ኖራለች፡፡ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበትም ኖረዋል፡፡ ይህ ድርጊት ለብዙ ጊዜ ሳትወልድ እንድትቀይ ቢያደርጋትም እርሷ እንዳሰበችው ግን ዘላቂ አልሆነላትም፡፡ አንድ ቀን አብደላህ ራሱን መቆጣጠር ያቅተውና ዘሩን ወደ ውጭ ሳያፈስ ቀረ፡፡ አሚናም በዚያች ቀን አረገዘች፡፡ በዚህች ቅፅበት የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ኢብን አብደላህ ተረገዙ፡፡ አሚና በማርገዟ በጣም ስለተናደደች ልታስወርደውም ብዙ ሞክራ አልሳካላት አለ፡፡ ባሏም ባራካት የተባለች ትውልዷ ኢትዮጵያዊ የሆነች ባሪያ ሴት ሠራተኛ ቢያመጣላትም አሚና ባረገዘች በ6 ወር ውስጥ አብደላህ ሞተ፡፡ "Because Abdullah did not have a consistent income, his household often suffered from deprivations. Many a times, the couple had to go to bed without food. Persistent poverty took its toll; the couple frequently fought and argued on their financial condition as well as on what was likely to happen to them in future. Recognizing the fact that she and her husband did not have the means to feed another mouth, Amina always forced her man to ejaculate his semen outside her vagina. This practice helped her to avoid pregnancy for some time, but one night Abdullah failed to control himself, and she ended up being a pregnant woman. Amina was angry. She tried her best to destroy the pregnancy,

but failed. Unable to do anything else with her conception, she resigned to her fate and decided to carry her pregnancy to its full term. Abdullah, her husband, felt for her discomforts and sought to help by providing her with the services of a slave-girl, named Barakat. But as misfortune would have it, Amina's husband died when she was six months into her pregnancy." (Muhammad and the Origins of Islam, p. 126 & Philip K. Hitti, History of the Arabs, p. 133)

የመሐመድ የልጅነት ሕይወት እጅግ አሰቃቂ ነበር፡- አብዱላህ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ ልጁ መሐመድ በ570 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ አሚናም ስማቸውን ኮዛን (kothan) ብላ ጠራቻቸው፡፡ ነገር ግን በኋላ ላይ ወንድ አያታቸው መሐመድ ብሎ ሰይሟቸዋል፡፡ መሐመድ በተወለዱበት ዘመን መላው የዐረቢያን ምድር በአምልኮ ጣዖት፣ ልቅ በሆነ ዝሙትና በግብረ ሰዶማዊ ተግባርና በሌሎችም አጸያፊ ተግባራት የተጠመደ ሕዝብ ነበር የሚኖርባት፡፡ ይሁን እንጂ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዚህ ልቅና ቅጥ ባጣ ወሲባዊ ሕይወታቸው ምክንያት ሴቶቹ ዲቃላ ሲያረግዙ በጎብረተሰቡ ዘንድ በእጅጉ ይወገዙና ይጠሉ ነበር፡፡ አሚናም ዲቃላ ነው የወለደችው ተብላ ይህ መሰደብና መገለል ስለደረሰባት ልጇን አትይዘውም፣ ጡትም አታጠባውም ነበር፡፡ ይህንን ሁኔታ ተመልክታ የታዘበችው የመሐመድ አጎት የአቡ ላህብ ሠራተኛ የሆነችው ዙዋይባህ ለጊዜውም ቢሆን በማለት መሐመድን እየተመላለሰች ትመግባቸው ነበር፡፡

ሀብታም የካራቫን ነጋዴዎች ወቅት ጠብቀው በካዕባ አምልኮአቸውን ሊሚፈጽሙ ወደ መካ ከተማ በሚመጡበት ጊዜ ድህ የሆኑ የቤዱይን ዐረቦችም ወደ ቦታው እየመጡ ጥቃቅን ሥራዎችን ይሠሩና ይለምኑ ነበር፡፡ በዚህ ልማድ መሠረት ሀሊማ የተባለች ሴት ወደ መዲና መጥታ የአሚናን ቤት ታገኛለች፡፡ አሚናም ልጇን መሐመድን እንድትወስድላት ስትጠይቃት እንግዳዋ ሴትም ከፍ ሲል በእረኛነት አስቀጥሬው እጠቀምበታለሁ በማለት በአሚና ሀሳብ ተስማምታ መሐመድን ወሰደቻቸው፡፡ የሀሊማ ጎሳዎች ይኖሩ የነበረው በሰሜናዊ ዐረቢያ አካባቢ ለእርሻና ለእረኝነት አመቺ በሆነ ሸለቆያማ አካባቢ (pastoral valleys) ነበር፡፡ ሀሊማ በመሐመድ ዕድሜ የሚገኝ ማስሩድ የሚባል ልጅ ስለነበራት አብራ እያጠባች አሳደገቻቸው፡፡ ከአምስት ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ መሐመድና ማስሩድ አንድ ላይ ሲጫወቱ የዋሉትን ጨዋታ ለሀሊማ ይነግሯት ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን ማስሩድ ለእናቱ የተለየ ነገር ነገራት፡፡ «በዱር ስንጫወት መላዕክት የመሰሉ ሁለት ነጫጭ ሰዎች መጥተው መሐመድን ከበውት አየሁ» አላት፡፡ ንግግሩንም ቀጠለ፡- «እየተጫወትን እያለ ሁለቱ ሰዎች መጥተው መሐመድን መሬት ላይ ጣሉት፡፡ ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ጂብሪል የመሐመድን ልቡን ቀደደና ውስጡን አጠበለት፡፡ በዚህም በውስጡ ያለውን እንደ ጥቁር ያለ በዘር የሚተላለፈውን የአደምን በደል አጥቦ አውጥቶ ካነፃው በኋላ በእውቀትና በእምነት ሞላው፡፡ የነቢይነትንም ብርሃን አሳየው፡፡ የነቢይነትንም ምልክት በትከሻና ትከሻዎቹ መሀከል የጠባሳ ምልክት አድርጎበታል» እያለ ሁኔታውን በዝርዝር ለእናቱ ከነገራት በኋላ ነገሩን ከመሐመድም አንደበት እውነት መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ ሀሊማ ይህንን በአካባቢዋ ላሉ ሰዎች ሁሉ ነገረቻቸው፡፡ መሐመድንም አምጥታ በሰዎቹ ፊት ራቁታቸውን አቁማ በትከሻዎቻቸው መሀል ያለውን ጠባሳ አሳየቻቸው፡፡ በዚህም ፍርሃት ስላደረባት መሐመድን ወደ እናቱ መልሳ ወሰደቻቸው፡፡ ለእናታቸው ለአሚና የሆነውን ሁሉ ነገረቻትና ተመልሳ ወደ ሀገሯ ሄደች፡፡

አሚናም በመካ ያሉ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እየወሰደች አሳየቻቸው፡፡ ከእናቷም ዘመዶች ጋር ልታገናኛቸው ወደ መዲና ከተማ ስትሄድ መንገድ ላይ ሳለች «አብዋ» በሚባል ቦታ ድንገት ሞተች፡፡ (አብዋ በመካና በመዲና መካከል የምትገኝ ትንሽ መንደር ነበረች፡፡) በዚህ ጊዜ መሐመድ 7 ዓመት እንኳን አልሞላቸውም ነበር፡፡ አብራ ተጉዛ የነበረችው ሠራተኛዋ ባራካት መሐመድን ለአያታቸው ለአብድ አል-ሙታሊብ ወስዳ ሰጠቻቸው፡፡ አብድ አል-ሙታሊብ የካዕባ ቤተ-ጣኦት ዋና ጠባቂ ነበር፡፡ ከዚህ ሥራው የተሻለ ገቢ የሚያገኝ ቢሆንም ቤተሰቡ ብዙ ስለሆነ የእርሱም የኑሮ ሁኔታ ሌላ ሰው ለመጨመር የሚያስችል አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት ቤተሰቦቹ መሐመድን እንዲሄዱላቸው ሁልጊዜ የተለያየ በደል ያደርሱባቸውና ጥላቻቸውም ይገልጹላቸው ነበር፡፡ መሐመድም በዘመዶቻቸው ላይ ቂም እያያዙና ጥላቻ እያሳደሩ መጡ፡፡ ነገሩን አብድ አል-ሙታሊብ ሲሰማ መሐመድን ከ3 ዓመት ቆይታ በኋላ ለመጀመሪያ ልጁ ለአቡ ጣሊብ ሰጣቸው፡፡ አቡ ጣሊብም በኋላ ላይ አባቱ ሲሞት በምትኩ የካዕባ ቤተ-ጣኦት ዋና ጠባቂ ሆነ፡፡ መሐመድም በዚያ በቤተ ጣኦቱ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ እያዩ እንዲያድጉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጠሩላቸው፡፡

የአቡ ጣሊብም ቤተሰብ በርካታ ስለነበር ገቢውን ለማሳደግ ከቤተ-ጣኦቱ ዋና ጠባቂነት በተጓዳኝ ከካራቫን ነጋዴዎች ጋር ለንግድ ወደ ሶሪያ፣ የመን፣ ግብፅና ሌሎችም ሀገራት እየሄደ መነገድ ጀመረ፡፡ መሐመድም አጎታቸውን አብሮ ይዟቸው እንዲሄድ ብዙ ከለመኑት በኋላ ይዟቸው መሄድ ጀመረ፡፡ መሐመድም በሄዱበት ሀገር ሁሉ ያለውን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሥርዓት ይመለከቱና ይጠይቁ ነበር፡፡ ስለ እምነት ጉዳይ ከእነዚህ ሀገራት ያገኙትን ነገር እርሳቸው የሚፈልጉትን እየመረጡ ይወስዱና በመሠረቱት እስልምና ውስጥም ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ይህንን ወደፊት ራሱን የቻለ ርዕስ ስላለው ያን ጊዜ በደንብ እናየዋለን፡፡ ለአሁን ግን አንድ ምሳሌ እንይ፡- አንድ ጊዜ ወደ ሶሪያ ሲሄዱ ቀይ ባሕር አካባቢ ኢይላ (eyla) በምትባል ትንሽ መንደር ያድራሉ፡፡ ነዋሪዎቿ ጣኦት አምላኪዎች ነበሩና ማታ

ስለ ጣኦታቸው ሲያወሩ መሐመድ ይሰማሉ፡፡ «አምላካችን ዓለምን ወደተሻለች ሌላ ዓለም ይለውጣታል» ብለው ያምኑ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም አምላካችን ኃጢአት የሠሩ ትላልቆቹን ሰዎች ወደ አሳማነት፣ ትናንሾቹን ሰዎች ደግሞ ወደ ዝንጀሮነት ይለውጣቸዋል ብለው እንደሚያምኑ ለእነ መሐመድ ነግረዋቸዋል፡፡ መሐመድም ይህንን በቀጥታ ወስደው በሐዲሱ ላይ ተጠቅመውበታል፡፡ ማለትም አላህ አይሁዶችን ወደ ዝንጀሮነት እንደሚለውጣቸው ተናግሯል፡፡

ሌላም አንድ ምሳሌ እንይ፡- መሐመድ ከመካ ነዋሪዎች ጋር ጦርነት ውስጥ በገቡ ሰዓት ራሳቸውን ለጦርነት ለማዘጋጀትና ድጋፍም ለማግኘት ሲሉ ከመካ 70 ማይልስ ርቃ ወደምትገኘው ጣይፍ ወደምትባል ትንሽ መንደር ሄደው ነበር፡፡ በዚያም የሚኖሩ ታቂፍ የሚባሉ ፓጋን የዐረብ ጎሳዎች «አል-ላት» የተባለችውን አንዷን የአላህን ሴት ልጅ ያመልኩ ነበር፡፡ «ከሞት በኋላ ከአላህ ዘንድ እየለመነች ሥጋዊ ፍለጎታችንን የምታሟላልን አማልክታችን ናት» ብለው ያምናሉ፡፡ መሐመድም ጦራቸውን አዘጋጅተው እስኪመለሱ ድረስ ከአንድ ወር በላይ በዚህች መንደር ቆይተው ነበርና ይህንን የጣኦት እምነት እርሳቸውም «በጂሃድ ተሳትፎ በአላህ መንገድ ለሚጋደል ለአንድ ሙስሊም ከሞተ በኋላ በጀነት ውስጥ 72 ደናግላን ለዝሙት ተግባር በሽልማት ይሰጡታል» በማለት በቀጥታ ወስደው በቁርአኑና በሐዲሱ ውስጥ ተጠቅመውበታል፡፡ (በጀነት ውስጥ ከ72 ደናግላን ጋር ስለሚደረገው ዝሙት በገጽ-—ላይ ይመልከቱ) በሌላም ወቅት እንዲሁ አንድ የተፈጸመ ሌላ ታሪክ አለ፡፡ ሰልማን አል-ፓርሲ/psalman al-parsi/ የተባለ የፐርሺያ ጦር መሪ ከሮማኖች ጋር ጦርነት ገጥመው ካሸነፉ በኋላ ወደ ሀገሩ ሳይመለስ ወደ መዲና በመሄድ መካን ለመውረር ይሰናዱ የነበሩትን መሐመድን ተቀላቅሏል፡፡ ሁለቱም ቀደም ብለው በጎግዱ እያሉ በደንብ ይተዋወቁ ነበር፡፡ ሰልማን አል-ፓርሲ የዞራስትሪያን እምነት ተከታይ ሲሆን ለመሐመድ ይህንን እምነቱን በሚገባ ገልጾ አስተምሯቸዋል፡፡ ሰልማን ከነጭራሹም ወደ ሀገሩ ፐርሺያ ሳይመለስ በዚሁ በመዲና በቋሚነት ኖሮ ነው የሞተው፡፡ ዛሬም ድረስ በቁርአን ውስጥ የዞራስትሪያንን የእምነት አስተሳሰቦችን በሰፊው ተጽፈው የምናገኘው ለዚህ ነው፡፡

መሐመድ ለጎግድ ወደ ሶሪያና ግብፅ በተጓዙበት ወቅት ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር ተገናኝተው ስለ እምነታቸውም ብዙ ሰምተዋል፡፡ ባሂራ (bahira) የተባለ አንድን መነኩሴ እንዳገኙና ከእርሱም ጋር በተደጋጋሚ ተገናኝተው ስለ ክርስትናው፣ ስለ ጣኦታት ከንቱነት፣ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርትን፣ ስለ መንግስተ ሰማያትና ስለ ሲኦል ብዙ እንዳስተማራቸው የመሐመድን የግል የሕይወት ታሪካቸውን በስፋት የዘገቡት የታሪክ መዛግብት ይገልጻሉ፡፡ መሐመድ ከዚህም ሌላ ከዐረብኛው በተጨማሪ የዕብራይስጥኛን ቋንቋ የሚናገር አዳስ (Adas) ከተባለ መነኩሴም ጋር ብዙጊዜ አውርተዋል፡፡ ይህንን ቁርአኑ 16፡103 ላይ እንዲህ በማለት ጠቅሶታል፡፡ «ለመሐመድ ቁርአንን የሚያስተምረው ሰው ብቻ ነው ማለታቸውን በእርግጥ እናውቃለን፤ የዚያ ወደርሱ የሚያስጠጉበት ሰው ቋንቋ ዐጀም ነው፤ (1) ይህ ቁርአን ግን ግልጽ ዐረብኛ ቋንቋ ነው» ይላል ቁርአኑ፡፡

(1) የቁርአኑ የግርጌ ማስታወሻ ላይ «ዐጀም ከዐረብኛ ሌላ የሆነ ቋንቋ ነው» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡

እንመለስና ምልከታችንን እንቀጥል፡- መሐመድ በጎግዱ ሥራ ታታሪና ጎበዝ መሆናቸውን ተመልክተው የካራቫን ነጋዴዎች እንደ ወኪል (commericial agent) አድርገው ሊቀጥሩአቸው ብለው ነበር ነገር ግን ማንበብና መጻፍ የማይችሉ በመሆኑ ሀሳባቸው ሳይሳካና ሳይቀጥሩአቸው ቀሩ፡፡ መሐመድ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ መሆኑን በቁርአኑ ላይ ጠቅሶታል፡፡ መሐመድ ለጎግድ ኢየሩሳሌም ድረስ ሄሰው በዚያ በሞሪያም ከፍታ ላይ የተሠራውን የሰሎሞንን ቤተ መቅደስም ተመልክተዋል፡፡ በኋላ ላይ እምነታቸውን ሲመሠርቱ ይህን የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ እንደ ግብዓት ተጠቅመውበታል፡፡ ማለትም መሐመድ ሲያስተምሩ አንድ ሴት ፈረስ ጋልበው ወደ ሰባቱ ሰማያት ሲሄዱ ፈረሷ በዚህ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ላይ አርፋ ነበር፡፡ ሴቷ ፈረስ ክንፍ ያላት ሲሆን ስሟ «ቡራቅ» ይባላል፡፡ የፊቷ ቅርጽ የቆንጆ ሴት ፊት ሲሆን ጅራቷ ደግሞ የጢኮክ ጅራት ነው፡፡ መሐመድ ለተከታዮቻቸው እምነታቸውን ሲያስተምሩ በዚህች «ቡራቅ» የምትባል ፈረስ ጋልበው በእኩለ ሌሊት እዚህ ቤተ መቅደስ ላይ ወጥተው በዚያውም ወደ ሰባቱ ሰማያት እንደሄዱ አስተምረዋቸዋል፡፡ ዛሬ ሙስሊሞቹ ይህንን ቦታ ከቤተ ጣኦቱ ከካዕባና መሐመድ መዲና ላይ ከሠሩት ከነቢ መስጂድ /masjidul nabi/ ቀጥሎ 3ኛው ቅዱስ ቦታችን ነው የሚሉት ለዚህ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር ማንሳት ፈለግሁ፡፡ ነቢያቸው መሐመድ መዲና ላይ በግመላቸው ጠቋሚነት መስጂዱን ከሠሩ በኋላ ተከታዮቻቸውን እንዴት አድርገው መጥራት እንዳለባቸው ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ የጦር መሪ እያደረጉ ያሰማሯቸው የነበሩትን ሰዎችም ሰብስበው አማከሯቸው፡፡ «እናንተን ለስግደት ስጠራ ጥሪ ማድረግ ያለብኝ እንዴት ነው? እንደ አይሁዶች የትራምፔት ድምጽ በማሰማት ልጥራ? ወይስ የመስጂዱ ጫፍ ላይ በመሆን እሳት በማንደድ ልጥራ?» እያሉ ሲጠይቋቸው መልስ ከሰጧቸው ሰዎች መሀል «ለምን አንድ ሰው ከመስጂዱ አናት ላይ ወጥቶ አይጮህም?» የሚለው የዛይድ ልጅ የሆነው የአብዱላህ ሀሳብ ነው ተቀባይነትን ያገኘው፡፡ «ታዲያ ጮሆ የሚጣራው ሰው ማን ይሁን?» ሲባል ድምጹ በጣም ያምር የነበረውና በባርነት ተይዞ የነበረው በኋላ ለጂሃድ ውጊያ ሲባል ነጻ የተለቀቀው የአቢሲኒያው ተወላጅ ቢላል ሀበሺ ተመራጭ ሆኖ የመጀመሪያው ጥሪ አድራጊ ሆነ፡፡ መደበኛ ሥራውም ይህ ብቻ ሆኖ ቀረ፡፡ መሐመድ በሞቱ ጊዜ በዚያ ራሳቸው በሠሩት መስጂድ ውስጥ ነው የተቀበሩት፡፡ ሙስሊሞች ዛሬ መዲናን «የነቢዩ ከተማ» /the city of the prophet/ በማለት ነው የሚጠሯት፡፡ መዲና

ከተማ ላይ ዛሬም ሆነ ወደፊት አውሮፕላን ፈጽሞ አያርፍባትም ምክንያቱም አውሮፕላኑ የመስቀል ቅርፅ ስላለው ነው።።
የመሐመድን የሕይወት ጉዞ ወደማየቱ እንመለስና በ25 ዓመታቸው የመጀመሪያ ሚስታቸውን የ40 ዓመቷንና ሀብታሟን ከድጃን ካገቡ በኋላ ሕይወታቸው በአንድ ጊዜ ነበር የተለወጠው።። ከድጃ አባቷ ኩዋሊድ ከቁራይሾች ወገን ሲሆን ቀደም ብላ ሁለት ጊዜ አግብታ ሁለቱም የሞቱባት ቢሆንም ሁለተኛው ባሏ ሀብታም ስለነበር ሀብቱን አውርሷታል።። ኩዛይማ የሚባል የወንድሟ ልጅ ነው ከመሐመድ ጋር ያስተዋወቃት።። ኩዛይማና መሐመድ ለአምልኮ በየጊዜው ወደ ካዕባ ቤተ-ጣኦት ሲሄዱና ሲገናኙ በዚያው ወዳጅነት መሠረቱ።። መሐመድም አንድ ቀን የተሻለ ሥራ ቢያገኙ ደስተኛ እንደሚሆኑ ሲነግሩት ወስዶ ከከድጃ ጋር አገናኛቸው።። እርሷም ንግዷን የሚቆጣጠርላት ጠንካራ ሰው ትፈልግ ስለነበርና መሐመድን ገና እንዳየቻቸው ስለወደደቻቸው እሳቸውን ለማግባት ጊዜ አልፈጀችም።። አግብታውም የንግዱን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ሰጠቻቸው እርሳቸውም በብቃት ተወጡት፣ ትርፋማ መሆንም ጀመሩ።። ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ ያዩአቸውን የሕዝቦች ባሕልና እምነት በመካ ካለው የዘቀጠና ሞራላዊ እሳቤ ከሌላቸው ወገኖቻቸው ጋር ሲያነፃፅሩት ሀዘን ይሰማቸው ነበርና ይህንንም ለመለወጥ ተመኙ።። ይህንንም ለማድረግ ሲነሡ ብዙ ነገሮችን ማሰባሰብ ጀመሩ።። በዝሙትና በባዕድ አምልኮ የተጠመዱ ወገኖቻቸውን ለመለወጥ ካላቸው ፅኑ ፍላጎትና ምኞት የተነሳ በቅድሚያ ስለ ሌሎቹ እምነቶች ማወቅና መረጃም ማሰባሰብ ጀመሩ።። የክርስትናውን ትምህርት ማለትም ቀደም ብሎ ያ ባሂራ (bahira) የተባለው መነኩሴ ያስተማራቸውን ትምህርት፣ ስለ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (ሙስሊሞቹ ዛሬ ተውራትና ኢንጂል ይሏቸዋል) ጠየቁ።። ከላይ እንዳልነው ወገኖቻቸውን ለመለወጥ ካላቸው ፅኑ ፍላጎትና ምኞት የተነሳ ከወገኖቻቸው ባዕድ እምነት የተሻለ ነው ብለው ያሰቡትን ትምህርት አሰባሰቡ።። ለምሳሌ በወቅቱ ተነስተው የነበሩ የመናፍቃንንም ትምህርት እንኳን ሳይቀር የዞራስትሪያንን ትምህርት፣ የታልሙድን ሥርዓትና የጁዲይዝምን ትምህርት በአጠቃላይ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ የተሻለ ነው ያሉትን ትምህርትና ሥርዓት ሰብስበው ነው ወደ እምነት ምሥረታ የገቡት።። (ወደፊት የቁርአን ምንጮች ምን ምን እንደሆኑና ከየት ከየት ተሰብስበው በአንድ እንደተጠቃለሉ ኮፒ ከተደረጉበት ጋር አንድ ላይ በማያያዝ በዝርዝር እናየዋለን) አሁን ግን የተነሳሁበትን ሀሳብ ልቀጥልና መሐመድ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ነው «መልአኩ ጂብሪል ተገለጠልኝ» እያሉ ብቻውን ስንቃቸውን እያየዙ ወደ ሂራ (hira) ተራራ መሄድ የጀመሩት።። በዚያም በሚያጋጥማቸው ነገር ልክ በልጅነታቸው እንዳደረገው «ጂብሪል መጥቶ ልቤን ቀዶ ውስጤን አጥቦ የነቢይነትን መንፈስ በድጋሚ ሞላኝ» በማለት መሐመድ እንደተናገሩ በሐዲሱ ላይ ተመዝግቧል።። በኋላ ላይ ሰይጣን ይዞኛል በማለት በዚህም ባጋጠማቸው ነገር እጅግ ስለፈሩ ራሳቸውን ለማጥፋት ሁሉ ሞክረው መልአኩ እንደከለከላቸውና እንዳዳናቸው ራሳቸው መሐመድ በሐዲሱ ላይ ተናግረዋል።። (ዝርዝሩን በመጀመሪያዎቹ ገጾች ላይ መመልከት ይቻላል)

መሐመድ በዚህ መልኩ «ጂብሪል ነቢይ መሆኔን አብስሮኛል» ካሉ በኋላ ነው እምነታቸውን ለመመስረት የተነሡት።። በቁርአኑ ላይም እምነታቸውን ለመመስረት የመጀመሪያ ሰው ሆነው እንደተነሡ ብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሷል።። ለምሳሌ ሱረቱ አል-አንዓም 6፡163 ላይ "እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ" ብለው ተናግረዋል።። በሌላም ቦታ በሱረቱ አል-ዙመር 39፡12 ላይ "የሙስሊሞችም መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ" ነው ያሉት።። እናም በዚህ መልኩ በ610 ዓ.ም እምነታቸውን ለመመስረት ሲነሡና የመጀመሪያውን መገለጥ ከጂብሪል ተቀበልኩ ሲሉ ዕድሜአቸው 40 ነበር።። «ነቢይ ሆንኩ» ብለው ለመነሣት ለምን ይህንን ዕድሜ መረጡት? ካልን ፓጋን ዐረቦቹ በባሕላቸው መሠረት አንድ ሰው በ40 ዘመኑ የበቃ የነቃ ይሆንና ከሁሉም የበላይ ከሆነው አምላክ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይኖረዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው።። መሐመድ እንደተናገሩት በሂራ ተራራ ዋሻ ውስጥ ሆነው ጂብሪል አረፋ እስኪደፍቃቸው ድረስ ልባቸውን በኃይል ሦስት ጊዜ እየተጫነ ቃሉን በልባቸው ላይ እንዳኖረላቸው ነው የተናገሩት።። በዋሻው ውስጥ ለብዙ ጊዜ እየቆዩ ወደቤታቸው የሚመለሱት ሰውነታቸው በላብ ተዘፍቆ እንደነበር ሚስታቸው ከዲጃ ተናግራለች።። እቤት እንደገቡም «በብርድ ልብስ ሸፍኚኝ» ይሏትና ይተኙ ነበር።። በተኙም ሰዓት ጂብሪል ተገልጦላቸው «እስካሁን ተኝተሃል እንዴ? ተነሣና ስበክ እንጂ!» እያለ ከተኙበት እንደቀሰቀሳቸው ራሳቸው መሐመድ ተናግረዋል።።
ነቢያቸው መሐመድ ስብከታቸውን በጀመሩ ሰዓት ለባሏ ዓላማ መሳካት የራሷን አስተዋፅኦ ለማድረግና ሂደቱንም ለማስጀመር ስትል የመጀመሪያ የእምነታቸው ተከታይ የሆነችው ሚስታቸው ከድጃ ናት።። እርሷም በ619 ዓ.ም በ65 ዓመቷ ነው የሞተችው።። ከእርሷ ቀጥሎ የአጎቷ ልጅ የሆነው ዋራቅ ኢብን ኖፋል መካ ውስጥ የነበረው አስከፊ ገፅታ እንዲለወጥ ካለው ፍላጎት የተነሣ የቅርብ ሰዎችን በማስተዋወቅ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ቢሆንም አላመነበትም ነበርና የመሐመድን እምነት ሳይቀበል ነበር የሞተው።። አሳዳጊ አጎታቸው አቡ ጣሊብም እንዲሁ ለመሐመድ ሁኔታዎችን ያመቻቸላቸውና በከፍተኛ ሁኔታ የረዳቸው ሰው ቢሆንም እምነታቸውን ግን ሳይቀበል ነበር የሞተው።። እንዲሁም አምሩ ኢብን ሀሺም የተባለውን የመሐመድን አጎት ቁራይሾች «የእውቀት አባት» 'father of wisdom' እያሉ ይጠሩት ነበር ምክንያቱም ሚዛናዊ ውሳኔዎችን በመስጠትና በብልህ ፈራጅነቱ ያደንቁት ስለመነበር ነው።። ሆኖም በተቃራኒው ይኸኛውም ብልሁ አጎታቸው መሐመድን ስላልተቀበላቸው እንዳውም መሐመድን «ተው ልጄ ይህ ነገር ይቅርብህ» እያለ ይመክራቸው ነበር።። መሐመድ ግን ምክሩን አልቀበል ከማለታቸውም በላይ ብልህ አጎታቸው እምነታቸውን አልቀበል ስላለ በንዴት «አቡ ጃህል» የሚል ስያሜ አውጥተውለታል።። ትርጉሙም «የሞኝ አባት» 'father of fully' ማለት ነው።። በቁራይሾች ዘንድ «የእውቀት አባት»

ለተባለው ስሙ የአፀፈ፟ታ ምላሽ መሆኑ ነው::
ከመሐመድ ሚስት ቀጥለው የሰለሙት የመጀመሪያዎቹ አምስት ሰዎችም የከድጃና የእርሳቸው የቅርብ ዘመዶች ናቸው:: ከእነዚህ ሰዎች ጋር ሆነው ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ያህል በምሥጢር ቤት ለቤት ነበር ይሰብኩ የነበረው:: ተከታዮቻቸውም እስከ 40 ከደረሱላቸው በኋላ ነው በግልጽና በድፍረት መስበክ የጀመሩት:: መሐመድ በገሀድ መስበክ እንደጀመሩ የመካ ሰዎች በእርሳቸው ላይ የተለያየ አስተሳሰብ ነበራቸው:: አንዳንዶቹ «ትምህርቶችህ ቀድሞ የምናውቃቸው ተረቶች እንጂ ሌላ አይደሉም» ሲሏቸው ሌሎቹ ደግሞ የአእምሮ ችግር እንጋጠማቸው በማሰብ «የአብድ አል-ሙታሊብ የልጅ ልጅ የሆነው ይህ ሰው አብዷል» ይሏቸው ነበር:: ሌሎች ሰዎች ደግሞ «በሰይጣን ተይዟል» እያሉ ሲያዝኑላቸው በሌላ በኩል ደግሞ «አንዳች የማጂክ ኃይል» እንዲኖረው የሚፈልግ መተተኛ ዓይነት ሰው እንደሆኑ አድርገው ያስቧቸው ነበር:: የባሰባቸው ደግሞ እሰብካለሁ ሲሉ የግመል ፈርስና ቆሻሻ እያነሱ ፊታቸው ላይ እየጣሉባቸው ትተዋቸው ይሄዱ ነበር:: ምክንያቱም መሐመድ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ጂኒዎችንም (ሰይጣኖችን) ጭምር ወደ እስልምና ለማምጣት እንደተላኩ ይሰብኩ ስለነበር ነው:: ይህም በቁርአኑ 46ኛውና 72ኛው ሱራ ላይ ተጠቅሷል:: መሐመድ ከዚህ በኋላ ሰላማያዊ በሆነ መልኩ ማስተማሩ እንዳላዋጣቸው ሲያውቁ ነው ሰይፍን እንደዋነኛ የእምነታቸው ማስፋፊያ መሳሪያ አድርገው የተጠቀሙበት:: (የመሐመድን አጠቃላይ የሕይወት ጉዞአቸውን መመልከታችንን በኋላ ስለምመለስበት ለአሁኑ ትንሽ ገታ ላድርገውና ከእምነት ምስረታቸው ጋር ብቻ ተያያዥ የሆኑ ነጥቦችን ላንሳ:: ስለዚህ ቀጥሎ የማነሳቸውን ሦስት ተያያዥ ርዕሶችን ልብ ብላችሁ እንድትመለከቱልኝ እፈልጋለሁ)

<u>መሐመድ ያደጉት የፓጋን ዐረቦችን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓታቸውን እየፈጸሙ ነበር</u>:- ከመሐመድ መነሳት በፊት የነበሩ ፓጋን ዐረቦች የተያዩ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች ነበሯቸው:: ለምሳሌ ከወሩ ውስጥ አንዱን ቀን የመጾም ልማድ ነበራቸው፤ ሲጾሙም ምግብና መጠጥ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ ነገር ግን ምንም አያወሩም ነበር:: አማልእክቶቻችን እንዳይጠፉ እያሉ ስለ ፀሐይና ጨረቃ መግባትና መውጣት በጾማቸው ወቅት ሦስት ጊዜ ይጸልያሉ:: ሌላው ክብረ በዓላቸው የነበረው ነገር ወቅት እየጠበቁ አንድ ላይ ተሰብስበው ወደ ቤተ-ጣኦቱ ካዕባ የሃጂ ጎዞ (pilgrimage) ያደርጋሉ:: የቤተ-ጣኦቱንም የካዕባን ግንብ ሰባት ጊዜ ይዞራሉ:: በዚያ ለሚገኙትም በርካታ ጣኦቶቻቸው በስማቸው እንስሳትን መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ:: ሌላው ሥርዓታቸው ደግሞ ማርዋ እና ሳፋ የተባሉ ሁለት ከፍታ ቦታዎች አሉ:: በእያንዳንዳቸው ላይ ሴትና ወንድ ጣኦታት ያሉ ሲሆን ከአንደኛው ወደ ሌላኛው ሮጠው በመሄድ በዓል የማክበር ልማድ ነበራቸው:: የሁሉንም ወንዶች ጸጉር መላጨት የበዓላቸው የፍጻሜ ፕሮግራም ነበር:: የመሐመድም ጎሳ አባላት የሆኑት ቁራይሾች በካዕባ ይካሄዱ የነበሩ ባዕድ አምልኮዎችን ይፈጽሙ ነበር:: መሐመድም ይህንኑ ያሳዳጊዮቻቸውን እምነት ይዘው ድርጊቶቹን ሁሉ ተግባራዊ እያደረጉ ነው ያደጉት:: እንዲያውም ያሳደጉአቸው አያታቸውና አጎታቸው የቤተ-ጣኦቱ ጠባቂዎች መሆናቸውን ቀደም ብለን አይተናል:: እናም መሐመድ ከእነዚህ የፓጋን ዐረቦች ሃይማኖታዊ ሥርዓት ውስጥ አንዳንዶቹን አሁንም ላለው እስልምና መሠረት አድርገዋቸዋል:: ለምሳሌ በእስልምናው አሁን እንደ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከሚደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ወደ መካ ሄዶ በፊት የጣኦታት ቤት የነበረውን ካዕባን እንዲሳለሙና እርሱንም ሰባት ጊዜ እንዲዞሩ ማድረግ ነው:: ጾማቸውንም ቢሆን ከፓጋን ዐረቦች የጾም ሥርዓት በተወሰነ ምልኩ ነው ማሻሻያ ያደረጉበት:: ሌላው መሐመድ ከፓጋን ዐረቦቹ ባዕድ አምልኮ ውስጥ በዋናነት የወረሱት ነገር እነርሱ ከሁሉም የበላይ አድርገው የሚያመልኩትን «አላህ» የሚባለውን የጣኦት ስም ነው:: ይህንን ቀጥሎ ባለው ርዕስ ላይ በደንብ እናየዋለን::

<u>መሐመድ አምላካቸውን ፈጠሩ</u>:- ከመሐመድም መነሳት በፊት በቅድመ እስልምና ዘመን በአረቢያ ምድር በካዕባ ውስጥ ጣኦታትን ያመልኩ የነበሩ ፓጋን አረቦችም «አላህ» የሚለውን ስም ለጣኦታቸው የግል መጠሪያ ስም አድርገው ይጠቀሙበት እንደነበር ብዙ ማስረጃዎች አሉ:: ፓጋን ዐረቦቹ በካዕባ ካሉ አማልእክቶቻቸው መሀል የበላይ አድርገው የሚያስቡትን አምላክቸውን «አል-ረሂም» ማለትም ሩህሩህ የሆነ ጌታ ብለው ይጠሩታል:: እንዲሁም «አል-ረህማን-አን» ማለትም መሀሪው ጌታ በሚባል ሌላ ስያሜም ይጠሩታል:: «አላህ» በሚለው ስያሜ የሚታወቀው ጣኦት በእነዚህ ስሞቹም ይጠራ ነበር:: በአሁኑም እስልምና «ለአላህ» 99 የተለያዩ ስሞች አሉት:: ቁርአኑ በሱረቱ አል-ኢስራእ 17፡110 ላይ *"አላህን ጥሩ፤ ወይም አልረህማንን ጥሩ፤ ከሁለቱ ማንኛውንም ብትጠሩ መልካም ነው፤ ለእርሱ መልካም ሰሞች አሉትና በላቸው"* ተብሎ ነው የተጻፈው:: ከመሐመድ መነሳት በፊት ፓጋኖቹ በወቅቱ በካዕባ ካሉ አማልእክቶቻቸው መሀል የበላይ አድርገው የሚያስቡትንና አል-ረሂም (ሩህሩህ)፣ አል-ረህማን (መህሪው)፣ አላህ... እያሉ በተለያየ ስም የሚጠሩትን አምላክቸውን የሰው ልጆች ሁሉ ባሕርያት እንዳሉት ያስቡ ነበር:: እርሱ ሕይወት እንደሰጣቸውና በይቅርታም እንደሚያኖራቸው ያምናሉ:: የሚታይና የሚዳሰስ አምላክ እንደሆነም ስለሚያስቡ ሀውልት አቁመውለት ነበር:: ሦስት ልጆችም እንዳሉት ስለሚታሰብ በካዕባ ውስጥ ሀውልቱ ቆሞለት የነበረው ከሦስት ልጆቹ ጋር ነበር::
መሐመድም በተነሡ ጊዜ ይህንን የካዕባ የ360 ጣኦታት አምልኮ ወደ አንድ አምልኮ ሥርዓት ነው የለወጡት:: የእርሳቸው ጎሳ አባላት

የሆኑት ቁራይሾች ከእነዚህ ጣኦታት ውስጥ የሚያመልኩትንና ከሁሉም የበላይ ተድርጎ የሚታሰበውን አላህን «የሁሉም የበላይ ስለሆነ እርሱን አምልኩ» በማለት ለሕዝቡ መስበክ ጀመሩ፡፡ ይህንንም ጥንታዊ የሆኑት የታሪክ መዛግብት ብቻም ሳይሆኑ ቁርአኑም ራሱ ያረጋግጥልናል፡፡ አራት ቁጥሮች ብቻ ያሉት 106ኛው ምዕራፍ እንዲህ ይላል፡፡ *«ቁረይሽን ለማላመድ ባለዝሆኖቹን አጠፋ፡፡ የብርድንና የበጋን ወራት ጉዞ ሊያላምዳቸው ይህንን ሠራ፡፡ ስለዚህ የዚህን ቤት የካዕባን ጌታ ይገዙ፡፡ ያንን ከረኃብ ያበላቸውን ከፍርሃትም ያረካቸውን ጌታ ይገዙ»* በማለት ቁርአኑ እንደመሰከረው መሐመድ እነዚያን 360 ጣኦታት አጥፍተው ነው በመጨረሻ አንዱንና የእርሳቸው ወገን ያመልኩት የነበረውን ብቻ አስቀርተው ነው ለአንድ አምላክ ተገዙ ያሏቸው፡፡ መሐመድ በተነሡና መካ ከተማን በኃይል በተቆጣጠረ ሰዓት የካዕባን 360 ጣኦታት ደምስሰው ሲያጠፉ ከሁሉም የበላይ ነው ተብሎ የሚታሰበውን «አላህ» የሚባለውን ጣኦት ግን ትተውታል፡፡ ይህም በሐዲሱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ቡኻሪ ሐዲስ ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- "ነቢዩ መካን በተቆጣጠራት ሰዓት ወደ መካ ሲገባ 360 ጣኦታት በካዕባ ዙሪያ ነበሩ፤ ነቢዩም በረጅም ዱላ ይመታቸው ጀመር፡፡" "When the Prophet entered Mecca on the day of the Conquest, there were 360 idols around the Ka'aba. The Prophet started striking them with a stick." (Sahih Bukhari: 5:59:583) ለመሆኑ መሐመድ ሁሉንም 360 የካዕባ ጣኦታን በዱላ ጨፍጭፈው ሲያጠፉ ለምን «አላህ» የሚባለውንስ ጣኦት አላጠፉትም? ቢባል ስለ ሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንድም የመሐመድ ነገድ የነበሩት የቁራይሽ ነገዶችና ቤተሰቦቻቸውና ራሳቸው መሐመድም ጭምር ያመልኩበት የነበረ የጣኦት ስም ስለሆነ ነው፡፡ 2ኛው ምክንያት ደግሞ ፓጋን ዐረቦች በካዕባ ውስጥ ያሉ ጣኦታትን ሁሉ ሲያመልኩ «አላህ» የሚባለውን ከሁሉም የበላይ አድርገው ያስቡ ስለነበር «የምታውቁትን፣ የምታመልኩትንና ከሁሉም የበላይ የሆነውን አምላክ አከበርኩላችሁ» ብለው ታማኝነትና ተቀባይነት ለማግኘት ነው፡፡ አሁን ደግሞ ሦስቱ የአላህ ልጆች የተባሉትን ጣኦታት በደንብ እንያቸው፡፡ በፓጋን ዐረቦቹ ዘንድ ሦስቱ የአላህ ልጆች የሚባሉት በስም አል-ላት፣ አል-ዑዛና መናት እንደሚባሉ በቁርአኑ ሱረቱ አል-ነጅም 53፡19 ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ *«አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (1) አያችሁን? የምትገዟቸው ኃይል አላቸውን? ለእናንተ ወንድ ለእርሱም ሴት ልጅ ይኖራልን? ይህቺ ያን ጊዜ አድላዊ ክፍያ ናት፡፡ እነርሱ፣ እናንተና አባቶቻችሁ አማልክት ብላችሁ የጠራችኋቸው ስሞች ብቻ እንጂ ምንም አይደሉም፡፡ አላህ በእርሷ መገዛት ምንም ማስረጃ አላወረደም»* ይላል ቁርአኑ፡፡ እንዲሁም በቁርአኑ ላይ በሌላ ቦታ «ለአል-ረህማን ልጅ የለውም እንጂ ቢኖረው እኔ ለልጁ የተገዢዎቹ መጀመሪያ ነኝ በላቸው» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ 43፡81

(1) ተብሎ በተቀመጠው የግርጌ ማስታወሻ ላይ "እነርዚህ ሦስቱ የጣዖታት ስሞች ናቸው" ተብሎ ተጽፏል፡፡

የመካ ሕዝቦች መሐመድን መጀመሪያ አካባቢ የጣኦቶቻቸውን ስም እየጠሩላቸው ስላስተማሩ በደስታ ይሰሟቸው ነበር፡፡ መጀመሪያ ላይ እንደተነሡ ስለ ጣኦቶቻቸውም ጥሩና መልካም ነገሮችን መናገር ቢጀምሩም ቆይተው ግን «እነርሱ አያስፈልጉም ዋናውንና አምሳያ የሌለውን አላህን ብቻ አምልኩ» እያሉ መስበክ ሲጀምሩ በተቃውሞ ተነሱባቸው፡፡እንዲያውም እንደነ አል-ዋሊድ ቢ.አል-ሙግሂራ ዓይነት ያሉ ሽማግሌዎች ቆሻሻና የግመል ፈርስ በመሐመድ ፊት ላይ ይደፉባቸው ጀመር፡፡ ከዚያ በኋላ የመካ ሕዝቦች በመሐመድ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ አጠናክረውባቸዋል፡፡ ትምህርታቸውንም «እኛ ቀድሞ የምናውቃቸው ተረቶች ናቸው» ይሏቸው እንደነበር ቀደም ብለን በገጽ----ላይ አይተናል፡፡ በቁርአኑ 109፡2 ላይ *«እናንተ ከሓዲዮች ሆይ ያንን የምትገዙትን ጣኦት አሁን አልገዛም፡፡ እናንተም እኔ የምገዛውን አምላክ አሁን ተገዢዎች አይደላችሁም፣ ወደፊትም ተገዢዎች አይደላችሁም»* በማለት ነው መሐመድ ይህንኑ ተቀባይነት ያጡበትን ክስተት የገለጹት፡፡ መሐመድም ወገኖቹ የመካ ነዋሪዎች እንዳልተቀበሏቸው ሲያውቁ ወደ እናታቸው ትውልድ ሀገር መዲና በ622 ዓ.ም ተሰደዱና በዚያ ኃይል አሰባስበው በመምጣት ነው መካን የተቆጣጠሯት፡፡ የፓጋን ዐረቦቹ ከሁሉ በላይ የሆነውና የዋናው አምላካቸው የፅንሰ ሀሳቡ መነሻ ጨረቃና ፀሐይ ናቸው፡፡ ቁርአኑ 91፡1 ላይ ገና ሲጀምር «በፀሐይና በጨረቃ እምላለሁ» ይላል፡፡ በጣም አስገራሚ በሆነ መልኩ ብዙዎቹ የቁርአን ምዕራፎች የሚጀምሩት በዚህ «በፀሐይና በጨረቃ እምላለሁ» በሚለው ቃለ መሀላ ነው፡፡ እንደ ፓጋን አረቦቹ እምነት የፀሐይ አምላክ ሴት አምላክ ስትሆን የጨረቃ አምላክ ደግሞ የወንድ አምላክ ነው፡፡ «አላህ» የሚለው ስም ደግሞ የጨረቃው አምላክ የግል መጠሪያ ስሙ ነበር፡፡ ስለዚህ የፀሐይና የጨረቃ አምለክ ማለትም ሴቷና ወንዱ ተጋብተው ሦስት ሴት ልጆችን ማለትም አል-ላትን፣ አል-ዑዛንና መናትን ወለዱ፡፡ ይህ ግልጽ የሆነ የፓጋን ዐረቦች እምነት ነው፡፡ ለእያንዳንዳቸውም ቤተ መቅደስ ሰርተው ጣኦት አቁመውላቸው ነበር፡፡ ይህ ነው እንግዲህ መሐመድን በቁርአኑ ላይ "አላህ ሴት ልጅ የለውም" ብለው እንዲናገሩ ያደረጋቸው ነገር፡፡



The moon-god from all four sides. Note the cresent moon carved on his chest.

ከላይ ያለው ስዕል በአራቱም አቅጣጫ የሚያሳየው የወንዱን የጨረቃ አምላክ ሃውልት ነው። በደረቱ ላይ የጨረቃዋ ምስል መኖሩን አስተውሉ። ቀጥሎ ያለው ስዕል ደግሞ ከአላህ ሴት ልጆች ውስጥ አንደኛዋ የአል-ኡዛ /Al-Uzza/ እና የቤተ መቅደሷ ሃውልት ነው።



አል-ኡዛ /Al-Uzza/ ማለት በቁራይሾች ዘንድ ከሌሎቹ የአላህ ልጆች በተለየ ሁኔታ ከዋናው አምላካችን ታስታርቀናለች ተብሎ የሚታመንባት ነበረች። ራሳቸው መሐመድ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከጎሳቸው ጋር ሆነው በለየ ሁኔታ ያለምኩባትና መሥዋዕት ይሠውላት ነበር። እንዳውም ከመሐመድ አጎቶች ውስጥ አንደኛውና አሳዳጊው በእርሷ ስም የተሰየመ ነበር። ሙሉ ስሙ አብድ አል-ኡዛ (Abd al-uzza) ሲባል በጓላ ነው በቅጽል ስሙ አቡ ላሀብ እየተባለ መጠራት የጀመረው።

«የፀሐይና የጨረቃ አምለክ (ሴቷና ወንዱ) ተጋብተው ሦስት ሴት ልጆችን ወለዱ» የሚለው ግልጽ የሆነ የፓጋን ዐረቦች እምነት በመሐመድ ላይ ምን ያህል ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው የሚታወቀው ይህንን አስከፊ የሆነ የፓጋኖችን እምነት ወደ ክርስትናውም ሊያመጣው መሞከሩ ነው። መሐመድም ሆነ ቁርአኑ ወይም አሁንም ያሉት ሙስሊም መምህራን በክርስትናው «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለውን አስተምህሮ እጅግ አሳዛኝና አስቂኝ በሆነ መልኩ ነው የሚረዱትና የሚተረጉሙት። ማለትም «የእግዚአብሔር ልጅ አለው» ሲባል በሰው ሰውኛ ግብር እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርጎ የወለደው መስሎ ነው የሚታያቸው። “ለእርሱ (ለአላህ) ሚስት የሌለችው ሲሆን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል” /ሱረቱ አል-አንዓም 6፡101/ በማለት ቁርአኑ ይሞግታል። በሌላም ቦታ ቁርአኑ “እነሆ የጌታችን ክብር ላቀ፤ ሚስትንም ልጅንም አልያዘም” /ሱረቱ አል-ጂን 72፡3/ በማለት የእግዚአብሔርን የልጅነት ምሥጢር በግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደተገኘ አድርጎ ሲያቀርበው ትንሽ እንኳ ትዝብት ውስጥ እገባለሁ ብሎ አለማፈሩ እጅግ አስገራሚ ነው በእውነት። እንደ እውነቱ ከሆነ እንኳን ክርስቲያኖቹ ሰይጣንም እንደዚያ ብሎ አያምንም። መሐመድም ሆኑ አሁን ያሉት ተከታዮቻቸው ቢያንስ ክርስቲያኖቹ ምን ብለው ነው የሚያምኑት? የሚለውን ነገር እንኳን አጣርተው አለማወቃቸው ምን ያህል ትዝብት ውስት እንደጣላቸው ተመለከቱ!

<u>አላህ-የሚለው የቃሉ ትርጉም</u>፡- ከላይ እንዳየነው ቁርአኑ በሱረቱ አል-ኢስራእ 17፡110 ላይ “አላህን ጥሩ፤ ወይም አልረሕማህንን ጥሩ፤ ከሁለቱ ማንኛውንም ብትጠሩ መልካም ነው፤ *ለእርሱ መልካም ሰሞች* አሉትና በላቸው” ተብሎ ነው የተጻፈው። "Say, Call Him Allah or call Him Ar-Rahman; whatever the name you call Him, all His names are beautiful." (Qur'an 17:110)

በዚህ ጥቅስም ሆነ በሌሎች የቁርአን ጥቅሶች ላይ “አላህ” የሚለው ቃል በራሱ «የመጠሪያ ስም» ብቻ መሆኑን ነው የሚያለመክተው፡፡ ቁርአኑ በግልጽ «አላህን ወይም አልረሕማህንን ጥሩ... ለእርሱ መልካም ስሞች አሉት» ካለ “አላህ” የሚለው ቃል በራሱ «አላህ» በመባል የሚጠራ የአንድ አካል የመጠሪያ ስም ብቻ መሆኑን ነው እንጂ የአምላክነቱ ወይም የባሕርይው መገለጫ ስያሜ አይደለም፡፡
በእስልምናው አንድ ሰው መጀመሪያ ሙስሊም መሆኑ የሚታወቀው በዐረብኛ “አላሁ አክበር! ላ ኢላሃ ኢል አላህ መሐመድ ራሱል አላህ” ብሎ በሚያሰማው የምስክርነት ቃል ነው፡፡ በእነርሱ ሸሀዳ (ምስክርነት) ይሉታል፡፡ ትርጉሙም “አላህ ትልቅ ነው፤ ከአላህ በቀርም ሌላ አምላክ የለም፤ መሐመድም መልእክተኛው ነው” ማለት ነው፡፡ “ላ ኢላሃ ኢል አላህ” የምትለዋን ቃል በደንብ ማየት ስለፈለኩ ነው ይህን ያነሳሁት፡፡ “ላ ኢላሃ ኢል አላህ” /La ilaha illAllah/ የሚለው የአረብኛ ቃል ትርጓሜው “ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም” የሚል ትርጓሜን የሚሰጥ ይመስላል፡፡ ግን አይደለም፡፡ ይህንን ቀጥሎ ያለውን ትርጓሜ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡- La [no] ilaha [god] ill [except] Allah [Allah]. ይህም “አላህ” የሚለው ቃል በራሱ የመጠሪያ ስም ብቻ መሆኑን ነው የሚያመለክተው እንጂ የአምላክነቱ ወይም የባሕርይው መገለጫ ስያሜ አለመሆኑን አይተናል፡፡ ይህንንም የእንግሊዝኛው ፊደል የበለጠ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ በእንግሊዝኛ አምላክ የሚለውን ቃል ለመግለጽ በትልቁ ፊደል በ"G" ይጀምራል፡፡ በትንሹ ፊደል በ"g" ከጀመረ ግን የጣኦትን ስም ለመግለጽ ነው የሚያገለግለው፡፡ ስለዚህ የአረብኛው “ilaha” የሚለው ቃል የሚወክለው «God» የሚለውን ሳይሆን «god» የሚለውን ቃል ነው፡፡ ይህ “ilaha” የሚለው ቃል የተጠቀሰው ከመሐመድ መነሳት በፊት በካዕባ ይመለኩ የነበሩ ጣኦታን ለመግለጽ ነው፡፡ ስለዚህ “ላ ኢላሃ ኢል አላህ” /La ilaha illAllah/ ለሚለው የዐረብኛ ቃል “ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም” የሚለው ትርጉም ቀጥተኛና ተዛማጅ የሆነ ትርጓሜው አይደለም፡፡ የአረብኛው “ilaha” የሚለው ቃል ትርጓሜው ጣኦት /god/ ማለት ሲሆን «አላህ» የሚለው ቃል ደግሞ የግል መጠሪያ ስሙ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ዐረብኛው ቃል መነሻ ሀሳብና አገባብ ከሆነ “ላ ኢላሃ ኢል አላህ” La [no] ilaha [god] ill [except] Allah [Allah] የሚለው የዐረብኛ ቃል ትክክለኛ አገባቡ “ካሉት ጣኦታት ውስጥ አላህ ብቻ እንጂ ሌሎች ጣኦታት ሊመለኩ አይገባም” የሚል ነው፡፡ የቃሉን አውዳዊ አገባቡ /contextual meaning/ በትክክል የሚያሳየን ይህንን ብቻ ነው፡፡
መሐመድ የካዕባን ባዕድ እምነት አጥፍተው «አላህን» ብቻ ለይተው ለሕዝቡ ያስተዋወቁበትን መንገድ እንዲህ ባለ መልኩ ካየን አሁን ደግሞ «የመሐመድን አጠቃላይ የሕይወት ጉዞውን መመልከታችንን ለጊዜው ትንሽ ገታ ላድርገውና በኋላ ስለምእመለስበታለሁ» ወዳልኩት ሀሳብ ልመለስ፡፡ መሐመድ በ5ኛ ዓመት ስብከታቸው ተከታዮቻቸው እስከ 70 በደረሱ ጊዜ ነው ፓጋን ዐረቦችን ፊት ለፊት በግልጽ መዋጋት የጀመሩት፡፡ ሰላማያዊ በሆነ መልኩ ማስተማሩ እንዳላዋጣቸው ሲያውቁ ሰይፍን እንደዋነኛ የእምነታቸው ማስፋፊያ መሳሪያ አድርገው ተጠቀሙበት፡፡ መጀመሪያ ያደረጉት ነገር የቅርብ ዘመዶቻቸውን ከመካ ከተማ አስወጥተው ጥገኝነት የሚያገኙበትን ሀገር ሲያስብ የአቢሲኒያው (የኢትዮጵያው) ንጉሥ ማንኛውንም እንግዳ የሚያከብር እንዲሁም ሃይማኖቱና ምግባሩ ነቅ የሌለበት ደግ ንጉሥ መሆኑን ቀደም ብለው ሰምተው ነበርና ዘመዶቻቸውን «እዚያ ሂዱ ሰላም ታገኛላችሁ» በማለት ወደ አቢሲኒያ ላኳቸው፡፡ ይህም የሆነው በ615 ዓ.ም ሲሆን የላኳቸውም ሴት ልጃቸውን ሩቂያን ጨምሮ ባሏን ኦትማን ኢብን አፋንን የሌሎች 10 ሰዎች መሪ አድርገው ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንደደረሱም በመካ ያሉ ከመሐመድ ጋር ጦርነት ውስጥ የገቡት ቁራይሾች ተከታትለዋቸው የመጡ ቢሆንም ንጉሡ አሳልፎ ሳይሰጣቸው ቀርቷል፡፡
መሐመድ ከዚህ በኋላ እነዚህን 70 የመጀመሪያ ተከታዮቻቸውን በጥቅማ ጥቅም መያዝና ለተቃውሞም ብቁ ከማድረግ አኳያ እንደመፍትሄ የወሰዱት እርምጃ የመካ ካራቫን ነጋዴዎች ወደ ተለያዩ ሀገራት ለንግድ ሲሄዱ እነርሱን ጠብቆ መዝረፍን ነበር፡፡ እንዳሰቡትም ተግባራዊ አደረጉትና መሐመድ ራሳቸውንና ተከታዮቻቸውን በጦር መዝረፍንና ጂሃድ ማወጅን አስጀመሯቸው፡፡ በድርጊቱም የሚገኘውን ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ አጣጣሙ፡፡ ተከታዮቻቸውም በመጀመሪያዋ ዘረፋ ባገኙዋት ንብረት ተነሳሽነታቸውም ሆነ ቁጥራቸው በጣም እየጨመረ መጣ፡፡ (ከሃይማኖታቸው ማስፋፋት ጎን ለጎን የተለያዩ ዝርፊያዎችን እንዴት አድርገው ይፈጽሙ እንደነበር ዝርዝር ሁኔታዎችን በኋላ ላይ እናያለን)

መሐመድ በ622 ዓ.ም ተከታዮቻቸውን ይዘው ከመካ ወደ መዲና ተሰደዱ፡፡ ሙስሊሞች ዘመናቸውን አንድ ብለው የሚቆጥሩት ከዚህ ዓመት ጀምሮ ነው፡፡ መዲና ከመካ ከተማ በስተሰሜን 250 ማይልስ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ስትሆን በወቅቱ በዋናነት 5 የተላያዩ ጎሳዎች ይኖሩባት ነበር፡፡ እነዚህም ባኑ ቃይኑቃ፣ ባኑ ናድህር፣ ባኑ ቁራይዛ የተባሉት ሦስቱ የአይሁድ ጎሳ አባላት ናቸው፡፡ የተቀሩት ሁለቱ ጎሳዎች ካዝራጅና አውስ የተባሉ ፓጋኖች ሲሆኑ እነዚህ መሐመድን ወዲያው ነው የተቀላቀሏቸው፡፡ ምክንያቱም የአይሁዶቹ ጎሳዎች የተለያዩ የዕደ ጥበብ ሥራዎችን በመሥራትና ያትሪብ በሚባለው ቦታ ላይ የግብርና ውጤቶችን በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቀም የተሻለ የኑሮ ደረጃ ስለነበራቸው፣ የእነርሱንም ልጆች ብቻ ለይተው የሚያስተምሩበትም ት/ቤት ስለነበራቸው እነርሱንም ለማጥቃት ሲሉ ፓጋኖቹ መሐመድን በፍጥነት ነበር የተቀበሏቸው፡፡ መሐመድም ጂሃድ አውጀውባቸው ያሰለሙትን አስልመው እምቢ ያላቸውን ሰይፈው ንብረት፣ ሴቶችና ሕጻናቶቻቸውን በምርኮ ወስደው ለራሳቸውና ለተከታዮቻቸው አከፋፍለዋቸዋል፡፡ ከሁሉም አስከፊ የነበረውና እኔም ብዙ ቦታ ላይ የጠቀስኩት 900 የሚሆኑ የባኑ ቁራይዛዎች ጅምላ ጭፍጨፋ ነው፡፡ አልሳካላቸው አለ እንጂ መሐመድ

እነዚህን በመዲና የሚኖሩትን የአይሁድ ጎሳዎች መጀመሪያ አስተምረው ለማሳመን ብዙ ሞክረው ነበር። ለማሳመንም ሲሉ አንዳንድ የአይሁዶችን ሥርዓተ እምነቶች በመሠረቱት አዲሱ እምነታቸው ውስጥ እንዲካተቱ አድርገውላቸው ነበር። ለምሳሌ፡- ለአብርሃም ብቻ የተሰጠውን የግዝረትን ሥርዓትና ትእዛዝ ሙስሊሞችም እንዲተገብሩት አዘዙ። ሌላው እነ መሐመድ በመካ እያሉ የሚሰግዱት ወደ ቤተ-ጣኦቱ ወደ ካዕባ ዞረው ነበር። አሁን ግን መሐመድ ልክ እንደ አይሁዶቹ ወደ ኢየሩሳሌም ዞረው እንዲሰግዱ አዘዙ። እነዚህንና ሌሎችም ሥርዓተ እምነታቸውን ወደ እስልምናው በመውሰድ አንድ ሊያደርጓቸው ቢሞክሩም ከሁለቱ ፓጋን ዐረቦች በቀር አይሁዶቹ አልቀበል ስላሏቸው እነርሱ ላይ ጂሃድ አውጀው ድል ካደረጓቸው በኋላ የጸሎትና ስግደት አቅጣጫውንም መልሰው ወደነበረበት ወደ መካ እንዲሆን አድርገውታል። ቅዳሜ የነበረውን የአይሁድ የሰንበት በዓል መጀመሪያ የተቀበሉት ቢሆንም በጦርነት ካሸነፏቸው በኋላ ግን «ቅዳሜ ሳይሆን አርብ የሙስሊሞች ቅዱስ ቀን ይሁን» ብለው ነቢያቸው አወጁ። ይህም «መሲሁ ኢየሱስን በዚህ ዕለት አይሁድ ሰቀሉት» ብለው መከራውን እያሰቡ የሚውሉትን ሌሎች ክርስቲያኖችን ለመቃወም ሲሉ ያደረጉት ነገር ነው እንጂ መሐመድ ዕለተ አርብን «ልዩና ቅዱስ ቀን» አድርገው እንዲከበሩ የሚያዙበት ሌላ ምንም ምክንያት አልነበራቸውም። በሐዲሱም ላይ በግልጽ ተጽፎ እንደምናነኘው ከአይሁድና ከክርስቲያኖች ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ማድረግ እንዳለባቸው መሐመድ ለተከታዮቻቸው አስተምረዋቸዋል። ለምሳሌ፡- አይሁድና ክርስቲያኖች ጸጉራቸውን ቀለም ስለማይቀቡ በመሐመድ ትእዛዝ መሠረት ሙስሊሞች ከክርስቲያኖቹ በተቃራኒው ጸጉራቸውን ቀለም መቀባት እንዳለባቸው ተነግሯቸዋል። “The Prophet said, "Jews and Christians do not dye their hair so you should do the opposite of what they do.” Sahih Bukhari 7:72:786. አሁን ደግሞ እስቲ መሐመድ «ከሰማይ ወረደልኝ» ስላሉት ቁርአን አንዳንድ ነጥቦችን ላንሳላችሁ። ከዚህ ርዕስ ልጀምር፡-

<u>አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ማን ነው</u>? (Abd Allah Ibn Sa`d Ibn Abi Sarh and verse 6:93)

በአማኞቹ እንደሚታሰበው ከሆነ ቁርአኑ በቀጥታ ከሰማይ በአላህ ዘንድ ካለው መዝገብ ተቀድቶ በጂብሪል በኩል ለመሐመድ የመጣላቸው መገለጥ ነው። ይህም በ23 ዓመታት ውስጥ በየጊዜው ነው ለመሐመድ ሲገለጥላቸው የነበረው። በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ቁርአኑ እንደሚያረጋግጠው መሐመድ ምንም ስላልተማሩ ማንበብና መጻፍ እንኳን አይችሉም ነበር። እነዚህንና ሌሎችንም ነገሮች ታሳቢ በማድረግ ሙስሊሞች ሊሰሟቸውና ሊጠየቁ የማይፈልጓቸውን እጅግ በርካታ ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን።

መሐመድም ማንበብና መጻፍ ካልቻሉ ታዲያ እንዴት በየጊዜው የመጡ እነዚያን የ23 ዓመታት መገለጦች ዛሬ በአንድ ላይ ተጠርዘው በቁርአን መልክ ልናገኛቸው ቻልን? መሐመድ ከሞቱ በኋላ ነውና የተሰበሰቡት በአንድ ላይ ጠርዞ ያዘጋጃቸውስ ማን ነው? ያሰባሰቡ ሂደትስ እንዴትና ምን ይመስል ነበር? መሐመድ ራሳቸው «ተገለጠልኝ» ያሉበት መንገድስ አግባብ ነው? ማለትም የሆነ አንድ አካል (መሐመድ መልአኩ ጂብሪል ነው ያሉት) እርሳቸውን ወደ ሂራ ተራራ ጫፍ ላይ ወስዶ በአፍ በአፍጫቸው አረፋ እስኪደፍቁ ድረስ መሬት ላይ ጥሎ እያሰቃየ መገለጦቹን እንደሰጣቸው ሐዲሱ ይናገራል። (ዝርዝሩን በመጀመሪያዎቹ ገጾች ላይ በስፋት ስላየነው ከዚያ ላይ ይመልከቱ) ታዲያ ከእውነተኛ አምላክ የሚመጣ መገለጥ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ መሆን ነበረበት? ይህንን ተከትሎ በተፈጠረባቸው ስሜት መሐመድ ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ሊያጠፉ ሞክረው እንደነበር አሁንም ሐዲሱ ይመሰክራልና መሐመድ ለምን ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ሊያጠፉ ሞከሩ? እስልምና በመላእክትና በነቢያት ያምናል። ለመሆኑ ለየትኛው ነቢይ ነው መላእክት በእንደዚያ ዓይነት ሁኔታ የተገለጡለት? የአምላክስ ቅዱስ መንፈስ ለነቢይ በእንደዚያ ዓይነት መንገድ መምጣት ነበረበት? የቁርአኑንስ ይዘት ልብ ብላችሁ ካያችሁት በውኑ ከሰማይ የመጣ ይመስላል? ማለትም በውስጡ ያሉት የታሪክ መፋለሶች፣ የጀመረውን ያለመጨረስ ችግርና የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሕግን አለመጠበቅ (grammatical errors) እነዚህና ሌሎቹም ስሕተቶቹ የእውነት ከሰማይ የመጣ ያስመስሉታል? ታሪኩን ጠለቅ ብላችሁ የምታውቁት ሙስሊሞችስ የመሐመድ የግል ጸሐፊው ስለነበረው ሰው ስለ አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ምን የምትሉት ነገር አለ?

ቀጥሎ የምንመለከተው የእነዚህንና የሌሎችንም ጥያቄዎች መልስ ነው። በመጀመሪያ አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ማን ነው? የሚለውን እንይ፡- አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ማለት የመሐመድ የግል ጸሐፊው የነበረ ሰው ነው። በቁርአኑ ሱረቱ አል-አንዓም 6፡93 ላይ እንዲህ በማለት ተጽፏል፡- “በአላህም ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያልወረደለት ሲሆን ወደኔ ተወረደልኝ ካለና አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?” ይላል ቁርአኑ። ይህ አነጋገር ከመሐመድ ሌላ ቁርአንን ወረደልኝ የሚል ሰው ሊኖር ስለመቻሉ ነው በግልጽ የሚናገረው። ይህ ሰው ደግሞ መሐመድ ቁርአንን እንዲጽፉላቸው ካደረጓቸው በርካታ ሰዎች ውስጥ አንዱ የሆነው አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ የሚባለው ሰው ነው። በኋላ ላይ መሐመድንም ሆነ እምነታቸውን ትቶ ከመዲና ወደ መካ ተመልሶ ሄዶ ነበር። መሐመድም ጸሐፊያቸው ተፈልጎ እንዲገደል ትእዛዝ አስተላልፈውበት ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ አብደላህ አብድ አል-ፋዲ ተባለው ጸሐፊ “Is the Qur'an Infallible?” ማለትም “ቁርአን እንከን የለሽ ነውን?” በሚል ርእስ በጻፈው ጽሑፍ ላይ የሚከተለውን አስፍሯል፡- “የመሐመድ ጸሐፊዎች በቁጥር 42 ነበሩ። አብደላህ ኢብን ሳርህ አል-አሚሪ ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ነበር። እስልምናን ትቶ ከመሄዱ በፊት መካ ውስጥ ከጻፉት መካከል እርሱ

የመጀመሪያው ቁራይሽ ነው፡፡ እንዲህም ይል ነበር፡- ‘መሐመድን እኔ ወደፈለኩበት እመራው ነበር፡፡ ‘በጣም የላቀ’፣ ‘ሁሉን አዋቂ’ እያለ በቃል ያጽፈኛል፤ እኔም ‘በጣም የላቀ’ የሚለውን እተውና ‘ሁሉን አዋቂ’ የሚለውን ብቻ እጽፍ ነበር፡፡ እርሱም ‘አዎ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ነው፤ ይህንና ይህን የመሳሰለውን ጻፍ’ ይለኛል፡፡ ነገር ግን እኔ ‘ጻፍ’ የሚለውን ቃል ብቻ ነበር እጽፍ የነበረው፡፡ ‘የፈለከውንም ጻፍ’ ይለኝ ነበር’” በማለት አብደላህ ኢብን ሳርህ ተናግሯል፡፡ በዚህም ሁኔታ መሐመድን ሲያጋልጠው መሐመድ ቁርአን ላይ “ወደርሱ ምንም ያልወረደለት ሲሆን ወደኔ ተወረደልኝ ካለና አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?” የሚል ጥቅስ አጻፈ፡፡ “ስለዚህም መሐመድ መካን በተቆጣጠረ ጊዜ ጸሐፊው የነበረውን አብደላህ ኢብን ሳርህን እንዲገደል ትእዛዝ ሰጥቶበታል” በማለት አብደላህ አብድ አል-ፋዲ ተባለው ጸሐፊ በሰፊው አብራርቷል፡፡ “The scribes of Muhammad were 42 in number. `Abdallah Ibn Sarh al-`Amiri was one of them, and he was the first Quraishite among those who wrote in Mecca before he turned away from Islam. He started saying, "I used to direct Muhammad wherever I willed. He would dictate to me 'Most High, All-Wise', and I would write down 'All-Wise' only. Then he would say, 'Yes it is all the same'. On a certain occasion he said, 'Write such and such', but I wrote 'Write' only, and he said, 'Write whatever you like.'" So when this scribe exposed Muhammad, he wrote in the Qur'an (6:93), "And who does greater evil than he who forges against God a lie, or says, 'To me it has been revealed', when naught has been revealed to him." So on the day Muhammad conquered Mecca, he commanded his scribe to be killed. But the scribe fled to `Uthman Ibn `Affan, because `Uthman was his foster brother (his mother suckled `Uthman). `Uthman, therefore, kept him away from Muhammad. After the people calmed down, `Uthman brought the scribe to Muhammad and sought protection for him. Muhammad kept silent for a long time, after which he said yes. When `Uthman had left, Muhammad said "I only kept silent so that you (the people) should kill him." (Is the Qur'an Infallible? by `Abdallah `Abd al-Fadi, & Al-Sira by al-'Iraqi)

ሌላው ማወቅ ያለብን ነገር መሐመድ የረሷቸውን የቁርአን ጥቅሶች ሌላ ሰው ያስታውሳቸው የነበረ መሆኑ ነው፡፡ (Mohammed forget Quranic verses):- Allah’s Apostle heard a man reciting the Qur’an at night, and said, “May Allah bestow His Mercy on him, as he has reminded me of such-and-such Verses of such-and-such Suras, which I was caused to forget.” Sahih al Bukhari Volume 6, Book 61, Number 558.

አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ በእርግጥ መሐመድ መካን በተቆጣጠሩ ሰዓት ባሳደገው ወንድሙ ኦትማን ኢብን አፋን አስታራቂነት ከመሐመድ ጋር ታርቆ ወደ እስልምናም ተመልሷል፡፡ የጦር መሪና አዛዥም ሆኖ ተሹሞ በብዙ ጂሃዶች ላይ ተሳተፏል፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ላይ ማለትም መሐመድ መካን በተቆጣጠሩ ሰዓት መሐመድ እንዲገሉ ትእዛዝ ከሰጠባቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ኢብን አቢ ሳርህ ነበር፡፡ ይህንንም የአቡ ዳውድ ሀዲስ ዘግቦት ይገኛል፡፡ በሐዲሱ ዘገባ መሠረት መካ በቁጥጥር ስር በዋለችበት ዕለት መሐመድ ሊገድሏቸው ከሚፈልጓቸውና በስም ከጠቀሷቸው ከ4 ወንዶችና 2 ሴቶች በስተቀር ነዋሪዎቿ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ኢብን አቢ ሳርህም ከሚገደሉት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ “On the day when Mecca was conquered, the Apostle of Allah gave protection to the People except four men and two women and he named them. Ibn AbuSarh was one of them.” Abu Dawud 14:2677

ልብ በሉ የዚህን ጸሐፊ ታሪክ ቀደም ብለን ካየነው ከመሐመድ ታሪክ ጋር ብናነፃፅረው አንድ ነገር እንደ ማጠቃለያ መናገር እንችላለን፡፡ መሐመድ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ስለ ተለያዩ እምነቶች ሲተረክላቸው የሰሟቸውን ታሪኮች ሰብስበው ነው ለሰዎች በድጋሚ በሚፈልጉት መልኩ ሲያጽፉ የነበረው ማለት ነው፡፡ የቁርአኑን ይዘት በደንብ ስናስተውለው ይህ ምን ያህል እውነት መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ወደፊት በደንብ እናየዋለን ለአሁኑ ግን የጀመርነውን እንቀጥል፡፡ አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ የመሐመድን ሁኔታ ካየ በኋላ ከመዲና ወደ መካ ትቷቸው ሄዷል፡፡ ማለትም መሐመድ ሲፈልጉ «የፈለከውንና ደስ ያለህን ጨምረህ ጻፍ» ሲሉት በአንድ በኩል ደግሞ «ከሰማይ ወደረልኝ» እያሉ ለተከታዮቻቸው ሲያስተምሩ ሲያያቸው እየተደረገ ያለውን የሐሰት ሥራ ስለታዘበ መሐመድን «እንደዚህማ ከሆነ እኔም ነቢይ መሆንና ማስተማር እችላለሁ» ብሎ ጥሏቸው ጠፋ፡፡ መሐመድም ምስጢሬን ያወጣብኛል ብለው ስለፈሩ *“በአላህም ላይ አብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያልወረደለት ሲሆን ወደኔ ተወረደልኝ ካለና አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?”* (ሱረቱ አል-አንዓም 6:93) የሚለውን ጥቅስ በቁርአኑ ውስጥ በማካተት «የቁርአን መገለጦች የመጡልኝ ብቸኛው ሰው እኔ ነኝ» የሚል አንድምታ ያለው አዋጅ አወጁ፡፡

ኢብን አቢ ሳርህን ከመሐመድ ዘንድ በድብቅ ጠፍቶ እንዲሄድ ያስገደደው የመጨረሻው ክስተት የቁርአኑ 23ኛ ምዕራፍ ላይ ስለ ሰው አፈጣጠር የሚናገረው ነው፡፡ ሱረቱ አል-ሙእሚን 23:14 ላይ ከቁ.12 ጀምሮ ስለ ሰው አፈጣጠር መሐመድ ኢብን አቢ ሳርህን

ያጽፉታል፡፡ «በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው» ብሎ ይጀምርና «በተጠበቀ መርጊያ ካደረግነው በኋላ የስፐርም ሴል (የፍቶት ጠብታ) አደረግነው» ይላል፡፡ ከዚያም ስፐርም ሴሉ ወደ ረጋ ደምነት፣ የረጋው ደም ወደ ቁራጭ ሥጋነት፣ ቁራጩ ሥጋ ወደ አጥንትነት ከተለወጠ በኋላ አጥንቱን ሥጋ በማልበስ ሌላ ፍጥረት እንደተፈጠረ ቁርአኑ ይናገራል፡፡ ያ ሌላ ፍጥረት ደግሞ ሰው ሆነ፡፡ በዚህም አላህ ከሰዓሊዎች ሁሉ የበላይ እንደሆነ በመናገር ሰው የተፈጠረበትን መንገድ መሐመድ ከምድራዊ ሰዓሊ ጋር አነፃፅረውታል፡፡ ቀጥሎ ስካን (scan) የተደረገውን የቁርአኑን ጥቅስ ይመልከቱ፡፡

12 በእርግጥም ፣ ሰውን ፣ ከነጠረ ፣ ጭቃ ፣ ፈጠርነው ።

13 ከዚያም ፣ በተጠበቀ ፣ መርጊያ ፣ ውስጥ ፣ የፍቶት ፣ ጠብታ ፣ አደረ ግነው ።

14 ከዚያም ፣ ጠብታዋን ፣ (በአርባ ፣ ቀን) ፣ የረጋ ፣ ደም ፣ አድርገን ፣ ፈጠርን ፤ የረጋውንም ፣ ደም ፣ ቁራጭ ፣ ሥጋ ፣ አድርገን ፣ ፈጠ ርን ፤ ቁራጭዋንም ፣ ሥጋ ፣ አጥን ቶች ፣ አድርገን ፣ ፈጠርን ፤ አጥን ቶቹንም ፣ ሥጋን ፣ አለበስናቸው ፤ ከዚያም ፣ (ነፍስን ፣ በመዝራት) ፣ ሌላ ፣ ፍጥረትን ፣ አድርገን ፣ አስገ ኘነው ፤ ከሰዓሊዎችም ፣ ሁሉ ፣ በላጭ ፣ የኾነው ፣ አላህ ፣ ላቀ ።

በቅንፍ ውስጥ ያሉት (በአርባ ቀን፣ ነፍስን በመዝራት) የሚሉት ቃላት ትርጉም እንዲሰጡ በማሰብ ዘመናዊ ሙስሊም ምሁራን (Muslim scholars) በቅርብ ጊዜ የጨመሯቸው ቃላት ናቸው፡፡

የእውነት ሰው በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ተፈጥሯል ወይ? የሚልና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች ቢኖሩም አሁን ግን ጉዳዩ መሐመድን ከጸሐፊያቸው ጋር እንዴት ሊያጣላቸው እንደቻለ ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ መጨረሻ ላይ ያለውን ሀሳብ ማለትም ‹ከዚያ ሁሉ ሂደት በኋላ ሌላ ፍጥረት በመፈጠሩ አላህ ከሰዓሊዎች ሁሉ የበላይ ሆነ› የሚለውን የፅንሰ ሀሳቡን መቋጫ ጸሐፊው ኢብን አቢ ሳርህ ያልተነገረውን ነገር ከራሱ ሀሳብ አመንጭቶ ነበር የጨመረበት፡፡ በወቅቱም መሐመድ ሀሳባቸውን ስለጠቀለለላቸው በሆነው ነገር ደስተኛ ነበሩ፡፡ ይህቺ ክስተት ናት ለመጨረሻ ጊዜ ኢብን አቢ ሳርህን ከመሐመድ ተለይቶ እንዲጠፋና የግደሉት ትእዛዝ እንዲተላለፍበት ያደረገችው፡፡ እስካሁን ይህን ስለ ኢብን አቢ ሳርህ ያየነውን በሙሉ ራሳቸው የዐረብ ጸሐፊዎች ሳይቀሩ በጻፏቸው መጻሕፍቶቻቸው ላይ በደንብ መስክረዋል፡፡ ለምሳሌ ኢብኑ ሂሻምና ዛኪ አሚን የተባሉ ጸሐፊዎች በዐረብኛ በተከታታይ «አል-ሲራ አል-ናባዊያ» እና «አል-ሲራ አል-ሀላቢያ» በተባሉ መጽሐፎቻቸው ላይ ታሪኩን በደንብ ጽፈውታል፡፡ ለማሳያ ያህል ከኢብኑ ሂሻም «አል-ሲራ አል-ናባዊያ» መጽሐፍ ከገጽ 57 ላይ ስካን (scan) ተደርጎ ከዐረብኛው ጎን ለጎን የእንግሊዝኛውም ትርጉም የያለበትን ጽሑፍ ቀጥሎ ይመልከቱ፡፡



Al Sira Al Nabawiya, by Ibnu Hisham, Ch. IV, p. 57

٥٧ ذكر الأسباب الموجبة المسير إلى مكة وذكر فتح مكة

يقطعـنَ كـل سـاعـد وجُمجُمـة ضَـرْبـاً فـلا يُسْمَـع إلاّ غمغمـة[١]
لهـمْ نَهيـتٌ خلفَنَـا وهَمهَمَـة لم تنطقِي في اللوم أدنى كلمة[٢]

The prophet of Allah asked his commanders from Muslim army: when you enter Mecca don't fight or kill, kill only the people who fight you, but he asked to kill list of people in Mecca even if the are under the velvet of Kaaba , one of them was Ibn Sarh.

الطائف

وكان شِعار أصحاب رسول الله ﷺ يوم فتح مكة وحُنين والطائف، شعارُ المهاجرين: يا بني عبد الرحمن، وشعار الخزرج بني عُبيدِالله.

Why the prophet of Allah ordered to kill Ibn Sarh and how Ibn Affan saved his life - The prophet of Allah ordered to kill him because he was a Muslim, he was one of the Quran writers, he left Islam (Murtad) became None Muslim (kafar) and went back to Quraysh in Mecca, he escaped to his half brother Uthman Ibn Affan

عهد الرسول إلى أمرائه وأمره بقتل نفر سماهم

قال ابن إسحاق:

وكان رسول الله ﷺ قد عَهِدَ إلى أمرائه من المسلمين، حين أمرهم أن يدخلوا مكة، أن لا يقاتلوا إلا من قاتلهم، إلا أنه قد عَهِد في نفر سمّاهم أمر بقتلهم وإن وُجدوا تحت أستار الكعبة، منهم عبدالله بن سعد، أخو بني عامر بن لؤي.

[٥٢/٤] / سبب أمر الرسول بقتل سعد وشفاعة عثمان فيه

وإنما أمر رسولُ الله ﷺ بقتله لأنه قد كان أسلم، وكان يكتب لرسول الله ﷺ الوحي، فارتد مشركاً راجعاً إلى قريش، ففرّ إلى عثمان بن عفان، وكان أخاه

= خطيب قريش. والموتمة والموتم بلا همز، وتجمع على ميائم، وهي المرأة مات زوجها وترك لها أيتاما. وقال ابن إسحاق في غير هذه الرواية: «المؤتمة» الأسطوانة، وهو تفسير غريب، وهو أصح من التفسير الأول، لأنه تفسير راوي الحديث. وعلى قوله هذا يكون لفظ المؤتمة من قولهم: وتم، وأتم: إذا ثبت، لأن الأسطوانة تثبت ما عليها. ويقال فيها على هذا: مؤتمة بالهمز، وتجمع على مآتم، وموتمة بلا همز، وتجمع على: مواتم. (انظر «الروض الأنف»).
(١) الغمغمة: أصوات غير مفهومة لاختلاطها.
(٢) النهيت: صوت الصدر، وأكثر ما يوصف به الأسد. والهمهمة: صوت في الصدر أيضا.
(٣) كذا في أكثر الأصول. وفي ا: «الرعاس» قال أبو ذر: «الرعاش: يروى ههنا بالسين والشين، وصوابه بالشين المعجمة لا غير».

ቦታና ጊዜ ከመቆጠብ አንጻር በአንዱ ገጽ ላይ ብቻ ተወሰንን እንጂ ይህ የኢብኑ ሂሻም መጽሐፍ የኢብን አቢ ሳርህን ታሪክ በስፋትና በጥልቀት ነው የሚተርከው:: ሌሎች የምናያቸው በጣም ብዙ ነገሮች ስላሉ ነገሩንም እየጠቀለልነው ለማለፍ እንዲመቸን ወደ መጀመሪያው ሀሳብ እንመለስ:: መሐመድ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ ስለተለያዩ እምነቶች ሲተረክላቸው የሰሟቸውን ታሪኮች ሰብስበው ለግል ጸሐፊዎቻቸው በድጋሚ በሚፈልጉት መልኩ አጽፈው ነው ለተከታዮቻቸው ከሰማይ ወረደልኝ ያሉት:: ይህንንና ተያያዥ ጉዳዮችን ማለትም ቁርአኑ ምን ያልህ በሰው የተቀናበረ እንደሆነ ወደፊት በስፋት እናየዋለን:: ይቆየን!!!



ማጠቃለያ፡- ጌታችን መድኃኒታችን ከእርሱ በኋላ የሚነሡት ነቢያት በሙሉ ሐሰተኞች እንደሆኑ አስረግጦ ነግሮናል፡፡ «ኢየሱስም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፡- ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ፣ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፡፡» /ማቴ 24÷6-12/ በዚህ ትንቢት መሠረት በታሪክ የሚታወቁ ተራ ሰዎች ራሳቸውን ነቢይ ነኝ ብለው የመጡና ብዙዎችን ያሳቱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ይህ ጥቅስ ከጌታችን ዕርገት ከ600 ዓመታት በኋላ የመጣውን መሐመድንም በትክክል ይመለከተዋል፡፡ «ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፡፡»

ስለመሐመድና ተከታዮቹም ሐዋርያት እንዲህ ብለው ጽፈዋል፡- “በግልፅ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የኢጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ” /1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1/ “ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጀቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ” /2ኛ ጴጥ 2፡1/

ጂሃድ-የእስልምና እምነት ማስፋፊያ መንገድ! (jihad- the Way of Islam)

"ባገኛችሁባቸው ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው" ቁርአን 2:191

"Kill disbelievers [Christians] wherever you find them, take them captive, torture them" Qur'an 9:5



"Allah is our objective, the Quran is our Constitution, the Prophet is our leader, and Jihad is our way."

ስለ ጂሃድ ከመነጋገራችንና እኔም ምንም ዓይነት ትንታኔ ከመስጠቴ በፊት ይህንን ርዕስ የምታነቡ አንባቢያን ሁሉ ተከታዮቹን የመሐመድ ትእዛዞች ልብ ብላችሁ እንድትመለከቷቸው እፈልጋለሁ:: ከዚያ በኋላ የኅሊናውን ፍርድ ለእናንተው እተዋለሁ:: (ጥቅሶቹን በቀጥታ ከቁርዓኑና ከሐዲሱ የወሰድኳቸው ሲሆኑ ሁሉም ትእዛዞችና ንግግሮች የመሐመድ ናቸው:: የአማርኛውን የቁርዓኑን ጥቅሶች በ1997 ዓ.ም ነጃሺ ካሳተመው ቁርአን ላይ በቀጥታ የወሰድኳቸው ስለሆነ ከእንግሊዝኛው ቁርአን ጋር ያለው መልዕክት አንድ ላይሆን ስለሚችል የእንግሊዝኛውን ጥቅስ በደንብ ቢመለከቱት የተሸለ ነው:: የሐዲሱን ጥቅሶች በተመለከተ ግን ከእንግሊዝኛው የሐዲስ ጥቅስ ላይ ፅንሰ ሀሳቡን ብቻ ነው የወሰድኩት እንጂ ቀጥተኛ የቃል በቃል ትርጉም አልተጠቀምኩም) እነዚህ ቀጥሎ የዘረዘርኳቸው የመሐመድ "ፍለጠው፣ ቁረጠው" የሚሉ የቁርዓንና የሐዲስ የግድያ አንቀጾች ስለ ምድራዊ ሕይወት የተነገሩ እንዳይመስላችሁ! ይልቁንም አንድ ሙስሊም (ጂሃዲስት) ኢስላም ባልሆኑ ሌሎች ሰዎች ላይ እነዚህን የግድያ አንቀጾች ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ጀነት ለመግባቱ እርግጠኛ እንዲሆን ነቢያቸው መሐመድ ሰማያዊ ተስፋ ሰጥተውታል:: ጥቅሶቹን እንያቸው:-

- Qur'an 2:191 "And kill them wherever you find and catch them. Drive them out from where they have turned you out; for Al-Fitnah (polytheism, disbelief, and oppression) is worse than slaughter." "ባገኛችሁባቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጡአችሁ ስፍራ አውጡዋቸው፤ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት" ሱረቱ አል-በቀራህ 2:191

 Qur’an 9:5 “When the sacred forbidden months for fighting are past, fight and kill disbelievers wherever you find them, take them captive, torture them, and lie in wait and ambush them using every stratagem of war.”, “የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን (ኢስላም ያልሆኑትን) በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ያዙዋቸውም፤ ከበቡዋቸውም፤ ለእነሱም መጠባበቅ በየመንገዱ ተቀመጡ” ሱረቱ አል-ተውባህ 9፡5

“እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚዋጉ፣ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከሀገር መባረር ነው፡፡ ይህ ለርነሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው፣ በመጨረሻይቱም ለነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው” ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡33 “The punishment of those who wage war against Allah and His messenger and strive to make mischief in the land is only this, that they should be murdered or crucified or their hands and their feet should be cut off on opposite sides or they should be imprisoned; this shall be as a disgrace for them in this world, and in the hereafter they shall have a grievous chas-tisement” Qur'an 5:33

Qur’an 9:111 “Allah has purchased the believers, their lives and their goods. For them is Paradise. They fight in Allah’s Cause, and they slay and are slain; they kill and are killed.” “አላህ ከምእመናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ጀነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመሆን ገዝቸው፤ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፤ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም” አል-ተውባህ 9፡111 እንዲሁ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ቁ.123 ላይ “እናንተ ያመናችሁ ሆይ እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲዎች (ኢስላም ያልሆኑትን) ተዋጉ” ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ “Fight the unbelievers around you, and let them find harshness in you.”
Qur’an 9:123.
 ሳሂህ ቡኻሪ በተባለው ሐዲስ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው መሐመድ ሲናገሩ ‹‹እኔ ድል አድራጊ የሆንኩት በሽብር ነው›› በማለት ተናግረዋል፡፡ “Allah’s Apostle said, ‘I have been made victorious with terror.’” Sahih Bukhari: 4፡52፡220. መሐመድ ስለራሳቸው ሲናገሩ “አንደበተ-ርቱእ የመሆን (ልብ የሚነካ ንግግር) የማድረግና በሽብር ድል የማድረግ ቁልፍ ተሰጥቶኛል” ነው ያሉት፡፡ “The Proph-et said, ‘I have been given the keys of eloquent speech and given victory with terror.’” Sahih Bukhari: 9፡87፡127. “Allah’s Apostle said, ‘know that Paradise is under the shade of swords.’” ነቢያቸው መሐመድ ጀነት በጎራዴ (በሰይፍ) ጥላ ስር መሆኗን አስረግጠው ነው የተናገሩት፡፡ Sahih Bukhari: 4፡51፡73. ይህም ማለት ያለ ጂሃድ ጀነት አይገባም ማለት ነው፡፡ Sahih Muslim: 41፡20፡4681 “the Mes-senger said: ‘Surely, the gates of Paradise are under the shadows of the swords.’”

 ከመሐመድ ተከታዮች ውስጥ አንዱ እንደተናገረው መሐመድ ለግድያ ተልዕኮ ሰዎቻቸውን ሲልኳቸው ‹‹የምታገኙዋቸውን ሁሉ በእሳት አቃጥሏቸው›› ብለው ነው መመሪያ የሰጧቸው፡፡ Sahih Bukhari: 4፡52፡259 “Allah’s Apostle sent us on a mission as an army unit and said, ‘If you find so-and-so and so-and-so, burn all of them with fire.’”
 መሐመድ ለተከታዮቻቸው ካስተላለፉላቸው መልዕክቶች ውስጥ አንዱ “ለጂሃድ (ለመጋደል) በተጠራችሁ ጊዜ ወዲያውኑ በፍጥነት በመውጣት ለጥሪው ምላሽ መስጠት አለባችሁ” የሚል ነው፡፡ Sahih Bukhari: 4፡52፡311 “When you are called for jihad, by the Muslim ruler for Jihad fighting, you should come out imme-diately, responding to the call.” እንዲሁም የዚሁ ዓይነት ትእዛዝ በሳሂህ ቡኻሪ 4፡53፡412 ላይና በሌሎችም ሐዲሶች ላይ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ Sahih Muslim: 20፡1፡4597 “The Prophet said at the conquest of Mecca: ‘There is no migration now, but only Jihad, fighting for the Cause of Islam. When you are asked to set out on a Jihad expedition, you should readily do so.’”
 ሐዲሱ ላይ እንደተዘገበውና ካሁን በፊትም እንዳየነው ራሳቸው መሐመድ በሌሊት የጦር ወረራ አድርገው ድል ከቀናቸው በኋላ ‹‹አላሁ አከበር ካይባር ወድማለች (ተደምስሳለች)…›› እያሉ እንደተናገሩ ተጽፏል፡፡ በመጨረሻ የካይባር ነዋሪዎቿንም መሐመድም ወንዶቹን ከገደሉ በኋላ ልጆቻቸውንና ሴቶቻቸውን በጦር ማርከው ወስደዋል፡፡ ለዝሙት ለባርነት መጠቀሚያነትም ዳርገዋቸዋለል፡፡ Sahih Bukhari: 5፡59፡512 “The Prophet offered the Fajr Prayer [Prayer of Fear] near Khaybar when it was still dark. He said, ‘Allahu-Akbar!’ [Allah is Great-est] Khaybar is destroyed, for whenever we approach a hostile nation to fight, then evil will be the morning for those who have been warned.’ Then the inhabitants came out running on their roads. The Prophet had their men killed; their children and woman were taken as captives.”
 Qur’an 2:216 “Jihad (holy fighting in Allah’s Cause) is ordained for you (Muslims), though you dislike it. But it is possible that you dislike a thing which is good for you, and like a thing which is bad for you. But Allah knows, and you know not.” ከሓዲዎችን (እስልምናን የማያምኑትን) መጋደል እርሱ ለእናንተ (ለሙስሊሞች) የተጠላ ሲሆን በእናንተ ላይ ተጻፈ፤ አንዳች ነገርን እርሱ ለእናንተ

የበለጠ ሲሆን የምትጠሉት መሆናችሁ ተረጋገጠ፤ አንዳችንም ነገር እርሱ ለእናንተ መጥፎ ሲሆን እንደምትወዱት ተረጋገጠ፤ አላህም የሚሻላችሁን ያውቃል፤ እናንተ ግን አታውቁም" አል-በቀራህ 2፡216፡፡ በእንግሊዝኛው "jihad is ordained for you" የሚለውን ቃል አማርኛው ቁርአን "ጂሃድ በእናንተ ላይ ተጻፈ" ብሎ ነው ያስቀመጠው፡፡ ነገር ግን በትክክለኛው መንገድ መቀመጥ የነበረበት "ጂሃድ በእናንተ ላይ ታዟል ወይም ታውጇል" ተብሎ ነበር፡፡ ዐረብኛውም ቁርአን ከእንግሊዝኛው ጋር ተመሳሳይና አንድ ነው፡፡ የአማርኛው ቁርአንን አሳታሚዎች ግን ይዘቱን ቀለል ለማድረግ ብለው ቃሉን ቀየር ቢያደርጉትም አዋጁ በየትኛውም መልኩ ቢቀመጥ መልዕክቱ ያው ኢስላም ያልሆኑትን ሰዎች ግደሉ የሚል ነው፡፡

 በነቢያቸው ትእዛዝ መሠረት እቤታቸው የተቀመጡ ሙስሊሞች አማኒያንና በጂሃድ ጦርነት ክርስቲያኖችን ለመግደል የወጡ ሙስሊሞች በሰማይ የሚያገኙት ክብር እኩል አይደለም፡፡ "Believers who sit home and those who go out for Jihad in Allah's Cause are not equal." Sahih Muslim: 40፡20፡4676.

 Qur'an 4:95 "Not equal are those believers who sit at home and receive no injurious hurt, and those who strive hard, fighting Jihad in Allah's Cause with their wealth and lives. Allah has granted a rank higher to those who strive hard, fighting Jihad with their wealth and bodies to those who sit. Allah pre-fers Jihadists who strive hard and fight above those who sit home. He has distinguished his fighters with a huge reward." "ከምእመናን የጉዳት ባለቤት ከሆኑት በቀር ተቀማጮቹና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት አይተካከሉም፤ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉትን አላህ በተቀማጮቹ ላይ በደረጃ አበለጠ፤ ለሁሉም አላህ መልካሚቱን ተስፋ ሰጠ፡፡ ታጋዮቹንም በተቀማጮቹ ላይ አላህ በታላቅ ምንዳ አበለጠ" ይላል ቁርአኑ፡፡ ሱረቱ አል-ኒሳእ 4፡95፡፡ አሁንም ቢሆን የእንግሊዝኛውና የአማርኛው ጥቅሶች ልዩነት እንዳላቸው ልብ በሉ፡፡ "those who strive hard, fighting Jihad in Allah's Cause with their wealth and lives" ማለትም "በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው በአላህ መንገድ በጂሃድ የሚጋደሉና ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉ" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉ" በምትል ቀላል አገላለጽ ነው የአማርኛው ቁርአን ያስቀመጠው፡፡

 በሌላም ቦታ መሐመድ በቁርአኑ ላይ ተከታዮቻቸውን "በአላህ መንገድ እንዳትጋደሉ ምን ምክንያት አላችሁ? ምን ሆናችሁ ነው ለአላህ የማትጋደሉት?" እያሉ በመጠየቅ ለጂሃድ ሲያነሳሷቸው ነው የምናነበው፡፡ Qur'an 4:75 "What reasons have you that you should not fight in Allah's Cause?" "What is wrong with you that you do not fight for Allah?"

 እንደ ቁርአኑ አገላለጽ ከሆነ በእርግጥም አላህ በእርሱ መንገድ የሚጋደሉለትን ተዋጊዎች ይወዳል፡፡ Qur'an 61:4 "Surely Allah loves those who fight in His Cause."

 ሳሂህ ሙስሊም በተባለው ሐዲስ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው በጂሃድ ግድያ መሳተፍ የሁሉም ሙስሊሞች ግዴታ ነው፡፡ Sahih Muslim: 40፡20፡4676 "Jihad Is Compulsory" እንዲል መጽሐፉቸው፡፡

 ‹‹በአላህ መንገድ በጂሃድ ጦርነት ለመጋደል በጠዋት ወይም በማታ መውጣት በጅነት ውስጥ በዓለምና በእርሷ ካለው ነገር ሁሉ የሚበልጥ ሽልማት ያስገኛል›› በማለት ነቢያቸው መሐመድ ተናግረዋል፡፡ ተዋጊውንም ጂሃዲስት የጅነትን በሮች የሚጠብቁ መላኢኮች "ግዳጅህን ተወጥተህ ጀብዱ ፈጽመሃልና ና ወደ ጅነት ግባ" እያሉ ይጠሩታል፡፡ Sahih Muslim: 30፡20፡4639 "The Messenger said: 'Leaving for Jihad in the Way of Allah in the morning or in the evening will merit a reward better than the world and all that is in it.'" Sahih Bukhari: 4፡52፡94 "The Prophet said, 'whoever spends two things in Allah's Cause [his life and his wealth], will be called by all the gatekeepers of Paradise.'"

 በሐዲሱ ላይ እንደተዘገበው ከመሐመድ ተከታዮች ውስጥ አንዱ ሲናገር እንዲህ ነው ያለው፡- ‹‹‹ማንም ቢሆን ከእኛ መካከል በእምነቱ እንደ ሰማእት ሆኖ ቢገደል ወደ ጅነት ይሄዳል ይህም አይቶት የማያውቀውን የተንደላቀቀ ሕይወትን በዚያ ይኖር ዘንድ ነው› ብሎ አማላካችን እንዳለን ነቢያችን አሳውቆናል፡፡›› Sahih Bu-khari: 4፡53፡386 "Our Prophet has informed us that our Lord says: 'Whoever amongst us is killed as a martyr shall go to Paradise to lead such a luxurious life as he has never seen."

 Sahih Bukhari: 4፡52፡44 "A man came to Allah's Apostle and said, 'Instruct me as to such a deed as equals Jihad in reward.' He replied, 'I do not find such a deed.'" ከመሐመድ ተከታዮች ውስጥ አንዱ ወደ ነቢያቸው መጥቶ ከጂሃድ (ከመጋደል) ጋር በሽልማት እኩል የሆነን ተግባር ወይም ጀብድ እንድፈጽም እዘዘኝ ይላቸዋል፡፡ መሐመድም ሲመልሱለት ‹‹ከጂሃድ (ከመጋደል) ጋር እኩል የሆነን ተግባር አላገኝም›› ነው ያሉት፡፡ ቀጥሎ ባለው ሐዲስ ላይም "ከሁሉም የበለጠው ተግባር ወይም ጀብድ የትኛው ነው?" ተብለው መሐመድ ለተጠየቁት ጥያቄ ተመሳሳይ መልስ ነው የሰጡት፡፡ በአላህና በመሐመድ ከማመን ቀጥሎ በጂሃድ መሳተፍ ከሁሉም ምርጡ ተግባር ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት በጣም ብዙ ጥቅሶች በሐዲሱ ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ Sahih Bukhari: 1፡2፡25 "Allah's Apostle was asked, 'What is the best deed?' He replied, 'To believe in Allah and His Apos-tle Muhammad.' The questioner then asked, 'What is the next best in good-ness?' He replied, 'to participate in Jihad, religious fighting in Allah's Cause.'" Sahih Muslim: 34፡20፡4652-3 "A man came to the Holy Prophet and said: 'Who is the best of men?' He replied: 'A man who fights staking his life and spending his wealth in Allah's Cause.'"

Sahih Muslim: 20፡4678 "Before the battle of Uhud a Muslim asked, 'Messenger, where shall I be if I am killed?' He replied: 'In Paradise.' The man fought until he was killed." Muslim: 41፡20፡4678 "Proof of the Martyr's Attaining

Paradise: Jabir said that a man said, 'Messenger of Allah, where shall I be if I am killed?' He re-plied: 'In Paradise.' The man threw away the dates he had in his hand and fought until he was killed." መሐመድ ተከታዮቹን ጂሃድ እውጀው ኢስላም ያልሆኑትን ሁሉ በሰይፍ እንዲሰይፉ ሲያስተምሯቸው ከዚህ ድርጊታቸው ሁለት ዓይነት ጥቅሞችን እንደሚያገኙ ያስተምሯቸው ነበር። አንደኛውና የመጀሪያው በጂሃዱ ወቅት እነርሱም ድንገት ቢሞቱ እንኳን በጀነት ውስጥ ዝሙትን ጨምሮ ሁሉም ሥጋዊ ፍላጎቶቻቸው እንደሚሟሉላቸው ይነግሯቸውና ያሳምኗቸው ነበር። ሁለተኛው ደግሞ በጂሃዱ እነርሱ ድል ሲያደርጉ በዚያውም በዘረፋት ንብረት ተጠቃሚ ይሆናሉ። ድል ያደረጓቸውን ጎሳዎችም ወንዶቹን ይሰይፉና ሴቶቻቸውን በምርኮ ወስደው ይከፋፈሏቸዋል። ሲፈልጉ ለዝሙት ተግባር ይጠቀሙባቸዋል፣ ሲፈልጉ ለባርነት ንግድ ሸጠው ይለውጧቸዋል። ይህንንም በወቅቱ ራሳቸው መሐመድም ተግባራዊ አድርገውታል። ይህንንም ግልጽ በሆነና በተብራራ ሁኔታ በገጽ--------ላይ ማየት ይቻላል። ነቢያቸው መሐመድም ተከታዮቻቸው በጂሃድ ተሳትፈው ዘርፈው ስለሚያመጡት ንብረትና ስለ ድርሻ አወሳሰዳቸው በቁርአኑ ላይ በግልጽ አስቀምጠውታል። "ከማንኛውም ነገር በጦር ከከሓዲዎች የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልዕክተኛው ለነቢዩ፣ ለዝምድና ባለቤቶችም፣ ለየቲሞችም፣ ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኛም የተገባ መሆኑን ዕወቁ" ነው የሚለው ቁርአኑ። (ሱረቱ አል-አንፋል 8፡41) ይህንንም ተከታዮቻቸውና ራሳቸው መሐመድም በሕይወት በነበሩበት ወቅት ተግባራዊ አድርገውታል። ማለትም በተለያዩ ጦርነቶች ላይ በጂሃድ ጦርነት ተሳትፈው ካሸነፉ በኋላ ብዙ ንብረት ዘርፈው ሲያመጡላቸው አንድ አምስተኛውን ለራሳቸው ወስደው የተቀረውን ለተከታዮቻቸው ያከፋፍሏቸው ነበር። ስለዚህ እነ መሐመድ በጂሃዱ ጦርነታቸው ወቅት ቢያሸንፉም ቢሸነፉም በሁለቱም መንገድ አትራፊ እንደሚሆኑ ራሳቸውን ስላሳመኑት ማንም ሙስሊም ቢሆን ጂሃድን በታላቅ ድፍረትና ወኔ ለመፈጸም ዝግጁ ነው። Sahih Bukhari 4:52:46 "I heard Al-lah's Apostle saying, 'Allah guarantees that He will admit the Muslim fighter into Paradise if he is killed, otherwise He will return him to his home safely with re-wards and booty.'" በዚህ የሐዲስ ጥቅስ መሠረት መሐመድ ተከታዮቻቸውን የጂሃድ ወረራ እያደረጉ ለሚፈጽሙት ግድያ ሽልማታቸው ከሁለቱ አንዱ ነው። ካሸነፉ ንብረት ዘርፈው ምድራዊ ሀብት ያካብታሉ፣ በጂሃዱ ከሞቱ ደግሞ በጀነት ውስጥ እየበሉ፣ እየጠጡ፣ ከ72 ደናግላን ጋር ዝሙት እየፈጸሙ እስከዘላለም ድረስ በታላቅ ደስታ ይኖራሉ። (የእነዚህን በጀነት ለዝሙት ተግባር በሽልማት ስለሚሰጡት የ72 ደናግላንን ዝርዝር ሁኔታና ሰፊ ዘገባ ወደፊት እናየዋለን።)

እናም ጂሃዲስቱ ታዲያ በጀነት እንደዚህ ዓይነቱን ታላቅ ክብር ከማግኘቱና ከመደሰቱ የተነሣ "ምነው እንደገና ወደ ምድር ተመለሼ 10 ጊዜ በጂሃድ በተሳተፍኩ" ብሎ ይመኛል። የመሐመድ ተከታዮች በጂሃድ ግድያ ተሳትፈው ገድለው ጀነት ገብተው ምግቡን፣ መጠጡን፣ ከደናግላን ጋር ዝሙት መፈጸሙን... ብቻ በአጠቃላይ ምድራዊ ፍላጎቶቻቸው በጀነት ውስጥ ሲሟሉላቸውና የተንደላቀቀ ሕይወት እየኖሩ መሆናቸውን ሲያዩ ያን ጊዜ "ምነው እንደዚህ ዓይነቱን ክብር ካገኘንስ ወደ ምድር ተመልሰን 10 ጊዜ በጂሃድ ግድያ በተሳተፍን" ብለው ይመኛሉ። ተከታዮቹ ሁለት ሐዲሶች ይህንኑ ይመሰክራሉ። Sahih Muslim: 29:20:4635 "The Prophet said: 'Nobody who enters Paradise wants return even if he were offered everything on the surface of the earth except the martyr who will desire to return and be killed ten times for the sake of the great honor that has been bestowed upon him.'" Sahih Bukhari: 4:52:72 "The Prophet said, 'Nobody who enters Paradise likes to go back to the world even if he got everything on the earth, except a Mujahid [Islamic fighter] who wishes to return so that he may be martyred ten times because of the dignity he receives.'"

 እንደ ነቢያቸው ትምህርት ከተከታዮቻቸው ውስጥ በጂሃድ ጦርነት ተሳትፎ አድርጎ እግሮቹ በአቧራ የተሸፈኑ ማንም ቢኖር እርሱን የሲኦል እሳት ፈጽሞ ሊነካው አይችልም። Sahih Bukhari: 4:52:66 "Allah's Apostle said, 'Anyone whose feet get covered with dust in Allah's Cause will not be touched by the Hell Fire.'"

 በአላህ መንገድ እየተጋደለ እያለ ማንም ቢቆስል እርሱ ከነቁስሉ በፍርድ ቀን ይታያል። ለዛውም ቁስሉ እንደ አዲስ ቁስል ሆኖ እየደማ ነገር ግን ደሙ እንደ ዝባድ ሽቶ እጅግ ደስ የሚል ሽታ እየሸተተ በፍርድ ቀን ይታያል። Sahih Muslim: 28:20:4629 "The Messenger said: 'One who is wounded in the Way of Allah will appear on the Day of Judgment with his wound still bleeding. The color (of discharge) will be blood, (but) its smell will be musk.'"

 Sahih Muslim: 28:20:4626 "Merit Of Jihad And Campaigning In Allah's Cause: The Apostle said: 'Allah has undertaken to look after the affairs of one who goes out to fight in His Way believing in Him and affirming the truth of His Apostle. He is committed that He will either admit him to Paradise or bring him back to his home with a reward or his share of booty. If a person gets wounded in Allah's Cause he will arrive on the Day of Judgment with his wound in the same condition as it was when it was first inflicted; its color will be blood but its smell will be musk perfume. If it were not too hard on Mus-lims I would not lag behind any raid going out to fight in the Cause of Allah. But I do not have abundant means to provide them (the Mujahids [Islamic terrorists]) with riding beasts, nor have they all have the means (to provide themselves with the weapons of Jihad). I love to fight in the Way of Allah and be killed, to fight and again be killed and to fight and be killed.'"

 መሐመድ እንዳስተማሩት አንድ ጂሃዲስተኛ የፈረሱን የግንባር ጸጉር በጣቶቹ እየገመደ (እየጠመጠመ) ለጂሃድ ቢዘጋጅና ቢሳተፍ ትልቅ ጥቅም (ትርፋማነት) ነው። "ፈረሶችን ለጂሃድ ጦርነት ሲባል በኋላ እግራቸው እንዲቆሙ ማድረግ ትልቅ ሽልማት አለው፤ በጦርነት የተሰረቁ እቃዎችም በፈረሶች ግንባር ላይ መታሰር አለባቸው" ብለው ማናገራቸውን የመሐመድ ተከታይ መስክሯል። Sahih Muslim:

26፡20፡4614 “I saw Allah’s Messenger twisting the forelock of a horse with his fingers as he was saying: ‘A great benefit. A reward for rearing them for Jihad. The spoils of war have been tied to the forelocks of horses.’”

 ‹‹መሐመድ እንዲህ ሲል ተናገረ፡- ‹በአላህ መንገድ ለመጋደል ብሎ የፈረሱን ልጓም የሚይዝ፣ ጸጉሩ ቆሸሾ እግሮቹም በአቧራ የተሸፈኑ ሆነው የሚጋደል ማንም ቢኖር ጀነት የእርሱ ናት፡፡››› Sahih Bukhari: 4፡52፡137 “The Prophet said, ‘Paradise is for him who holds the reins of his horse to fight in Allah’s Cause with his hair unkempt and feet covered with dust.’”

 አዝ-ዙባይር የተባለው የመሐመድ ተከታይ እንደተናገረው በጦርነት ላይ ሳሉ አንዱን በጦር ዐይኑን ይወጋዋል፡፡ በእግሩም እሬሳውን እረግጦ ጦሩን በኃይል ይነቅለዋል፡፡ ይህንን ትዕይንት መሐመድ በቦታው ሆነው ይመለከቱ ነበርና ድርጊቱን ይፈጽም የነበረውን ተዋጊያቸውን ይህን ዘግናኝ ግድያ የፈጸመበትን ጦር የከብር ስጦታ አድርጎ እንዲሰጣቸው ይጠይቀውታል፡፡ ተዋጊ ጦረኞቸውም ጦሩን ለመሐመድ በማስታወሻነት ሰጥቷቸዋል፡፡ Sahih Bukhari: 5፡59፡333 “Az-Zubair said, ‘I attacked him with my spear and pierced his eye. I put my foot over his body to pull the weapon out, but even then I had to use great force. Later on Allah’s Apostle asked me for that spear and I gave it to him.’”

 Sahih Bukhari: 4፡52፡68 “When Allah’s Apostle returned from the battle of the Trench, he put down his arms and took a bath. Then Gabriel, whose head was covered with dust, came to him saying, ‘You have put down your arms! By Allah, I have not put down my arms yet.’ Allah’s Apostle said, ‘Where to go now?’ Gabriel said, ‘This way,’ pointing towards the tribe of Qurayza. So Al-lah’s Apostle went out towards them.” መሐመድ ከትሬንች ጦርነት እንደተመለሱ ታጥቀዋቸው የነበሩትን የጦር መሳሪያዎች አውልቀው ካስቀመጡ በኋላ ሰውነታቸውን ይታጠባሉ፡፡ በሐዲሱ ዘገባ መሠረት በዚህ ጊዜ እስልምናን በጂሃድ ለማስፋፋት በሚደረገው ግድያ ላይ መሐመድን ከሚረዱት ብዙ መላኢኮች ውስጥ አንዱ ጂብሪል መጥቶ ያናግራቸዋል፡፡ ጂብሪልም በጂሃዱ ውጊያ እየተሳተፈ ስለነበር ጸጉሩ በአቧራ ተሸፍኖ ነበር፡፡ ጂብሪልም መሐመድን እቤታቸው መጥቶ የጦር መሳሪያዎቻቸውን አውልቀው ሲያስቀምጡ ሲያያቸው “የጦር መሳሪያዎችህን አስቀመጥህ እንዴ?” በማለት ይጠይቃቸዋል፡፡ መሐመድም በአላህ መንገድ ለመጋደል ገና እንደሆነ ይመልሱለትና የጦር መሳሪያዎቻቸውን ታጥቀው ሲወጡ ጂብሪል “አሁን ወደየት ነው የምትሄደው?” ብሎ ጠየቃቸው፡፡ መሐመድም የባኑ ቁራይዛ ጎሳዎች ወዳሉበት አቅጣጫ እየጠቆሙ “በዚህ በኩል ነው የምሄደው” ይሉታል፡፡ ከዚያም መሐመድ በባኑ ቁራይዛዎች ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ ለማካሄድ ፈጥነው ከቤቱ ወጥተው ነው የሄዱት፡፡ (መሐመድ በባኑ ቁራይዛዎች ላይ ባደረጉት ጅምላ ጭፍጨፋ 900 የሚሆኑ ሰዎችን አንገታቸውን በሰይፍ እያስቆረጡ እንደጣሉ በገጽ——ላይ ዝርዝሩን ማየት ይቻላል፡፡)

 አሁንም እንደ መሐመድ ትምህርት ከሆነ ማንም ቢሆን በአላህ መንገድ በጂሃድ ለመሳተፍ መሀላ አድርጎ ፈረሱንም አነሳስቶ በጂሃድ ቢሳተፍ በኋላ ላይ በጀነት ውስጥ ለፈረሱ ምግብና መጠጥ ሳይቀር ያወጣው ወጪ ታስቦ እጥፍ ዋጋው ይከፈለዋል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ ለፈረሱ ስለወጣው ምግብና መጠጥ ብቻም ሳይሆን ስለ ፈረሱ ሽንትና ፋንድያም ጭምር ተብሎ ተዋጊው በጀነት ሽልማት እንደሚያገኝ ነው በሐዲሱ ላይ የተጠቀሰው፡፡ Sahih Bukhari: 4፡52፡105 “The Prophet said, ‘If somebody keeps a horse in Allah’s Cause motivated by His promise, then he will be rewarded for what the horse has eaten or drunk and for its dung and urine.’”

አሁን የመሐመድን የግድያ አንቀጾች መዘርዘሩንና የእርሳቸውንም የሕይወት ተሞክሮ ማየቱን ለጊዜው ገታ ላድርገውና በቀጥታ ማንሳት ወደፈለኩት ሀሳብ ልግባ፡፡ በዚህ ባለንበት ዘመን በውጪው የዐረቡ ዓለም ያሉትም ሆኑ በእኛም ሀገር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የዘመኑ ሙስሊም ምሁራኖቻቸው (Muslim scholars) ጂሃድ (jihad) ለሚለው ቃል ጥሩ የሆኑ የሸፋን ትርጓሜዎችን ሲሰጡ ስትሰሙ እውነት እንዳይመስላችሁ፡፡ እውነታው እስካሁን ከላይ ያየነው ነው፡፡

እነርሱ የዘመኑ ሙስሊሞች እንደሚሉት ጂሃድ በሦስት ዓይነት መንገድ ይፈጸማል ይላሉ፡፡ ሲጠቅሷቸውም ጂሃድ ማለት 1ኛ. With the heart (intentions or feelings) በልብ ይህም ማለት በማቀድ፣ በመፈለግ፣ በማሰብ ወይም ከፍተኛ ስሜት በማሳየትና በጥሩ አስተያየት ይፈጸማል ይላሉ፡፡ 2ኛ. With the tongue (speeches, etc., in the Cause of Allah) ይህም በአንደበት፣ በንግግር ይፈጸማል፡፡ 3ኛ. With the hand (weapons, etc.) ማለትም በጦርነት ወይም በመሳሪያ ይፈጸማል ይላሉ፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ከሦስቱ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ትርጓሜዎች ዘመናዊያኑ ሙስሊሞች አሁን አሁን የፈጠሯቸው ሽፋኖች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በቁርአኑና በሐዲሱ ላይ እንደተቀመጠውና ከላይ እንዳየነው “ጂሃድ” የሚለውን ቃል በወቅቱ መሐመድና ተከታዮቻቸው አሁን የዘመኑ ሙስሊሞች በሚሉት መንገድ ፈጽሞ አልተጠቀሙበትም፡፡ ቁርአኑ ውስጥም ፈጽሞ ዘመናውያኖቹ በሚሉት ዓይነት መንገድ ተጽፎ አልተቀመጠም፡፡ እናም ያለ ምንም ርህራሄ የሰውን አንገት እንደ ጎመን እየቀረደዱ ለሚጥሉበት ዘግናኝና ኢሰብአዊ ድርጊታቸው እነርሱ ምንም እንኳን “ቅዱስ ጦርነት”, “holly war” የሚል ስያሜ ቢሰጡትም ቃሉ በተግባር ሲገለጽ ግን የዘመኑ ሙስሊሞች በሚሉት መንገድ አይደለም፡፡

ደግሜ ደጋግሜ እውነቱን እናገራለሁ፡፡ “ጂሃድ” የሚለውን ቃል በወቅቱ እነ መሐመድ የተጠቀሙበት መንገድና ቃሉም በቁርአን ተጽፎ የተቀመጠበት አገባብ እነኚህ አሁን ያሉት የዘመኑ ሙስሊም መምህራኖቻቸው እንደሚሉት አይደለም፡፡ ፈጽሞ አይደለም፡፡ በየቀኑ በተለያዩ የዜና አውታሮች የምናያቸውና የምንሰማቸው እጅግ አሰቃቂና ዘግናኝ ግድያዎችና የሽብር ጥቃቶች የዚህ ትክክለኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡

መጀመሪያ ላይ የጠቀስኳቸውን እዚያን የመሐመድን የግድያ አንቀጾች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አንድ ነገር ሙሉ በሙሉ መደምደም ይቻላል፡፡ በየቀኑ በተለያዩ የዜና አውታሮች የምናያቸውና የምንሰማቸው አሰቃቂና ዘግናኝ ግድያዎችና የሽብር ጥቃቶች ሁሉ የመሐመድ ውጤቶች ናቸው፡፡ በዚህ እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ማንኛውንም ጂሃዲስት ስለሚፈጽመው የግድያ ተግባር ለምን ያን እንደሚያደርግ ብትጠይቁት “ነቢያችን አዘዋል” ነው የሚላችሁ፡፡ የአላህን ትእዛዝ እንደፈጸመ ነው በልበ ሙሉነት የሚናገረው፡፡ ሳሂህ ቡኻሪ በተባለው ሐዲስ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ራሳቸው መሐመድም ሲናገሩ “እኔ ድል አድራጊ የሆንኩት በሽብር ነው” በማለት እውነቱን ነግረውናል፡፡ “Allah’s Apostle said, ‘I have been made victorious with terror.’” Bu-khari: 4፡52፡220፡፡ ከላይ በግልጽ እንዳየነው በቁርአኑም ላይ መሐመድ ለተከታዮቻቸው ያስተላለፉላቸው መልእክት “fight and kill disbelievers wherever you find them, take them captive, torture them” ማለትም ሙስሊም ያልሆኑትን ሰዎች “ባገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ማርኳቸውም፤ አሰቃዩዋቸውም፤ እነሱንም ለመጠባበቅ በየመንገዱ ተቀመጡ” (ቁርአን 2:191፣ 9:5)፤ “ከማንኛውም ነገር በጦር ከከሓዲዎች የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልዕክተኛው የተገባ መሆኑን ዕወቁ” (8፡41) በማለት ነው ተከታዮቻቸው ክርስቲያኖችን ገድለው ንብረታቸውን ከዘረፉ በኋላ ለአላህና ለእርሳቸው አንድ አምስተኛውን እንዲሰጡ ትእዛዝ የሰጧቸው፡፡ ይህንንም መሐመድ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ተግባራዊ አድርገውታል፡፡ ስለዚህ ዛሬ በየትኛውም ሀገር በዓለም ላይ እየተፈጸሙ ያሉ እጅግ አሰቃቂ ግድያዎችና የሽብር ጥቃቶች ሁሉ የመሐመድ ውጤቶች ናቸው የሚለው መደምደሚያዬ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው፡፡

በእንግሊዝኛው ‹Fight› የሚለው ቃል በቁሙ ሲተረጎም ጠብ፣ ጦርነት፣ ድብድብ፣ ውጊያ፣ ትግል፣ ማጥፋት፣ ማስወገድ፣ ግብግብ መግጠም….የሚሉ ብዙ አቻ ትርጉሞችን ሊይዝ ይችላል፡፡ በተግባር ሲገለጹ ‹fight› ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች የእንግሊዝኛ ቃላቶችን እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ Kill, murder, slaughter, slay, put to death, Combat, Struggle, Strife, War, do battle, የሚባሉትን ቃላት በምሳሌነት ማንሳት እንችላለን፡፡ እነዚህ ቃላት ሲተረጎሙ መግደል፣ ነፍስ ማጥፋት፣ ማረድ፣ መሰየፍ፣ ጦርነት መግጠም…. የሚል ፍቺ ቢኖራቸውም እነዚህ ሁሉ በቁም ትርጉማቸው የተለያዩ ይሁኑ እንጂ ሁሉም ቃላት ተግባር ላይ ሲውሉ የመጨረሻ መልእክታቸው ያው ግድያ ነው፡፡

እንደዚሁ ሁሉ ‹Fight› ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ‹QATL› የሚለው የዐረብኛ ቃል አቻ ትርጉሙ ሲሆን ‹QATL› የሚለው ቃል Qital, Kifah, 'Airak, Harb, Qatl, Thabh, Jazr, Thabh, Jazr የሚባሉ ሌሎች ተቀጽላዎች አሉት፡፡ ለእነዚህም ቃላት Fight, Kill, Murder, Slaughter, Slay, Murder, Combat, Slay, Put to death, የሚባሉት የእንግሊዝኛ ቃላት አቻ ትርጉሞቻቸው ናቸው፡፡

በጣም በሚገርምና እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ቁርዓኑና ሐዲሱ በእነዚህ የ“ግደለው ቁረጠው፣ ፍለጠው” የግድያ ቃላት የታጨቁ መሆናቸው ነው፡፡ ብታምኑም ባታምኑም እነዚህ የግድያ ቃላት በቁርዓኑና በሐዲሱ ውስጥ በአጠቃላይ ከ35,000 ጊዜ በላይ ተጠቅሰዋል፡፡ ይህንንም መረጃ “in the name of Allah” የተሰኘው መካነ ድር (website) በትክክል ቆጠራ ካደረገ በኋላ ይፋ ያደረገው መረጃ ነው፡፡ መካነ ድሩ እንዳውም በትክክለኛ ቆጠራው መሠረት እነዚህ የግድያ ቃላት በቁርዓኑና በሐዲሱ ውስጥ የተጠቀሱት ከ35,213 ጊዜ በላይ መሆኑን የዘገበው፡፡ The Arabic language, one word QATL with its derivatives like Fight (Qital, Kifah, 'Airak, Harb, etc), Kill (Qatl, Thabh, Jazr), Murder (Qatl), Slaughter (Thabh, Jazr), Slay (Qatl) and other derivatives like Qital, Qatl, Qatala, Yaqtulu, Youqatilou, are repeated in the Quran and Ahadith at least 35,213 times. All these words are usually used against all those who do not believe in Muhammad and his Quran.

የጂሃድ የመጨረሻ ዓላማና ተግባሩ ምንድን ነው? /the ultimate goal & purpose of jihad/

እስከሁን ድረስ ከላይ በግልጽ እንዳየነው ነቢያቸው መሐመድ ለተከታዮቻቸው ጂሃድን ያስተማሩት ጂሃድ ማለት ጀነትን የሚወርሱባት ዋነኛው መንገድ እንደሆነ አድርገው ነው፡፡ እንደ እሳቸው ትምህርት ከሆነ ሙስሊሞች ጀነትን ለመውረስ ሁለት ነገሮችን ብቻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው በአላህና በመሐመድ ማመን ሲሆን ሁለኛው ደግሞ ሕይወትንና ንብረትን ሙሉ በሙሉ መስዋዕት በማድረግ በጂሃድ መሳተፍ ነው፡፡ ታዲያ በጂሃድ ሲሳተፉ ድንገት ቢሞቱ እንኳን በጀነት ውስጥ ዝሙትን ጨምሮ ሁሉም ስጋዊ ፍላጎቶቻቸው እንደሚሟሉላቸው አስተምረዋቸዋል፡፡ በጂሃዱ እነርሱ ድል ካደረጉ ደግሞ በምድር ላይ በዘረፉት ንብረት ሀብታቸውን ያካብታሉ፤ ወንዶቹን ይሰይፉና ሴቶቻቸውን በምርኮ ወስደው ለዝሙትና ለባርነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ይህ በቁርዓኑና በሐዲሱ እንዲሁም በጣም ጥንታዊ በሆኑ የታሪክ መዛግብት ተመዝግቦ የሚገኝ ግልጽ የሆነ እውነታ ነው፡፡

ይሁንና የመሐመድ ጂሃድን የማወጅ ዋነኛ ዓላማ ተከታዮቻቸውን በጀነት የተንደላቀቀ ሕይወት ውስጥ ማኖር ወይም እነርሱን በምራዊ ሀብት ማበልፀግ አይደለም፡፡ ታዲያ መሐመድ ጂሃድን የመረጡበት የመጨረሻ ግባቸው ወይም ዓላማቸው ምንድን ነው? ካልን መልሱን ከቁርአኑ ላይ እነሆ፡- ‹‹እርሱ (አላህ) ያ ኢጋሪዎቹ ቢጠሉትም መልዕክተኛውን (መሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው›› ሱረቱ አል-ተውባህ 9፡፡33 “It is He Who has sent His Messenger (Muhammad) with guidance and the religion of truth, to make it superior over all religions, though the Mushrikûn (polytheists, pagans, idolaters, disbelievers in the Oneness of Allah) hate it.” Qur’an 9:33

መሐመድ ጂሃድን የመረጡበት የመጨረሻ ግባቸውና ዓላማቸው ‹‹እስልምናን ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ የበላይ ማድረግ›› ነው፡፡ “…to make it (Islam) superior over all religions” ተብሎ ነው በግልጽ የተቀመጠው፡፡ በዚህም መሠረት ነቢያቸው መሐመድ የመሠረቱት እስልምና ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ የበላይ ሲሆን ራሳቸው መሐመድ ደግሞ የነቢያት ሁሉ የበላይ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው ሀሳባቸው ተሳክቶላቸዋል ምክንያቱም እርሳቸውን የሚከተሉት አማኞቻቸው በሙሉ ስለ መሐመድ ሲናገሩ ‹‹ነቢያችን የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ነው›› ይሏቸዋል፡፡ እንዲው በእውነት ከማንነታቸው፣ ከድርጊቶቻቸውና ከአስተምህሮታቸው አንጻር መሐመድ ከነጭራሹ የነቢይነትን መስፈርት ያሟላሉ ወይ? የሚለው ትልቅ ጥያቄ የግድ ከግንዛቤ ውስጥ የሚገባ ቢሆንም ተከታዮቹ ግን

“መሐመድ የነቢያት ሁሉ የበላይ ነው” የሚለውን የግል ሀሳባቸውን ካወጁልን ቆይታል፡፡ አሁን የሚቀራቸው “እስልምና የሃይማኖቶች ሁሉ የበላይ ነው” የሚለው ሀሳባቸው ነው፡፡ “እስልምና ገና አፍሪካን፣ ሰሜን አሜሪካንና ድፍን አውሮፓን በአጠቃላይ መላውን ዓለም ይቆጣጠራል” Islam will dominate the world ለሚለው ጽፈኛ አቋማቸው በሚወስዱት ዘግናኝ የጂሃድ እምጃ ዛሬ በዓለም ላይ የብዙዎች ሕይወት እንደ ቅጠል እየረገፈ ይገኛል፡፡

ብዙ ሙስሊሞች እስልምና የሰላም ሃይማኖት እንደሆነ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ እስካሁን እንዳየነውና ወደፊትም በደንብ እንደምናየው ግን ቁርአናቸውና ሌሎች መጽሐፍቶቻቸው ግን በጂሃድ ጥቅሶች የተሞሉ ናቸው፡፡ መሐመድም ሆኑ ተከታዮቻቸው እስልምና እምነትን በመከተል ጀነት መግባት እንደሚቻል ተስፋ ከመስጠት ይልቅ በጂሃድ መሳተፍ የጀነት መግቢያ ዋስትና እንደሆነ አድርገው ከማቅረባቸውም በላይ ዋነኛ ዓላማቸው እስልምናን በዓለም ላይ ካሉ ሌሎች ሃይማኖቶች ይልቅ የበላይ ማድረግ ነው፡፡ ይህ በራሱ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው በእውነት፡፡ ሃይማኖት ሲባልኮ የነፍስ ጉዳይ እንጂ የሃይማኖት መበላለጥ ጉዳይ አሊያም በጀነት ሥጋዊ ፍላጎትን የማሟላት ጉዳይ አይደለም፡፡

በመሐመድና አሁንም ድረስ ባሉት ተከታዮቻቸው እምነትና አስተምህሮ መሠረት ማንኛውም ሙስሊም እስልምናን በዓለም ላይ ካሉ ሌሎች ሃይማኖቶች የበላይ ለማድረግ ሲባል ለሚደረገው የጂሃድ እንቅስቃሴ ተሳታፊ መሆን ግዴታው ነው፡፡ “Jihad Is Compulsory.”ብሎ መጽሐፋቸው በግልጽ እንዳስቀመጠው፡፡ Sahih Mus-lim: 40፡20፡4676. ስለዚህ እስካሁን እንዳየነው አንድ ሙስሊም በጂሃድ ሲሳተፍ ቢሞት በጀነት ሥጋዊ ፍላጎቶቹ ሁሉ ይሟሉለታል እርሱ ብቻ እስልምናን የበላይ ለማድረግ ራሱንም ሆነ ሀብቱን መስዋዕት በማድረግ በጂሃድ መጋደል አለበት፡፡ ለመሆኑ ራሳቸው ሙስሊም ምሁራኖቻቸውስ (Muslim scholars) በዚህ በጂሃድ ጉዳይ ላይ ምን ይላሉ? ዋና ዋና የሚባሉት የጥቂቶቹን አስተያየት ቀጥሎ እንመለከት፡-

የዘመኑ ሙስሊም መምህራኖቻቸውስ ስለ ጂሃድ ምን ይላሉ? (What did the mod-ern Muslim scholars say about jihad?)፡- የቀድሞው የሳውዲ ዐረቢያ የፍትህ አለቃ የበረውና መካ ውስጥ የሚገኘው የግራንድ መስጂድ ኢማም የሆነው ሼህ አብዱላህ ቢን ሙሐመድ ቢን ሁማይድ የጂሃድ ምንነት ሲያስረዳ እንዲህ ነው ያለው፡- “Among the obligatory acts of worship are offering the Salat (prayers), observing the Saum (fasts), paying the Zakat and performing the Hajj (pilgrimage to Makka). Besides these acts of worship, a Muslim is directed to abstain from evil deeds and to perform good deeds. But, as regards the reward and blessing, there is one deed which is very great in comparison to all the acts of worship and all the good deeds-and that is Jihad!” ትርጉም፡- “ከእስልምና እምነት ዋና ዋና ተግባሮች ውስጥ ሶላት መስገድ፣ መጾም፣ ዘካ መውጣት፣ ወደ መካ የሃጅ ጉዞ ማድረግ ይገኙበታል፡፡ ከእነዚህ የእምነቱ ዋና ዋና ተግባሮች በተጨማሪ አንድ ሙስሊም ከመጥፎ ድርጊቶች ታቅቦ ጥሩ ድርጊቶችን እንዲሠራ ይታዘዛል፡፡ ነገር ግን የከብር ሽልማትንና በረከት ማግኘትን በተመለከተ ከሌሎቹ የእምነቱ ዋና ዋና ተግባሮችና ከሁሉም መልካም ሥራዎች በጣም የሚበልጥ አንድ ድርጊት አለ- ያም ጂሃድ ነው”
(http://islaminitsownwords.blogspot.com/2009/04/jihad-in-quran-and-sunnah.html)

ዶ/ር ሰይድ ረመዳን አል-ቡቲ ግብፅ ውስጥ ዳማስከስ በሚባለው ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ የሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዲፓርትምንት ኃላፊ ነው፡፡ ስለ ጂሃድ ያለውን አስተያየት ሲናገር ተከታዩን አስገራሚ አስተያየቶችን ሰጥቷል፡፡ Dr. M. Sa’id Ramadan Al-Buti፡ “The Holy war as it is known in Islam is basically an offensive war, and it is the duty of all Muslims of every age, when the needed military power is available, because our prophet Muhammad said that he is ordered by Allah to fight all people until they say ‘No God but Allah, and he is his messenger.’ The theory that our religion is a peaceful and loving religion is a wrong theory.” “እንደሚታወቀው በእስልምና ቅዱሱ ጦርነት (ሂሃድ) መሠረታዊ የሆነ የማጥቃት ጦርነት ነው፡፡ ተፈላጊው የጦር ኃይል በተገኘ ሰዓት ጂሃድ መፈጸም በማንኛውም የዕድሜ ክልል ላይ ቢገኙ የሁሉም ሙስሊሞች ግዴታ ነው፡፡ ምክንያቱም ‘ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድም መልዕክተኛው ነው’ ብለው እስከያምኑ ድረስ ሁሉንም ሕዝብ እንድንዋጋ በአላህ እንደታዘዝን ነቢያችን መሐመድ ተናግረዋልና ነው፡፡ እስልምና ሃይማኖታችን የሰላምና የፍቅር ሃይማኖት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ የተሳሳተ ፅንሰ ሀሳብ ነው” (Dr. M. Sa’id Rama-dan Al-Buti - "Jurisprudence of Muhammad’s Biography", Pg. 134, seventh Arabic edition, published by Azhar University of Egypt)

“Jihad against the disbelievers is the most noble of actions, and moreover it is the most important action for the sake of mankind.” (Shaykh ul-Islam, Ibn Taymiyahh, Al Furqan, Page 44-45) “በማያምኑ (ኢስላም ባልሆኑ) ሰዎች ላይ ጂሃድን ማወጅ ከድርጊቶች ሁሉ በጣም ክቡር (ድንቅ) የሆነ ድርጊት ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ ጂሃድ ስለ ሰው ልጆች ሲባል በጣም ጠቃሚ ድርጊት ነው” በማለት የተናገረው ኡል-ኢስላም የተባለው ሼህ ነው፡፡

ReligionofPeace.com የተሰኘው መካነ ድር የኡሳማ ቢላደንንና ሌሎችም ኢስላማዊ ጂሃዲስቶች (ተዋጊዎች) ስለ ጂሃድ የተናገሩትን ንግግር “Why terrorists do what they do... in their own words” በሚል ርዕስ በዝርዝር የጠቀሳቸውን ጠቅለል ባለ መልኩ ቀጥሎ አቅርቤዋለሁ፡፡

"I am one of the servants of Allah. We do our duty of fighting for the sake of the religion of Allah. It is also our duty to send a call to all the people of the world to enjoy this great light and to embrace Islam and experience the happiness in Islam. Our primary mission is nothing but the furthering of this religion." (Osama bin Laden, May 1998.) “እኔ ከአላህ አገልጋዮች ውስጥ አንዱ ነኝ፡፡ ስለ አላህ ሃይማኖት ስንል በመዋጋት

ኃላፊነታችንን እንወጣለን፡፡ ይህንን ታላቅ ብርሃን (ጂሃድን) እንዲቀላቀሉና እስልምናን እንዲሰብኩ በዚህም በሚገኘው ደስታ እስልምናውን እንዲለምዱት ጥሪያችንን ለሁሉም የዓለም ሕዝቦች መልእክት መላክም የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡ የመጀመሪያ ተልዕኮአችንም ይህንን እስልምና ሃይማኖትን ከዚህ ይበልጥ ማስፋፋት ነው እንጂ ሌላ አይደለም›› በማለት ነው ቢላደን የተናገረው፡፡

ታፍነው የተያዙ ሰዎችን አንገት በሰይፍ በመቁረጥና በአሸባሪነቱ የሚታወቀው የሱኒ ሙስሊሞች አባል የሆነው አቡ ሙሳብ አል-ዛርቃዊ የተባለው ሰው እርሱና መሰሎቹ ጂሃድ የሚፈጽሙበትን ሁኔታ ሲናገር እንዲህ ነው ያለው፡- “ዓላማን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ በሆነ በማንኛውም መንገድ ካፊር የሆኑ የማያምኑ ሰዎችን እንድንመታ፣ እንድንገድልና እንድንዋጋ አላህ እንዳዘዘን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የአላህን ሕጎች ከፍ ለማድረግ ጂሃድን የሚፈጽሙ አገልጋዮቹ የማያምኑትን (ኢስላም ያልሆኑትን) እነርሱን ለመግደል፣ ነፍሳቸውን ከሰውነታቸው ለመለየት፣ ምድርን ከእነርሱ ከፍተኛ ጥላቻ ለማጽዳት የሚጠቅም ሁሉንም ማንኛውንም ዓይነት አስፈላጊ ነገር እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ ጂሃድ በሚፈጸምበት ወቅት ምንም እንኳን ሁሉቱም ወገኖች ማለትም አስበውና አቅደው በንቃት የሚዋጉና አቅደው የማይዋጉት እንደ ሴቶች፣ ሕጻናትና ሌሎችም በስነ ሕጋችን የተወሰኑትን የሚነካ ቢሆንም እንኳ የጂሃድ ዓላማው ያለማቋረጥ መቀጠል አለበት”, “There is no doubt that Allah commanded us to strike the Kuffar (unbelievers), kill them, and fight them by all means necessary to achieve the goal. The servants of Allah, who perform Jihad to elevate the word (laws) of Allah, are permitted to use any and all means necessary to strike the active unbeliever combatants for the purpose of killing them, snatch their souls from their body, and cleanse the earth from their abomination. The goal must be pursued even if the means to accomplish it affect both the intended active fighters and unintended passive ones such as women, children and any other passive cate-gory specified by our jurisprudence.” (Abu Musab al-Zarqawi, Sunni terrorist known for cutting captives’ throats)

አሁን ሥልጣን ላይ ከመውጣታቸው በፊት የግብፆቹ ሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ ኃላፊዎች በአንድ ወቅት ሃይማኖታዊ አስተሳሰባቸውን የገለጹበት መንገድ እንዲህ የሚል ነበር፡- “ዓላማችን አላህ ነው፣ ሕገ መንግስታችን ቁርአን ነው፣ መሪያችን ነቢያችን ነው፣ መንገዳችን ደግሞ ጂሃድ ነው” "Allah is our objective, the Quran is our Constitution, the Prophet is our leader, and Jihad is our way." (Credo of the Muslim Brotherhood)

ሽብርተኞች በስፔን ማድሪድ ከተማ አድርሰውት በነበረው የባቡር አደጋ የተነሳ ከ200 በላይ ንጹሐን ዜጎች ለሞት እንደተዳረጉ ይታወቃል፡፡ አቡ ሀፍስ አል-ማስሪ የተባለው ሰው የተፈጸመውን ይህንን የግድያ ተግባር ከቁርአን ጥቅስ ጋር በማያያዝ አስተያየት ሰጥቶበታል፡፡ "Allah, may he be praised, said ‘Kill them wherever you find them, and drive them out from where they have driven you out; for inter-nal strife [Fitna] is worse than killing.’" (The Qur’anic verse quoted by the Abu Hafs Al-Masri Brigades in explaining the murder of 202 Madrid train commuters) “አላህ የተመሰገነ ይሁንና እንዲህ ብሏል፡- ‘ባገኛችሁባቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጡአችሁ ስፍራ አውጡዋቸው፤ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት’” ሱረቱ አል-በቀራህ 2፡191፡፡

Mujahid ማለት የዐረብኛ ቃል ሲሆን ለጂሃድ የሚጋደል ጂሃዲስት (ተዋጊ) ማለት ነው፡፡ የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ኦማር አል-በሽር በአንድ ወቅት በጂሃዲስቶቹ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ያደረጉት ንግግር “ረጅም ዕድሜ ለጂሃዲስቶች!” የሚል ነበር፡፡ "Long live the Mujahideen" (Sudanese President, Omar al-Bahir, at a meeting of Janjaweed fighters) ሲጀመር ጂሃድ የመስሊሞች ግዴታ እንደሆነ በሱዳን ሕገ መንግሥት ውስጥ መካተቱ በራሱ ብዙ መልዕክት አለው፡፡ “Jihad is a duty.” (The constitution of the Islamic Republic of Sudan)

የመካከለኛው ምስራቅ የፖለቲካ ተንታኝ የሆነውና በተለያዩ ኢስላማዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ በጣም በርካታ ጽሑፎችን የሚጽፈው የኢራቅ ተወላጁ ሼህ ማጂድ ካዱሪ ስለ ጂሃድ ሲናገር “ማንኛውም ሀገርና ህዝብ (ክርስቲያኖቹን ለማለት ነው) የራሱ የሆነ ገዳማዊ ሥርዓት አለው፤ እናም የዚህ ኢስላማዊ ሀገርና ህዝብም ገዳማዊ ሥርዓቱ ጂሃድ ነው” በማለት ተናግሯል፡፡ "Every nation has its monasticism, and the monas-ticism of this [Muslim] nation is the jihad." Majid Khadduri.

እስራኤል ውስጥ ስድስት ሕጻናትን ጨምሮ 15 ንጹሐን ዜጎችን በጅምላ ከገደለ በኋላ ድርጊቱን የፈጸመው ግለሰብ የተናገረው ነገር “ይህ ቀድሞ የተሰላ ድርጊት ነበር፣ በአላህ ፅኑ እምነትና ፍርድ ነው የተፈጸመው፡፡ ስለ አላህ ስል ራሴን ለጂሃድ አሳልፌ ሰጥቻለሁ፣ አላህም ስኬትን አጎናጽፎኛል፡፡ በጦርነት የሞቱ ወይም የተጎዱ ሰዎች ምን ያህል እንደነበሩ ታውቃላችሁ? ያ የሆነው በአላህ ነው” የሚል ነበር፡፡ "It was a calcu-lated act, performed with conviction and faith in Allah. I dedicated myself to Jihad for the sake of Allah and Allah granted me success. Do you know how many casu-alties there were? That was made possible by Allah." (Ahlam Tamimi, one of the bombers who slaughtered fifteen innocents, including six children at a Sbarro's pizza parlor.)

ጣሂር የተባለው የኡዝቤኪስታን ኢስላማዊ እንቅስቃሴ መሪ ስለ ጂሃድ ሲናገር “ኡዝቤኪስታን ውስጥ ኢስላማዊ መንግሥት ለመፍጠር ሲባል ጂሃድን አዘናል” ነው ያለው፡፡ "We have declared a jihad to create a religious government in Uz-bekistan" (Islamic Movement of Uzbekistan leader, Tahir Yuldeshev)

“በጎራዴ ጫፍ የአላህን ሕግ በምድር ላይ በተግባር እንፈጽማለን፡፡” ይህን የተናገረው መቀመጫውን የመን አድርጎ አሜሪካና አውሮፓ ውስጥ የተለያዩ ግያዎችን በምሥጢር ያቀናብር የነበረ ሰው ነው፡፡ "We will implement the rule of Allah on earth by the tip of

the sword." (Islamic cleric Anwar al-Awlaki, who has inspired multiple bombing and shooting plots in the U.S. and Europe from his base in Yemen).

መሐመድ ባውየሪ የተባለው ሙስሊም ሆላንድ ውስጥ አንዱን የፊልም ባለሙያ በጨቤ ወግቶ ይገድለዋል፡፡ ተይዞ ፍርድ ቤት ቀርቦ ለምን ይህን ግድያ ፈጸምክ ተብሎ ሲጠየቅ የሰጠው ምላሽ “ያደረኩትን ነገር እንድፈጽም ያደረገኝ ነገር እምነቴ ነው፡፡ አላህንና ነቢዩን የሚዘልፈውን የማንኛውንም ሰው ጭንቅላት እንድቆርጥ በታዘዝኩት ሕግ ተነሳስቼ ነው የገደልኩት” የሚል ነው፡፡ ይህንንም ሲናገር በአንድ እጁ ቁርአንን ይዞ ነበር፡፡ "What moved me to do what I did was purely my faith. I was motivated by the law that commands me to cut off the head of anyone who insults Allah and his Prophet." (Mohammed Bouyeri, explaining in court why he stabbed Dutch filmmaker Theo Van Gogh to death. (Bouyeri was holding a Qur'an at the time).

“Terrorism is a badge of honor on our chests until Judgment Day. In the name of Allah, we’re pursuing the path of jihad. We follow the steps of the Prophet (Muhammad) Allah is our Lord." (Hassan al-Smeik, leader of the cell that plotted a chemical weapons attack intended to kill 80,000 Jordanians) “ሽብርተኝነት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ደረታችን ላይ ያለ የክብር መለያ ምልክት ዓርማችን ነው፡፡ በአላህ ስም የጂሃድን መንገድ ባለማቋረጥ እንሰራለን፤ የነቢዩ መሐመድን ፈለግ እንከተላለን አላህም የእኛ ጌታ ነው”

ናይጄሪያ ውስጥ በክርስቲያኖች ላይ ጂሃዳዊ ጦርነቶችን ከሚከፍቱ ቡድኖች ውስጥ አንዱ አባል ስለ ድርጊታቸው ሲናገር “የዶሮ ጫጩትና አውራ በግን በመግደል እንደምደሰተው ሁሉ አላህ እንዳዘዘኝ ማንንም በመግደል እንደሰታለሁ” ነው ያለው፡፡ "I enjoy killing anyone that Allah commands me to kill the way I enjoy killing chickens and rams" (A Boko Haram spokesman explaining his groups declared war on Nigerian Christians.)

"Our whole struggle is for the enforcement of Sharia law" “የእኛ ሙሉ ትግላችን የሸሪዓን ሕግ ተፈጻሚ ማድረግ ነው፡፡” ፓኪስታን ውስጥ ብዙ የቦምብ ጥቃቶችን፣ የተኩስ ግድያዎችንና ጠለፋዎችን በኃላፊነት ይመራ የነበረው ሰው ይህን የተናገረው፡፡ (Muslim Khan, Spokesperson for the Pakistani Taliban, responsible for hundreds of bombings, shootings and abductions.)

እ.ኤ.አ መስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም በአሜሪካ ኒውዮርክ ከተማ ላይ የደረሰውን አውሮፕላን አደጋ ሁሉም ያስታውሰዋል፡፡ በወቅቱ አውሮፕላኑን ጠልፎ የነበረው አህመድ አል-ሀዝናዊ የተባለው አሸባሪ ድርጊቱን ከመፈጸሙ በፊት የሚከተለውን ተናግሮ ነበር፡- “ከሀገራቸው ውጭ ገደልናቸው ምስጋና ለአላህ ይሁን! ዛሬ ግን ማዕከላዊ በሆነው በራሳቸው ቤት እንገላቸዋለን፡፡ ኦ! አላህ ለአንተ ስል ራሴን መስዋዕት አድርጌያለሁና እኔን እንደ ሰማዕት ተቀበለኝ” "We killed them outside their land, praise be to Allah. Today, we kill them in the midst of their own home. O Allah, I sacrifice myself for your sake, accept me as a martyr. (Ahmad al-Haznawi, Flight 93 Hijacker)

"Allahu Akbar! Allahu Akbar! Allahu Akbar!" (Last words from the cockpit of Flight 93)

አቡ ኢሻቅ አል-ሁዌይኒ የተባለው ግብፃዊ ሼህ በቅርቡ ስለ ጂሃድ ሲናገር ‹‹እኛ (ሙስሊሞች) አሁን ድሆች የሆንበት ምክንያት ጂሃድን ስለተውነው ነው፡፡ ቢያንስ በዓመት አንድ እንኳን የጂሃዲስት (የተዋጊ) ወረራ ማድረግ ከቻልን ወይም ሁለት አሊያም ሦስት ጊዜ ማድረግ ከቻልን በምድር ላይ ብዙ ሰዎች ሙስሊሞች ይሆናሉ›› ነው ያለው፡፡ በርካታ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች “እንዴት ነው ነገሩ!?” እያሉ ጉዳዩን በሰፊው ዘግበውታል፡፡ ሼሁ በሀገሩ የዐረብ ቴሌቭዥን ጣቢያ ላይ ቀርቦ ያደረገውን ንግግር TheReligionofPeace.com የተባለው መካነ ድር በሰፊው ዘግቦታል፡፡ ሙሉውን ዘገባ እንየው፡-

Consider this remarkable excerpt from a recent televised sermon by Abu Ishak al Huweini:

“We are at a time of Jihad; Jihad for the sake of Allah is a pleasure, a true pleasure. Mohammed’s followers used to compete to do it. The reason we are poor now is because we have abandoned jihad. If only we can conduct a jihadist invasion at least once a year or if possible twice or three times, then many people on Earth would become Muslims. And if anyone prevents our dawa or stands in our way, then we must kill them or take as hostage and confiscate their wealth, women and children. Such battles will fill the pockets of the Mujahid who can return home with 3 or 4 slaves, 3 or 4 women and 3 or 4 children. This can be a profitable business if you multiply each head by 300 or 400 dirham. This can be like financial shelter whereby a jihadist, in time of financial need, can always sell one of these heads (meaning slavery)”

ትርጉም፡- “እኛ (ሙስሊሞች) በጂሃድ ወቅት ላይ ነው ያለነው፡፡ ስለ አላህ ሲባል ጂሃድን መፈጸም (መጋደል) ታላቅ ደስታ ነው፣ እውነተኛ ደስታ ነው፡፡ የመሐመድ ተከታዮች ጂሃድን (ግድያን) ለመፈጸም ይወዳደሩ ነበር፡፡ እኛ አሁን ድሆች የሆንበት ምክንያት ጂሃድን ስለተውነው ነው፡፡ ቢያንስ በዓመት አንድ እንኳን የጂሃዲስት (የተዋጊ) ወረራ ማድረግ ከቻልን ወይም ሁለት አሊያም ሦስት ጊዜ ማድረግ ከቻልን በምድር ላይ ብዙ ሰዎች ሙስሊሞች ይሆናሉ፡፡ ዳዕዋችንን እንዳናደርግ የሚከለክለን ወይም በመንገዳችን የሚቆም ሰው ማንም ቢኖር እንደዚህ ዓይነቶቹን መግደል አለብን ወይም እነርሱን አግተን ሀብታቸውን፣ ሴቶቻቸውንና ለጆቻቸውን መውረስ አለብን፡፡ ሦስት ወይም አራት ባሪያዎችን፣ ሦስት ወይም አራት ሴቶችንና ሦስት ወይም አራት ልጆችን ይዞ ወደ ቤቱ ለሚመለስ አንድ ጂሃዲስት እንደዚህ ዓይነቶቹ ውጊያዎች የተዋጊውን ኪስ ይሞሉለታል፡፡ እያንዳንዱንም ሰው በ300 ወይም በ400 ድርሀም ካባዛነው ይህ በእርግጥም አትራፊ ስራ ነው፡፡ ይህ ለጂሃዲስቱ እንደ ገንዘብ ጥላ ይሆንለታል ማለትም ገንዘብ በፈለገ ጊዜ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሊሸጥ ይችላል፤ የባሪያ ንግድ ያካሂዳል”

እንደዚሁም በተመሳሳይ ሁኔታ ሼህ አቡ ኢሻቅ አል-ሁዌይኒ በሌላ ጊዜ ባደረገው ንግግር “Jihad Is Solution to Muslims' Financial Problems” (Egyptian Shaykh al-Huwayni) ማለትም “ለሙስሊሞች የገንዘብ ችግር ጂሃድ መፍትሄ ነው” በማለት ተናግሯል። አሁንም ሼሁ ይህንን የተናገረው ስለ ጂሃድ ብቻ አልነበረም። መሐመድ በሕይወት በነበረበት ዘመን በጦርነት ተማርከው ለባርነት እየተሸጡ ለዝሙት ተግባር ስለሚውሉት ሴቶች በእነርሱ አጠራር ስለ ዝሙት ባርያዎች (sex slaves) ሲናገር “የዝሙት ባርያ ከፈለግሁ በቀጥታ ወደ ገበያ እሄዳሁ፣ የወደድኳትንም ሴት እመርጥና እገዛታለሁ” ነው ያለው።

(ምንጭ፡-

http://www.wikiislam.net/wiki/Video:_Shaykh_alHuwayni:_%22When_I_want_a_sex_slave,_I_just_go_to_the_market_and_choose_the_woman_I_like_and_purchase_her%22)

ሼሁ በሀገሩ የዐረብ ቴሌቭዥን ጣቢያ ላይ ቀርቦ ያደረገውን ሙሉውን ንግግር ከፈለጉ በ youtube ላይ “Video: Shaykh al-Huwayni: "When I want a sex slave, I just go to the market and choose the woman I like and purchase her” ብለው ጉበተው መመልከትና መስማት ይችላሉ።

ሼሁ ያደረገውን ንግግር መጀመሪያ ላይ በግብፅ ኢስላማዊ ፓሬሶች ላይ የተለቀቀ ሲሆን ሰዎች ዐረብኛውን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች እየተረጎሙ በየሚዲያዎቻቸው አሰራጭተውታል። ሼሁም ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ May 22, 2011 ዓ.ም ስለተናገረው ነገር ምላሽ እንዲሰጥ አል-ሂከማ በተሰኘው ኢስላማዊ የሳተላይት ቴሌቭዥን ጣቢያ ላይ በድጋሚ ቃለ መጠይቅ ተደርጎለት ነበር። በዚህም ጊዜ የሰጠው መልስ ተመሳሳይ ነው። በወቅቱ ስለ ጂሃድና ስለ ዝሙት ባርያዎች (sex slaves) በተናገረበት በዚህ አስደንጋጭና አወዛጋቢ ንግግሩ ድፍን የዓለምን ትኩረት ስቦ ነበር። የዓለም ሚዲያዎችም አጀብ ተሰኝተዋል። ሰብአዊ መብት ተሟጋቾችንም “እኮ እንዴት!?” በማለት ቆፍጠን ብለው እንዲነሱ አድርጓቸው ነበር። የሼሁ ንግግር በወቅቱ በእርግጥም ብዙዎችን አስደምሞ ነበር። ገሚሱን ደግሞ በወደው አይስቁም ፈሊጥ ሳይወድ በግድ ፈገግ አሰኝቶታል። እኔ ግን ይህን የተናገረበት ምክንያት መሠረትነት ስላለው ነው እንጂ ወዶ የተናገረው አይመስለኝም። መሠረቱ ምንድን ነው ካላችሁ ቅዱሳን ሐዋርያት ደገኛይቱን ወንጌል ሲጽፉልን “በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል” ብለው እንደጻፉልን ሁሉ በእስልምናውም የዚህ ሼህ አነጋገር መሠረቱ ነቢያቸው መሐመድ ነው። መስራቹ መሐመድ በቁርአን 2:191፣ 9:5፣ 8፡41 ላይ ግልጽ ባለ አነጋገር “ባገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ማርኳቸውም፤ አሰቃዩዋቸውም፤ እነሱንም ለመጠባበቅ በየመንገዱ ተቀመጡ...ከማንኛውም ነገር በጦር ከከሓዲዎች የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልዕከተኛው የተገባ መሆኑን ዕወቁ” ብለው መመሪያ ካስቀመጡ የዛሬው የመሐመድ ተከታይ ታዲያ ዛሬ ላይ ቆሞ “ለሙስሊሞች የገንዘብ ችግር ጂሃድ መፍትሄ ነው” ብሎ ቢናገር ምን ይደንቃል? የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች እምነታቸውን ያስፋፉትና የገንዘብ አቅማቸውን ያሳደጉት በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር። አሁን ነገሩን የበለጠ አስገራሚም አሳዛኝም የሚያደርገው ነገር ተከታዮቹ በዚህ በሰለጠነው ዓለም እየኖሩ ነገር ግን ከ1400 ዓመት በፊት የነበረውን ኋላ ቀርና መሀይማዊ አስተሳሰብ ዛሬም ድረስ ማሰባቸው ነው። ምቹ ሁኔታዎችን ካገኙ ደግሞ ያሰቡትን ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይሉ ይታወቃል። በተግባርም እያየነው ነው።

